ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

# የግብርና ሚኒስቴር የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

አዲስ አበባ

ነሐሴ 2015 ዓ.ም

# ማውጫ

ይዘት..........................................................................................ገጽ


1. መግቢያ ........................................ 1

2. ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት ........................................ 1

2.1 የዕቅድ ዝግጅት፣የክትትልና ግምገማ እና የስታቲስቲክስ መረጃ አስተዳደር አሰራር ማሻሻል ........................................ 1

2.2. የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል ........................................ 1

2.3. የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል ........................................ 2

2.4. የኢንፎርሜሽን፣ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል ........................................ 2

2.5. የአጋርነት እና የህዝብ ግንኙነት አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል ........................................ 3

2.6. ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልሎች የሚደረገውን ድጋፍና ክትትል ማሻሻል ........................................ 3

2.7. የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና የክትትል ሥራዎችን ማሻሻል ........................................ 4

2.8. የሴቶችና ማሕበራዊ ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነትን ማሻሻል ........................................ 4

2.9 የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎችን ማሻሻል ........................................ 5

3. ገበያ ተኮር የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ........................................ 6

3.1. የአነስተኛ ይዞታ ሰብልና ሆርቲካልቸር ልማት ........................................ 6

3.2 በሰፋፊ እርሻ ኢንቨስትመንት የለማ ሰብልና ሆርቲከልቸር ........................................ 6

3.3 በአነስተኛ አርሶ አደሮች እና በሰፋፊ እርሻ በመስኖ የለማ ሰብልና ሆርቲካልቸር ........................................ 7

3.4 ቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ልማት ........................................ 7

3.5 የሰብልና ሆርቲካልቸር ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት ........................................ 7

3.6 የእፅዋት ጥበቃ አገልግሎት ማስፋፋት ........................................ 9

3.7 የከተማ የሰብልና ሆርቲከልቸር ልማት ........................................ 12

4. ገበያ ተኮር የእንስሳትና ዓሳ ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ........................................ 12

4.1 የአነስተኛ ይዞታ የእንስሳትና ዓሳ ምርት ........................................ 12

4.2 መኖ ልማት ........................................ 12

4.3 የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ........................................ 13

4.4 የእንስሳት ጤና አገልግሎት ማሻሻል ........................................ 14

4.5 የእንስሳትና ዓሳ ኤክስቴንሽን ........................................ 16

4.6 የከተማ የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ........................................ 16

5. ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ........................................ 17

5.1 የተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ........................................ 17

5.2. የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ........................................ 20

5.3. የአፈር ሀብት ልማት ........................................ 21

**5.4. የአነስተኛ ይዞታ መስኖ ልማት** 24
6. የደን ልማት 25
7. የብዝሀ ህይወት ጥበቃ አጠቃቀም 26
8. የግብርና ኢንቨስትመንትና ግብርና ግብይት 28
**8.1 የሰፋፊ አርሻና እንስሳት ልማት የግል ኢንቨስትመንት** 28
**8.3 የግብርና ግብዓት አቅርቦት** 32
**8.4 የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት** 34
9. ህብረት ስራ ማህበራት 35
10. ግብርና ምርምር 37
11. የግብርና ትራንስፎርሜሽን 38
12. የግብርና ቁጥጥር ስራዎች 39
13. ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች 44
**13.1 በግብርና የሚፈጠር የሥራ ዕድል** 44
**13.2 ምግብና ስርዓተ ምግብ** 45
**13.3 ምግብ ዋስትና** 48
**13.4 የአየር ንብረት ለውጥ** 49
**13.5 የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳዩች** 52
14. የበጀት አጠቃቀም 55
15. በ9 ወር የአፈጻጸም ግምገማ የተሰጡ አቅጣጫዎች አፈጻጸም 57
16. የግብርና ሚ.ር የ2015 ዓ.ም ተግዳሮቶች. መፍትሄዎች፣ ተሞክሮዎችና ለ2016 በጀ ዓመት 61
17. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች 66
18. ማጠቃለያ 67
19. የ2015 በጀት ዓመት ኢላማዎችና አፈፃፀም 68

## 1. መግቢያ

የ2015 ዓመታዊ ዕቅድ የዘርፉን ቁልፍ የውጤት መስኮችና ውጤቶችን ለማሳካት የሚያስችሉ የትግበራ መስኮችን መሰረት በማድረግና ግልፅ ዒላማዎችን በማስቀመጥ ለማሳካት የሚያስችሉ የማስፈጸሚያ ስልቶችን በማካተት እንዲዘጋጅ በማድረግና በዕቅዱ ላይ የሚመለከታቸውን የፌደራልና የክልል ፈፃሚ አካላት ጋር መግባባት በመድረስ ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡

በዚህም መሰረት የበጀት ዓመቱ አፈፃፀም በቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች ተዘጋጅቶ በበቂ ትንትና ተደግፎ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ሪፖርቱ የፊዚካል ስራዎች አፈፃፀም በዋና ዋና አመልካቾች እና በተለየ ትኩረት እየተከናወኑ የሚገኙ ሀገራዊ ፕሮግራሞችና ኢኒሸቲቮች አፈጻጸም፣ ፕሮግራም በጀት አፈፃፀም፣ የኦዲት ግኝት አፈፃፀም፣ የተቋማዊ ለውጥና አገልግሎት አሰጣጥ እና ለክልሎች የተሰጠ ድጋፍን እና በበጀት ዓመቱ የአፈጻጸም ግምገማ የተሰጡ አቅጣጫዎች አፈጻጸም አካቶ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

## 2. ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት

### 2.1 የዕቅድ ዝግጅት፣የክትትልና ግምገማ እና የስታቲስቲክስ መረጃ አስተዳደር አሰራር ማሻሻል

የሚ/ር መ/ቤቱን አቅም የማጎልበት፣ የሀብት አጠቃቀምን እና አገልግሎት አሰጣጥን ከማሻሻል አንጻር በበጀት ዓመቱ ውስጥ የእቅድ ዝግጅትን እና ትግበራን ከማሻሻል አኳያ የ2014 በጀት ዓመት የፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ሪፖርትና የ2015 በጀት ዓመት እቅድ ተዘጋጅቶና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመገምገም ለበላይ አካል በወቅቱና ጥራቱን በጠበቀ ሁኔታ ተልኳል፡፡ በተመሳሳይም ሁኔታ በ2015 በጀት ዓመት የፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ሪፖርት ጥራቱን በጠበቀና በስታንዳርድ መሰረት ተዘጋጅቶ በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካለት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ የክትትልና ግምገማ ሥርዓትን ዘመናዊ ለማድረግ የመደበኛ ፕሮግራሞች አፈጻጸም በፓዎር ቢ አይ ሶፍትዌር እንዲገባ የማድረግ ስራ ተከናውኗል፡፡

### 2.2. የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል

የሰው ሀብት ልማት አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ለማሻሻል በተደረገው ጥረት አዲሱ የመ/ቤቱ መዋቅር ተጠናቆ የሰው ሃይል ድልድል ተጠናቋል፡፡ ግልጽነት የሰፈነበት የሰው ሃይል ስምሪት ከማካሄድ አንጻር ቋሚ፣ ጊዜያዊ እና ለፕሮጀክቶች አዲስ ሠራተኛ ቅጥር ለማከናወን በበጀት ዓመቱ 20% ለማከናወን ታቅዶ 20% በቀረበው መሰረት ቅጥር ተፈጽሞ በሥራ ላይ እንዲሰማሩ ተደርጓል፡፡ የአመራርና የባለሙያ አቅም ለማሳደግ በአመራር ክህሎት በለውጥ አመራርና የቢሮ ሥነምግባር ለ1,300 ሰራተኞች ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ1,343 ወይም 100+% ለማከናወን ተችሏል፡፡

የሰራተኛውን እርካታን በማሳደግ ፍልሰትን ከመቀነስ አንጻር በመ/ቤቱ በተሰሩ የሪፎርም ስራዎችና መ/ቤቱ የተሻለ የስራ አካባቢ በመፈጠሩ በበጀት ዓመቱ ፍልሰቱን ከ0.8% ወደ 0.6% ለማድረስ በታቀደው መሠረት ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡

## 2.3. የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል

የፋይናንስና የንብረት አስተዳደርን ከማሻሻል አንጻር በበጀት ዓመቱ መ/ቤቱ ቀደም ባሉት ዓመታት ነቀፌታ አዘል የኦዲት ግኝት ውስጥ የነበረውን በ2014 በጀት ዓመት ተሰብሳቢ እና ተከፋይ ሂሳቦችን በማወራረድ ነቀፌታ ወደ ሌለበት ደረጃ እንዲሸጋገር ተደርጓል፡፡ በዚህ በጀት ዓመትም ሂሳቦችን በወቅቱ የማወራረድ ስራዎች ተከናውኗል፡፡

የፋይናንስ አጠቃቀም በየፕሮግራሞች በ2015 በጀት አመት በግብርና ሚኒስቴር በበጀት ዓመቱ በመደበኛ ብር 500.29 ሚሊየን ታቅዶ ብር 1,113,77 ቢሊየን (100⁺%) ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን የካፒታል በጀት ደግሞ ብር 15,511.18 ሚሊየን በዕቅድ ተይዞ ብር 22,733.33 ሚሊየን (100⁺%) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በአጠቃላይ በግብርና ዘርፍ በመደበኛና በካፒታል ብር 16,011.47 ቢሊየን በዕቅድ ተይዞ ብር 23,847.10 ቢሊየን (100⁺%) ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

የመንግስት ክፍያን ኤሌትሮኒክ ከማድረግ አንጻርም 70% ክፍያዎች በአሌክትሮኒክ መፈጸም ተችሏል፡፡ በበጀት ዓመቱ የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ 50% ለማድረስ ታቅዶ 44% በመፈጸም የእቅዱን 88% ማከናወን ተችሏል፡፡ መሰረታዊ አገልግሎቶች በቅልጥፍና በመስጠት የደንበኞችን እርካታ ለማሳደግ በተደረገው ጥረት የንብረት አያያዝን ኦቶሜት በማድረግ ወደ ተቀናጀ የፋይናንስ ስርዓት ከማስገባት አንጻር 85% ማከናወን ተችሏል፡፡

## 2.4. የኢንፎርሜሽን፣ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል

የመ/ቤቱን የመረጃ ቋት ከማደራጀት አኳያ በተለያየ ቦታ ተዘጋጅተው የነበሩ መረጃዎችን ወደ አንድ የመረጃ ሥረዓት /Agr.Data Hab/ ለማምጣት በተደረገው እንቅስቃሴ ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር 50 የመረጃ ሥርዓቶችን ወደ አንድ መረጃ ሥርዓት ለማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን በበጀት ዓመቱ እቅድ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡ ቀሪ መረጃ ሥርዓቶች የማሰበሰብ ወደ አንድ የማደራጀትና ለተጠቃሚዎች የማስተዋወቅና አገልግሎት ላይ የማዋል ሥራ የሚሰራ ይሆናል፡፡

ወረቀት አልባ አሰራርን ለመተግበርም በተደረገው እንቅስቃሴ 20% ለማከናወን በታቀደው መሰረት የአሰራር ስርዓት የሚያሳልጥ ሶፍትዌር ማበልጸግ ሥራ ሙሉ በሙሉ ተከናዉኗል፡፡የተገልጋዮች እርካታም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ 80% ለማድረስ ታቅዶ 70% ማድረስ ተችሏል፡፡

## 2.5. የአጋርነት እና የህዝብ ግንኙነት አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል

የሚ/ር መ/ቤቱንና ተጠሪ ተቋማትን ግንባታ በሀገር ውስጥና ከውጭ ድጋፍ ለማሰባሰብና ጥቅም ላይ ለማዋል ተጀምሯል። ከዚህ አንጻርም ባለፈው በጀት ዓመት በተጀመረው መሰረት የሶስት ፕሮጀክቶች ዝግጅት ተጠናቆና በለጋሽ አካላት ተፈርሞ ሥራ በመጀመር ላይ ይገኛል። በዚሁ መሰረት የኢትዮጵያ የምግብ ስርዓት መቋቋሚያ ፕሮግራም 602 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (400 ሚ/ን በብድር 202 ሚ/ን በእርዳታ) የስደተኞች ተጽእኖ ምላሽ ልማት ፕሮጀክት ለሁለተኛ ዙር 180 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንዲሁም ለአርብቶ አደር ስነ-ምግብና የምግብ ዋስትና መቋቋሚያ ፕሮግራም 38.9 ሚሊዮን ዶላር ከውጭ ድጋፍ እንዲሁም 3.8 ሚሊዮን ዶላር ከመንግስት ድጋፍ በድምሩ 42.7 ሚሊዮን ዶላር በአደጋ ስጋት ቅነሳና አካታች የኢኮኖሚ እሴት ማሻሻያ ፕሮጀክት 115 ሚ/ን ዶላር የፋይናንስ ሀብት ለማግኘት ተችሏል። በተመሳሳይ ሁኔታ የአሳታፊ የግብርና ትራንስፎርሜሽንና አየር ንብረት ለውጥ መቋቋም ፕሮግራም የ185.6 ሚ/ን ዶላር ፕሮጀክት ሰነድ ተፈርሟል። የበጀት ምንጩም 94.6 ሚ/ን ዶላር እርዳታ ፣60.7 ሚ/ን ዶላር ብድርና 30.3 ሚ/ን ዶላር ከመንግስት ነው:: በጠቅላላው በ4ቱም ፕሮጀክቶች 1,125.33 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት ተችሏል። የመጀመሪያው ፕሮግራም ለ7 ዓመት የሚተገበር ሲሆን ቀሪዎቹ አራት ፕሮጀክቶች ለ5 ዓመት የሚተገበሩ ይሆናል።

መረጃዎችን በተለያዩ የተግባቦት ዘዴዎች ለህዝብና ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ለማድረግ በተደረገው ከፍተኛ ጥረት የተዘጋጁ መድረኮች የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ፣ መረጃዎች በምስልና በጽሑፍ ተቀርጸው በመ/ቤቱ ፌስ ቡክና በዌብሳይት በመጫን ለተጠቃሚዎች ሁሉ ተደራሽ በማድረግ ከ100% በላይ ለመፈጸም ተችሏል። የበላይ አመራሩ ወቅታዊ በሆኑ የግብርና ጉዳዮች ላይ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን እንዲሰጥ ተደርጓል።

## 2.6. ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልሎች የሚደረገውን ድጋፍና ክትትል ማሻሻል

ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልሎች ድጋፍ በማድረግ አፈጻጸምን ለማሻሻል በተሰጠው ሥራ የተጠሪ ተቋማት ዕቅድን ከዘርፍ ዕቅድ ጋር ማናበብና የማጣጣም ሥራ ተሠርቶና የዕቅድ ኦረንቴሽን ተሰጥቶ ወደ ሥራ ተገብቷል። የ9 ወር አፈጻጸም የተጠሪ ተቋማት ሥራ ሃላፊዎች በተገኙበት ተገምግሞ ግብረመልስ ተሠጥቷል። በተመሳሳይ ሁኔታ የክልሎችን ዕቅድ ከዘርፍ ዕቅድ ጋር ማናበብና ማጣጣም ሥራ ተሰርቶና በጋራ መድረክ ተገምግሞና ኦረንቴሽን ተሰጥቶ ወደ ትግበራ ተገብቷል። በየሩብ አመቱ የክልሎች የስራ አፈጻጸም ግምገማ በማካሄድ በየንዑስ ዘርፉ ከክልል አቻ ዘርፍ ጋር የጋራ አቅጣጫ በማስቀመጥ ወደ ስራ ተገብቷል። ለክልሎች ወቅታዊ የአቅም ግንባታ ድጋፍ ለመስጠት በየዘርፉ በ4 ክልሎች በመስክ በመገኘት ድጋፍ ተደርጓል።

## 2.7. የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና የክትትል ሥራዎችን ማሻሻል

በመ/ቤቱ በብልሹ አሰራር ዙርያ ጥቆማ ከተደረገባቸው ውስጥ በበጀት ዓመቱ ውስጥ የመጡ ጥቆማዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥና ቦታቸው ድረስ በመሄድና መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጣራት ትክክለኛ ውሳኔ እንዲያርፍባቸውና የማስተካከያ ሥራ በታቀደው መሰረት ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡

ለብልሹ አሰራር የተጋለጡ አሰራሮች በጥናት በመለየት የማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብን በተመለከተ የአሰራር ስርአት ጥናት ለማድረግ መጠይቆችን በማዘጋጀት እና ችግሮችን በመለየት በእቅዱ መሰረት ጥናቱን በማጠናቀቅ የማሻሻያ ሃሳብ ለሚመለከተው አካል ለውሳኔ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

የሀብት ምዝገባ ያካሄዱ አመራሮች እና ባለሞያዎች ድርሻ ለማሳደግ ወደ ዲጅታል የሀብት ምዝገባ ከመገባቱ በፊት መሞላት ያለበትን ቅፅ 001 ሁሉም የሥራ ክፍሎች እንዲሞሉና መረጃው ተደራጅቶ እንዲያዝ የማድረግ ሥራ በታቀደው መሰረት ተሰርቷል፡፡

## 2.8. የሴቶችና ማሕበራዊ ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነትን ማሻሻል

የህፃናት ማቆያ ማዕከልን በሚመለከት ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመቀናጀት ምቹ ቦታ የመለየትና ዲዛይኑን የማሻሻል ስራ ተሠርቷል፡፡ እንዲሁም የሌሎች ተቋማት መልካም ተሞክሮዎችን ልምድ በመዉሰድ ምቹና ሳቢ ማዕከል በማቋቋም 5 /አምስት/ ሴት ሰራተኞችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ በበጀት ዓመቱ ሳይከናወን ቀርቷል፡፡ በተመሳሳይም በሁሉም ተጠሪ ተቋማት ዉስጥ እንዲቋቋም የክትትልና ድጋፍ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

ወደ አመራር የመጡ ሴት ሰራተኞች ብዛት ለማሳደግም በበጀት ዓመቱ 20 ሴቶችን ወደ አመራር እንዲመጡ ለማድረግ ታቅዶ በመ/ቤቱ በተደረገው የአዲስ ሰራተኛ ድልድል ለሴቶች በተቀመጠው አዎንታዊ ድጋፍ ተጠቃሚ በማድረግ 18 ሴቶች ወይም የእቅዱ 90% ሴቶች ወደ አመራር እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ የሴቶችን አቅም ከማጉልበትና ክህሎት ከማዳበር አንጻር በተለያዩ ሙያዎች ለ1,395 ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ1,435 (100$^{+}$%) ተሰጥቷል፡፡

ለአካል ጉዳተኛ ሰራተኞችና ተገልጋዮች ምቹ የስራ ሁኔታና ቦታ ከመፍጠር አኳያም በበጀት ዓመቱ በመጸዳጃ - ቤቶች በአሳንሰር አካባቢ ህንጻዎች መወጣጫ አካባቢ ለአካል ጉዳተኞች በምቹ ሁኔታ እንዲገነባ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል እቅዱም በሙሉ ተከናውኗል፡፡

## 2.9 የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎችን ማሻሻል

### የአረንጓዴ አሻራ የችግኝ ተከላ

የችግኝ ተከላን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ 75,000 ችግኝ ለመትከል ታቅዶ 75,000 ችግኝ 100% ተተክሏል፡፡

### ድጋፍ ለሚሹ ቤተሰቦች የቤቶች ግንባታ ማስጀመር

ከክልሉ ግብርና ቢሮ እና ቦንጋ ከተማ አስተዳደር ጋር በመቀናጀት ድጋፍ የሚሹ ቤተሰቦች ልየታ የተካሄደ ሲሆን በዚሁ መሰረትም የደሃ ደሃ የሆኑ 2 አባወራ እና 3 እማወራ በድምሩ የ5 ቤተሰቦች ቤት ፕሮግራም የማስጀመር ሥራ ተሰርቷል፡፡ የቤቶች ግንባታ በተመለከተ አንድ በዋናው መ/ቤት እና 4ቱ በተጠሪ ተቋማት እንዲገነባ ታቅዶ ለግንባታ የሚውል ብር 14,670,776 ብር በጀት ተመድቦ ዲዛይን ተሰርቶ የቦታ ርክክብ ተደርጎ የአምስቱ ግንባታ ተጀምሮ 5,880,000 ብር ሥራ ላይ ዉሏል፡፡

በተጨማሪም ለእነዚህ 5 ቤተሰቦች የየራሳቸው ቤት ተገንብቶ እስኪጠናቀቅ ለመኖር የሚያስችል የመኖሪያ ቤት ኪራይም ውል በመዋዋል ቤት ግንባታ የሚካሄድላቸው ቤተሰቦች ያለ ችግር እንዲኖሩ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ የተጀመረው የአቅመ ደካማ ቤተሰቦች መኖሪያ ቤቶች ግንባታ አስኪጠናቀቅ ለእነዚህ ቤተሰቦች የሚያስፈልግ የምግብ አስቤዛ የማሟላት ሥራ ተሠርቷል፡፡

## 3. ለተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ

የማህበራዊ ድጋፍ አገልግሎትን ለማሳደግ ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናትን ከመደገፍ አንጻር በበጀት ዓመቱ 400 ልጆችን ለመደገፍ ታቅዶ 400 (100%) በገንዘብ 382,609 የማድረስና እንዲሁም የተለያየ አልባሳትና የምግብ ቁሳቁስ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም 80 ወላጆቻቸዉን ያጡ ህፃናትን ለመደገፍ ታቅዶ ለሰዋሰው አዕምሮ ህሙማን መርጃ እና በኤች አይ ቪ / ኤድስ ወላጆቻችውን ላጡ ህፃናት በአጠቃላይ ለ115 ህፃናት ብር 110,000 የሚገመት የምግብ እህሎች እና የአልባሳት ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ደቡብ-ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ግብርና እና የትምህርት ቢሮ ጋር በመቀናጀት የትምህርት ቁሳቁሶች የሚያስፈጋቸዉ 150 ቤተሰቦች በመለየት የትምህርት ቁሳቁስ 150 ቦርሳ 150 ደርዘን ደብተር 30 ደርዘን እስክብርቶ 30 ደርዘን እርሳስ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚሳተፍባችው የበጎ አድራጎት ተግባራት መካከል አንዱ የደም ልገሳ ሲሆን 70 የሚሆኑት ሰራተኞች ደም የለገሱ ሲሆን ከጠቅላላ ሰራተኛው ውስጥ 10 በመቶ ይሸፍናል፡፡

# 3. ገበያ ተኮር የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ

## 3.1. የአነስተኛ ይዞታ ሰብልና ሆርቲካልቸር ልማት

በሰብል ልማት በ2014/2015 ዓ.ም ምርት ዘመን በአነስተኛ አርሶ አደሮች የአዝርዕት ሰብል 13.4 ሚ/ን ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ 14.06 ሚ/ን ሄ/ር መሬት በዘር ተሸፍኗል፡፡ ከዚህም 393.3 ሚ/ን ኩ/ል (98.3%) ምርት ማግኘት ተችሏል፡፡ የአነስተኛ አርሶ አደሮች የሆርቲካልቸር ሰብል 452 ሺ.ህ ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ 656.27 ሺ.ህ ሄ/ር መሬት በዘር ተሸፍኗል፡፡ ከዚህም 118.6 ሚ/ን ኩ/ል (100+%) ምርት ተገኝቷል፡፡ በአነስተኛ አርሶ አደሮች የዋና ዋና ሰብሎች ምርታማነት 31 ኩ/ል በሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 30 ኩ/ል በሄ/ር ማግኘት የተቻለ ሲሆን ይህም የዕቅዱን 95 በመቶ ማሳካት ተችሏል፡፡

በኩታ ገጠም እርሻ የተዘራ መሬት ስፋት አፈጻጸምን በተመለከተ 6.1 ሚ/ን ሄ/ር ለማልማት ታቅዶ ሙሉ ለሙሉ ማልማት ተችሏል፡፡ በኩታ ገጠም እርሻ 4 ሚ/ን አርሶ አደር ለማሳተፍ ታቅዶ 7.4 (100+%) ሚ/ን አርሶ አደር ተሳትፏል፡፡

የቡና ልማት ምርታማነትን 7.6 ኩ/ል/ ሄ/ር እና የቡና ምርትን 810 ሺ.ህ ቶን ለማድረስ ግብ ተይዞ የምርት ትመና ሥራ ተካሂዷል፡፡ በዚህ መሰረት ምርታማነት 7.17 ኩ/ል/ ሄ/ር ሲሆን፣ ጠቅላላ ሀገራዊ የቡና ምርት 761.5 ሺ.ህ ቶን ሊሆን ችሏል፡፡

የበልግ እርሻ እንቅስቃሴን ስራን በተመለከተ በአማራ፣ኦሮሚያ፣ሲዳማ፤ደቡብ እና ደ/ምዕራብ ክልሎች 2,484,144 ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ እስከ 19/10/2015 ዓ.ም ድረስ **2,744,657** ሄ/ር መሬት ታርሶ **2,691,758** ሄ/ር መሬት በዘር ተሸፍኗል፡፡ በዘር ከተሸፈነው መሬት ውስጥ በስንዴ (365,625 ሄ/ር) ፣በበቆሎ (1,015,133 ሄ/ር) ፣ በገብስ (281,595 ሄ/ር) ፣በማሽላ (157,043 ሄ/ር) እና ሌሎች ሰብሎች 872,362 ሄ/ር በድምሩ **2,691,758** ሄ/ር መሬት በዘር ተሸፍኗል፡፡ ከዚህ ውስጥም 65 ሚሊዮን ኩ/ል ምርት ይገኛል ተብሎ ይገመታል፡፡

## 3.2 በሰፋፊ እርሻ ኢንቨስትመንት የለማ ሰብልና ሆርቲከልቸር

በ2014/15 ምርት ዘመን በባለሀብቶች እርሻ 1.13 ሚ/ን ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ 980 ሺ.ህ ሄ/ር (82 በመቶ) በሰብል ተሸፍኗል፡፡ ከዚህም መሬት በጥቅሉ 30 ሚ/ን ኩ/ል (100+%) የአዝርዕት ምርት ይገኛል ተብሎ ተገምቷል፡፡ በአትክልትና ፍራፍሬ 1.8 ሚ/ን ኩ/ል ምርት ለማምረት ታቅዶ 1.76 ሚ/ን ኩ/ል (98%) ምርት ተገኝቷል፡፡

## 3.3 በአነስተኛ አርሶ አደሮች እና በሰፋፊ እርሻ በመስኖ የለማ ሰብልና ሆርቲካልቸር

በ2014/15 ምርት ዘመን በመስኖ 1.4 ሚ/ን ሄ/ር ሰብል ለማልማት የታቀደ ሲሆን 2.27 ሚ/ን ሄ/ር (100+%) በዘር ተሸፍኗል፡፡ ከዚህ ውስጥ ከውጪ የሚገባ የስንዴ ምርትን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት የተቀመጠውን ሀገራዊ ግብ ለማሳካት የመስኖ ስንዴ ልማት (በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ፤ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ ሲዳማ፤ ሶማሌ፤ጋምቤላ፤ቤንሻንጉልና አፋር ክልሎች) 1.32 ሚ/ን ሄ/ር መሬት በመሸፈን 52 ሚ/ን ኩ/ል ምርት ለማምረት ታቅዶ 1,356,743 ሄ/ር (100+%) መሬት በዘር የተሸፈነ ሲሆን በባህላዊ 274,853 ሄ/ር እና በዘመናዊ ዘዴ 62,852 ሄ/ር በድምሩ 337,705 ሄ/ር መሬት በበጋ መስኖ የለማ የስንዴ ማሳ ሰብል ተሰብስቦ 47,024,513 ኩ/ል ምርት ተገኝቷል:: የተገኘ ሲሆን በ31,531.65 ሄ/ር መሬት ላይ የተዘራ ስንዴ በውሃ እጥረት፣ በዝናብ መብዛት፣ በጎርፍ ምክንያት ምርት ማግኘት አልተቻለም፡፡ በ2014/15 ምርት ዘመን በመስኖ አትክልትና ፍራፍሬ 413 ሺህ ሄ/ር ለማልማት ታቅዶ 433.9 ሺህ ሄ/ር (100+%) በዘር ተሸፍኗል፡፡

## 3.4 ቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ልማት

በ2014/15 ምርት ዘመን የቡና ማሣ ምርታማነት ማሻሻያ ሥራዎችን በመፈፀም ለምርት የደረሰውን 1,062,034 ሄ/ር (በአርሶ አደር 944,393 እና አልሚ ባለሃብት 117,641 ሄ/ር) የቡና ማሣ ምርታማነቱን በሄ/ር 7.6 ኩ/ል በማድረስ 810 ሺህ ቶን ምርት ለማምረት ግብ ተይዟል፡፡ በመሆኑም በዋና ዋና ቡና አብቃይ እና የቡና ልማት እየተስፋፋ በሚገኝባቸው ክልሎችና ዞኖች በበጀት ዓመቱ የቡና ቅድመ-ምርት ትመና ዳሰሳ ጥናት መሠረት ምርት መስጠት ከሚችለው 1,062,034 ሄ/ር የቡና መሬት ላይ 761,478 ቶን ምርት የተገኘ ሲሆን ምርታማነቱ 7.17 ኩ/ል/ሄ/ር ማድረስ ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ የሻይ ማሳ ሽፋን 3,729 ሄ/ር (691 በአውትግሮወር እና 3,038 በአልሚ ባለሃብት በማልማት፤ ምርት ከሚሰጥ 3,337 ሄ/ር፣ 12.73 ሺህ ቶን ምርት፣ ምርታማነት 39.3 ኩ/ል/ሄ/ር ለማድረስ የታቀደ ሲሆን 12.73 ሺህ ቶን የደረቀ ሻይ ምርት ለማምረት ታቅዶ 9.28 ሺህ ቶን (73%) ተመርቷል፡፡

የቅመማ ቅመም ልማት በዓመታዊና በቋሚ ሰብል ለመሸፈን 441,759.5 ሄ/ር ታቅዶ 443,859 ሄ/ር (100+%) የተሸፈነ ሲሆን ምርት ከሚሰጠው 443,859 ሄር 802 ሺህ ቶን ምርት ለማምረት ታቅዶ 790.2 ሺህ ቶን (98.5%) ተከናውኗል፡፡

## 3.5 የሰብልና ሆርቲካልቸር ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎት

የእርሻና ሆርቲካልቸር ኤክስቴንሽን አገልግሎት በማጠናከር አርሶአደሩ የአዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮች ተጠቃሚ በማድረግ በምርትና ምርታማነት እድገት ከፍ ለማድረግ የተለያዩ ተግባራት

እየተከናወኑ ይገኛል፡፡ በዚሁ መሰረት በበጀት ዓመቱ በሁሉም ክልሎች የኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎችን 12,769,000 ለማድረስ ታቅዶ 12,190,906 (95.4%) ማድረስ ተችሏል፡፡ የሙሉ ፓኬጅ ተጠቃሚዎችን ቁጥር ማሳደግ 8,657,000 ለማድረስ ታቅዶ 5,848,600 (67.5%) ማድረስ ተችሏል፡፡

የሞዴል አርሶ፣ አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሮችን ቁጥር 4,114,000 ለማድረስ ታቅዶ 3,695,000 (89.8%) ማድረስ የተቻለ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ወንድ 2,956,000 (80%) ፣ ሴት 333,000 (9%)፣ ወጣቶች 406,000 (11%) ናቸው፡፡ በሜካናይዜሽን ተጠቃሚ ማሳደግ በትራክተር የታረሰ መሬት 2.85 ሚ/ን/ ሄ/ር ታቅዶ የነበረ ሲሆን 2.7 ሚ/ን/ ሄ/ር የተከናወነ ሲሆን ከአመቱ ጋር ሲነፃር 94.74 በመቶኛ ተከናውኗል፡፡

መልካም ተሞክሮዎችን (የኩታ ገጠም እርሻ፣ የሙሉ ፓኬጅ፣ ውጤታማ የሆኑ ሰርቶ ማሳያዎችን) በመለየትና በመቀመር ወደ ሌሎች አከባቢዎች እንዲሰፋ ለማድረግ 8 (ስምንት) ሰነድ ለማዘጋጀት ታቅዶ በአጠቃላይ 4 ኮሞዲቲዎች ላይ 8 (100%) የምርጥ ተሞክሮ ቅመራ ሰነዶች ተጠናቆ ተዘጋጅቷል፡፡

ያልተዋወቁ አዳዲስ የሰብል ዝሪያዎች በአራት ክልሎች (በኦሮሚያ ፣ አማራ፣ በደ/ብ/ብ እና በሲዳማ) እንዲተዋወቁ ከክልሎች ጋር በቅንጅት በተመረጡ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላትና አርሶ አደር ማሳ ላይ በግማሽ ዓመቱ በ1,022 የሰርቶ ማሳያዎች ላይ ለማስተዋወቅ ታቅዶ በዚህ ዓመት 622 ሰርቶ ማሳያዎች ላይ ተከናውኗል፡፡ አፈፃፀሙም ከእቅዱ 60.8 በመቶ ነው፡፡

የኩታ ገጠም አሰራርን ለማጠናከር በተለያዩ ሰብሎች ላይ የሚሰጠውን ድጋፍና ክትትል ወደ 367,393 የኩታ ገጠም አደረጃጀት ለማድረስ ታቅዶ 354,540 አደረጃጀቶች በ888 ወረዳዎች በሚገኙ 12,918 ቀበሌዎች ተፈጥሮ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ ይህም አፈፃፀም ከዕቅዱ ጋር ሲነፃር 97.5% ነው፡፡ በእነዚህ በኩታ ገጠም አደረጃጀቶች ወንድ 6,953,914 ሴት 934,699 በድምሩ 7,888,613 አርሶ አደሮች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

በአርሶአደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ውስጥ በዚህ ዓመት 11,695 ሰርቶ ማሳያዎች ለማከናወን ታቅዶ 9,735 ሰርቶ ማሳያዎች በ2,240 ሄ/ር መሬት ላይ 113 ቴክኖሎጅ ዓይነቶች ላይ ተከናውኗል፡

በተመረጡ ሞዴል አርሶ አደሮች ማሳ (88,282 ፕሎቶች) ላይ የቴክኖሎጂ ማስፋት ስራ ለመስራት ታቅዶ በ19,333 ሄ/ር መሬት በ71,377 (80.85%) ፕሎቶች ላይ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች እንዲተዋወቁ ተደርጓል፡፡ የተሳታፊ ብዛትም ወንድ 77,124 ሴት 1,620 (2.06%) በድምሩ 78,744 አርሶ አደሮች ናቸው፡፡

አዳዲስ አሰራሮችንና ቴክኖሎጅዎችን በማስተዋወቅ ማስፋት እንዲቻል በ10 ክልሎች እና በ1 ከተማ አስተዳደር በክልል ደረጃ 11 የመስክ ቀን በዓል ለማካሄድ ታቅዶ 13 ጊዜ የተከናወነ ሲሆን በተዋረድም በየደረጃው በሚገኘዉ ዞኖች እና ወረዳዎች 42,474 የአርሶ አደር የመስክ በዓል ቀን የተከበረ ሲሆን

ወንድ 818,188 ሴት 554,836 (40.4%) በድምሩ 1,373,024 የሆኑ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች፣ ባለሙያዎች እና አርሶ አደሮች ተሳትፎ ልምድ እንድለዋወጡ ተደርጓል:: በአጠቃላይ ከ100% በላይ ተከናውነዋል።

## 3.6 የእፅዋት ጥበቃ አገልግሎት ማስፋፋት

የድንበር ዘለል ተዛማች ተባዮች አሰሳና መከላከል ተግባርን በተጠናከረና በተቀናጀ አግባብ በመደገፍ በበልግና በመኸር ወቅት በሰብል ላይ ሊደርስ የሚችሉ ጉዳቶችን ለመቀነስ በርካታ ተግባራት ማከናወን ተችሏል።

### ሀ) የበረሃ አንበጣ መከላከልና መቆጣጠር

በበጀት ዓመቱ በአራት ክልሎች (አፋር፣አማራ፣ ሶማሌ እና ኦሮሚያ) እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በ 175,000 ሄ/ር ላይ አሰሳ ለማድረግ ታቅዶ በ175,844 ሄ/ር በምድር ላይ አሰሳ በተካሄደው መሰረት ምንም ዓይነት የበረሀ አንበጣ ክስተት አለመኖሩን ተረጋግጧል።

### ለ) አዲሱ መጤ ተምች መከላከልና መቆጣጠር

በበጀት ዓመቱ 75,000 ሄ/ር ላይ ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በ65,498 ሄ/ር ላይ የክትትልና ድጋፍ ስራ የተሰራ ሲሆን አፈጻጸሙም በመቶኛ 87% ነው። በበጀት ዓመቱ ስምንት ክልሎች (ኦሮሚያ፣ ጋምቤላ፣ ትግራይ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ አማራ፣ ደቡብ እና ቤንሻንጉል ጉሙዝ) በ54 ዞኖች እና በ479 ወረዳዎች ላይ 723,957 ሄ/ር ተከስቶ በ104,364 ሄ/ር በኬሚካል እና 503,537 ሄ/ር በባህላዊ በድምሩ 607,901 ሄ/ር የመከላከል ስራ ተከናውኗል። ለዚህም ተባይ ቁጥጥር 100,848 ሊትር ፀረ-ተባይ ኬሚካል ጥቅም ላይ ውሏል።

### ሐ) መደበኛ ተምች መከላከልና መቆጣጠር

በበጀት ዓመቱ 50,000 ሄ/ር ላይ የአሰሳና መከላከል ስራ ለማከናወን ታቅዶ በ47,000 ሄ/ር ላይ (94%) የአሰሳ ስራ ተከናውኗል። በበጀት ዓመቱ ኦሮሚያ፣ አማራ፣ትግራይ፣ ደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ሲዳማ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ እና በጋምቤላ ክልሎች በ51 ዞኖች፣ በ221 ወረዳዎች ላይ በ479,593 ሄ/ር በሩዝ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ዳጉሳ፣ ጤፍ ሰብል እና የግጦሽ መሬት ላይ የተከሰተ ሲሆን በኬሚካል 195,662 ሄ/ር በባህላዊ 229,669 ሄ/ር በድምር 425,331 ሄ/ር ላይ መከላከል ተደርጓል። 179,522 ሊትር ፀረ ተባይ ኬሚካል ጥቅም ላይ ውሏል።

### መ) የግሪሳ ወፍ መከላከልና መቆጣጠር

በበጀት ዓመቱ 12 የግሪሳ ወፍ መራቢያ ስፍራ ለመለየት ታቅዶ 11 የማደሪያ ስፍራ (በአማራ 5፣አፋር 3፣ ኦሮሚያ 3) ተለይቷል። 35 ማደሪያ ቦታዎች የግሪሳ ወፍ ክትትል፣ አሰሳና የመንጋ ብዛት መገመትና መከላከል ለመስራት ታቅዶ በ55 የማደሪያ ቦታ ላይ ተከነውኗል። 30 ማደሪያ ቦታዎች

የግሪሳ ወፍ ክትትል፣ አሰሳና የመንጋ ብዛት መገመትና መከላከል ለማካሄድ ታቅዶ በ51 የማደሪያ ቦታ ላይ ተከናውኗል፡፡ 160 ሚሊዮን የሚገመቱ የግሪሳ ወፍ መንጋ በመኸርና በበጋ መስኖ ስንዴ የተከሰተ ሲሆን በ1,138 ሄ/ር የማደሪያ ስፍራ ላይ በአውሮፕላን ርጭት 2,275 ሊትር ፀረ-ወፍ ኬሚካል በመጠቀም የመከላከል ስራ ተካሂዷል፡፡ ይህም በግሪሳ ወፍ መንጋ ምክንያት ይደርስ የነበረውን ሁለት ሚሊዮን ኩ/ል (200,000 ቶን) የምርት ብክነት መቀነስ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ ውስጥ በተዛማች ተባይ 300,000 ሄ/ር ላይ የአሰሳና መከላከል ለማከናወን ታቅዶ በ288,342 ሄ/ር ማሰስ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀም በመቶኛ 96% ነው፡፡

**ሠ) የሳር ዘርና ቅጠለ ሰፋፊ አረሞች መከላከልና መቆጣጠር**

በበጀት ዓመቱ የሳር ዘርና ቅጠለ ሰፋፊ አረሞች ቁጥጥርና መከላከል 90,000 ሺህ ሄ/ር ታቅዶ 190,345 ሄ/ር በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ፣ በሲዳማ፣ በደ/ም/ኢትዮጵያ፣ በሱማሌ፣ በሀረሪና በድሬዳዋ ክልሎች ላይ በመኸር፣ በበልግና በበጋ መስኖ እንዲሁም በአትክልትና ፍራፍሬ ሰብሎች ላይ የአረም መከላከልና ቁጥጥር ድጋፍ ተደርጓል፡፡ መጤና ወራሪ አረም ቁጥጥርና መከላከል ደንብና መመሪያ ከባለድርሻ አካላት ጋር ከልሶ ለማፀደቅ የታቀደ ሲሆን ሰነዱን እንደገና የመከለስ ስራ ከግብርና ሚኒስቴር ህግ ጉዳዮች ስራ አስፈጻሚ ጋር ስራዉን ለመስራት በሂደት ላይ ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ መጤና ወራሪ አረሞች ስርጭትና መከላከል ላይ 60,000 ሄ/ር ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ 61,070 ሄ/ር ተተከናወነ ሲሆን ይህም የእቅዱን 100% ተከናውኗል፡፡

በበጀት ዓመቱ ዉስጥ በሁሉም ክልሎች የአረም ሳምንት እንዲታወጅ እቅድ ተይዘዉ የአረም መከላከል ሳምንት በሁሉም ክልሎች ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በ6 ዞኖች ላይ የመጤና ወራሪ አረሞችን በስነ-ህይወታዊ የመከላከል ስራ /የዛይጎግራማ/ ማራባትና የመስክ ሙከራ ስራን ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በ4 ዞኖች ላይ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ በ12,000 ሄ/ር የመጤና ወራሪ አረሞችን በስነ-ህይወታዊ የመከላከል ስራ የመስክ ሙከራ ስራን ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ታቅደዉ እስካሁን በ10,250 ሄ/ር ላይ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ የጥገኛ አረሞች (አሮባንኬ፣ አቀንጭራ የኑግ አንበሳ) የተቀናጀ የአረም መከላከያ ስልቶችን በመጠቀም 3 ታቅዶ 1 ሄ/ር መከላከል ላይ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል፡፡

**ረ) የዕፅዋት በሽታ መከላከልና መቆጣጠር**

በበጀት ዓመቱ ውስጥ በበቆሎ ገዳይ ቫይረስ በሽታ በ19,876 ሄ/ር ላይ ለማከናወን ታቅዶ በ19,209 ሄ/ር ላይ የተከናወነ ሲሆን በመቶኛም 97% ነው፡፡ በስንዴ ዋግ በሽታ በ56,813 ሄ/ር ላይ ለማከናወን ታቅዶ በ40,441 ሄ/ር ላይ የተከናወነ ሲሆን በመቶኛም 71% ሆኗል፡፡ በአገዳና በብርዕ ሰብሎች አረማሞ በ29,814 ሄ/ር፣ በ4,969 ሄ/ር ላይ በተዘራ የቢራ ገብስ በሽታዎች፣ በባቄላ ጋልና ቸኮሌት ስፖት በ3,907 ሄ/ር በቲማቲምና ድንች ብላይት በ4,251 ሄ/ርና በእንሰት፣ በዝንጅብልና በበርበሬ በሽታዎች በ4,938 ሄ/ር ላይ ለማከናወን ታቅዶ እንደ ቅደም ተከተላቸው በ41,240 ሄ/ር፣በ5,517 ሄ/ር፣ 8,000

ሄ/ር ፣በ5,476 ሄ/ር እና በ7,277 ሄ/ር ላይ የተከናወነ ሲሆን በሁሉም ሰብሎች ክንውናቸው በመቶኛም 100+% ነው።

በኦሮሚያ ክልል በ23 ዞኖች በ138 ወረዳዎች በመኸር፣ በበጋ መስኖና በበልግ ከሚለማው 891,409 ሄ/ር የስንዴ ማሳ ላይ የስንዴ ዋግ በ891,409 ሄ/ር ላይ አሰሳ ተካሂዶ በ110,149 ሄ/ር ላይ የስንዴ ዋግ ተከስቶ በ103,650 ሄ/ር ማሳ ላይ 66,368 ሊትር የተለያዩ አይነት ፀረ-ዋግ በመጠቀም የመከላከል ስራ ተሰርቷል። በአማራ ክልል በመኸርና በበጋ መስኖ ስንዴ በ16 ዞኖች በ26 ወረዳዎች ከለማው 456,789 ሄ/ር የስንዴ ማሳ በዚሁ ሄ/ር ላይ የአሰሳ ሥራ ተከናውኖ በ13,583 ሄ/ር ላይ የስንዴ ዋግ ተከስቶ በ10,940 ሄ/ር ማሳ ላይ የመከላከል ሥራ ተከናውኗል። ለመከላከሉም ሥራ 9,759 ሊትር የተለያዩ አይነት ፀረ-ዋግ ኬሚካል ጥቅም ላይ ውሏል።

በደ/ብ/ብ/ህ/ክ በመኸርና በበጋ መስኖ ስንዴ በ7 ዞኖች በ34 ወረዳዎች ላይ በ253,351 ሄ/ር ከተዘራው የስንዴ ማሳ ውስጥ በ252,710 ሄ/ር ላይ አሰሳ ተካሂዶ በ3,800 ሄ/ር መሬት ላይ የስንዴ ዋግ የተከሰተ ሲሆን በ3,034 ሄ/ር ማሳ ላይ የመከላከል ስራ የተከናወነ ሲሆን ለመከላከሉም ሥራ 1,020 ሊትር የተለያየ ዓይነት ፀረ-ዋግ ኬሚካል ጥቅም ላይ ውሏል። በደ/ምዕ/ክ በመኸርና በበጋ መስኖ ስንዴ በ4 ዞኖች በ4 ወረዳዎች ላይ በ3,439 ሄ/ር ከተዘራው የስንዴ ማሳ ውስጥ በ2,484 ሄ/ር ላይ አሰሳ ተካሂዶ በ894 ሄ/ር መሬት ላይ የስንዴ ዋግ የተከሰተ ሲሆን በ728 ሄ/ር ማሳ ላይ የመከላከል ሥራ የተከናወነ ሲሆን ለመከላከሉም ሥራ 366 ሊትር የተለያየ ዓይነት ፀረ-ዋግ ኬሚካል ጥቅም ላይ ውሏል።

በሲዳማ ክልል በመኸር ወቅት በለማ ስንዴ በ1 ዞን በ3 ወረዳዎች ላይ በ9,358 ሄ/ር ከተዘራው የስንዴ ማሳ ውስጥ በ9,358 ሄ/ር ላይ አሰሳ ተካሂዶ በ990 ሄ/ር መሬት ላይ የስንዴ ዋግ የተከሰተ ሲሆን በ120 ሄ/ር ማሳ ላይ የመከላከል ሥራ የተከናወነ ሲሆን ለመከላከሉም ሥራ 60 ሊትር የተለያየ ዓይነት ፀረ-ዋግ ኬሚካል ጥቅም ላይ ውሏል።

**ሸ) በነፍሳት ተባዮች መከላከልና መቆጣጠር**

በበጀት ዓመቱ በ4,632 ሄ/ር ላይ የቲማቲም ቅጠል ሰርሳሪ አሰሳ ማካሄድ፣ በሥርጭት ወረዳዎች የተቀናጀ መከላከል ዘዴ ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በ2,339 ሄ/ር ላይ የድጋፍና ክትትል ሥራ የተከናወነ ሲሆን በመቶኛም 51% ሆኗል። በነጭ የማንጎ ስኬል ነፍሳት ተባይ ስርጭት የዳሰሳ ጥናት ማካሄድና የተቀመጡ የመከላከያ አማራጮችን በ8,938 ሄ/ር የማንጎ ተክል ላይ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍል በማስተዋወቅ አስተባብሮ ለመፈፀም ታቅዶ በ7,751 ሄ/ር በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ በሀረሪ ክልሎች ላይ የተከናወነ ሲሆን በመቶኛም 87% ሆኗል። በ6,625 ሄ/ር የተለያዩ ዕፅዋቶች (የብርእ፣ የፍራፍሬ እንዲሁም የአትክልት) አገዳ ቆርቁር፣ ክሽክሽና ትሪፐስ ተባዮች ላይ የመከላከል የምክር አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ በ27,973 ሄ/ር ላይ የተከናወነ ሲሆን በመቶኛም 100+% ሆኗል።

በ5,300 ሄ/ር ላይ የሚሊበግ ሥርጭትና ሁኔታ አሰሳ በማካሄድ ስለ ቁጥጥርና መከላከል ሙያ ምክርና ድጋፍ ለመስጠት ታቅዶ በ3,240 ሄ/ር ላይ የተከናወነ ሲሆን በመቶኛም 61% ሆኗል። በአጠቃላይ በበጀት ኣመቱ በዕፅዋት በሽታዎች አሰሳና መከላከል በበልግ፣ በመስኖና መኸር ወቅት በ134,505 ሄ/ር ላይ ለማከናወን ታቅዶ በ134,534 ሄ/ር ላይ የተከናወነ ሲሆን በመቶኛም 100% ሆኗል። በተጨማሪም በነፍሳት ተባዮች በ25,495 ሄ/ር ላይ አሰሳና ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በ41,303 ሄ/ር ላይ የተከናወነ ሲሆን በመቶኛም 100% ሆኗል።

### 3.7 የከተማ የሰብልና ሆርቲከልቸር ልማት

የጓሮ አትክልት፡- አትክልትና ፍራፍሬን 80.29 ሺህ ቶን ለማምረት ታቅዶ 89.2 ሺህ ቶን በማከናወን 100+ በመቶ ተፈጽሟል፣ ሰብል ልማት፡- በተለያዩ ሰብሎች 55.46 ሺህ ቶን ለማምረት ታቅዶ 56.2 ሺህ ቶን በማምረት 100% ተከናውኗል።

## 4. ገበያ ተኮር የእንስሳትና ዓሳ ምርትና ምርታማነት ማሳደግ

### 4.1 የአነስተኛ ይዞታ የእንስሳትና ዓሳ ምርት

በ2015 በጀት ዓመት የወተት ምርት (ከላም፣ ከግመል እና ከፍየል) 7.5 ቢሊየን ሊትር ለማምረት እቅድ ተይዞ እየተሰራ ሲሆን በአመቱ ከታቀደው 7.55 ቢሊየን ሊ/ር ለማምረት 8.69 ቢሊየን (100+ በመቶኛ) ሊ/ር ማምረት ተችሏል። የሥጋ ምርት መጠን በበጀት አመቱ (ከዳልጋ ከብት፣ በግ፣ ፍየል፣ ግመል) በድምሩ 505 ሺህ ቶን ለማምረት ታቅዶ 491.35 ሺህ/ቶን (97.3%) የሥጋ ምርት ተገኝቷል። በበጀት አመቱ 19.4 ሚ/ን የቆዳና ሌጦ ምርት ለማምረት ታቅዶ 19 ሚ/ን (97%) ማምረት ተችሏል። የዶሮ ሥጋና እንቁላል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በተያዘ እቅድ 96 ሺህ ቶን የዶሮ ሥጋ ለማምረት ታቅዶ 96 ሺህ ቶን (100+%) ተመርቷል። እንቁላል 3.64 ቢሊየን ታቅዶ 3.918 ቢሊየን እንቁላል (100+%) ለማምረት ተችሏል። ከሀይቆች፣ ከግድቦችና ትንንሽ ውሀ አካላት፣ ከወንዞች እና ከዓሣ ግብርና (ኩሬ) 106.2 ሺህ ቶን የዓሣ ምርት ለማምረት ታቅዶ 101.4 ሺህ ቶን (96%) ምርት ተገኝቷል። የማር ምርት 155.58 ሺህ ቶን ታቅዶ 194.27 ሺህ ቶን (100+%) ተመርቷል።

### 4.2 መኖ ልማት

የእንስሳት ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ዋናዉና ወሳኙ የመኖ አቅርቦቱን በመጠንና በጥራት ማሳደግ ነዉ። ይህን ለማሳካት በሁሉም ስነ-ምህዳር መስኖ በመጠቀም 23,055 ሄ/ር መሬት ላይ የተሻሻለ መኖ ለማልማት ታቅዶ 34,658 (100+%) ሄ/ር ማልማት ተችሏል። ከተለያዩ የመኖ ምንጮች 164 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ማምረት ታቅዶ 165 ሚ/ን ቶን (100+%) ድርቆ መኖ ማምረት ተችሏል። አፈፃፀሙ በዝርዝር የመኖ ምንጮች ሲታይ ከተፈጥሮ ግጦሽ 41 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ 40 ሚ/ን ቶን (98.1%) ማምረት ተችሏል። ከወል ግጦሽ መሬት 19.4 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት

ታቅዶ 23.48 (100⁺%) ሚ/ን ቶን ተመርቷል፡፡ ከግል የአርሶ አደር ግጦሽ መሬት 4.7 ሺህ ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ 7.31 ሺህ ቶን (100⁺%) ማምረት ተችሏል፡፡ ከተሻሻሉ የመኖ ምንጮች 11.66 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ 17.06 ሚ/ን ቶን (100⁺%) መፈጸም ተችሏል፡፡ ከሰብል ተረፈ ምርት 70 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ 64 ሚ/ን ቶን (92.3%) መፈጸም ተችሏል፡፡ ከኢንዱስትሪ (ስኳርና ሌሎች) ተረፈ-ምርቶች 8.14 ሚ/ን ቶን ድርቆ መኖ ለማምረት ታቅዶ 12.9 ሚ/ን ቶን (100⁺%) ማምረት ተችሏል፡፡

## 4.3 የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል

የሌማት ትሩፋቱን የወተት ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በሰው ሠራሽ ማዳቀል ዘዴ ዝርያ ማሻሻል ቀዳሚውን ሥፍራ የሚይዝ የአባለዘር ምርትን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ 1,500,000 ዶዝ አባለዘር ለማምረት ታቅዶ 1,338,340 ዶዝ (89.2%) አባለዘር እንዲመረት ተደርጓል፡፡ ከዚህ ምርት ውስጥ 1,150,528 ዶዝ በኢንስቲትዩቱ የተመረተ ሲሆን ቀሪዉ 187,812 ዶዝ በሦስቱ የክልሎች አባለዘር ማምረቻ ማዕከላት ማለትም በነቀምቴ 42,422 ዶዝ፣ በባህር ዳር 117,838 ዶዝ እና በሀዋሳ 27,552 ዶዝ ተመርቷል፡፡ በዓመቱ መገባደጃ ላይ የተካሄደው የግብርና ኤግዚቢሽን ምክንያት ለአንድ ወር ያህል ምርት ሂደቱ ባይቆም ኖሮ ከዚህ የበለጠ አፈጻጸም ሊኖር እንደሚችል ተገምግሟል፡፡ የአባለዘር ሥርጭትን በተመለከተ በክልሎችና በኢንስቲትዩቱ 1,300,000 ዶዝ አባለዘር ለማሰራጨት ታቅዶ 1,149,454 ዶዝ አባለዘር (የዕቅዱን 88.4%) ተከናውኗል፡፡ ይህ ስርጭት በክልሎች እና በኢንስቲትዩቱ የተሠራጨዉን ያካተተ ሲሆን 978,486 ዶዝ በኢንስቲትዩቱ ሲሠራጭ ቀሪዉ 170,968 ዶዝ በሦስቱ የክልሎች አባለዘር ማምረቻ ማዕከላት የተሠራጨ ነው፡፡

ለሠው ሠራሽ ማዳቀል አገልግሎት የሚውል አባለዘር በሕይወት እንዲቆይ የሚረዳ ፈሳሽ ናይትሮጂን ምርትን በተመለከተ በክልሎችና በኢንስቲትዩቱ 385,127 ሊትር ፈሳሽ ናይትሮጂን ለማምረት ታቅዶ 374,735 ሊትር (97%) እንዲመረት ተደርጓል፡፡ ከዚህ ውስጥ በኢንስቲትዩቱ 68,307 ሊትር የተመረተ ሲሆን ቀሪው 306,428 ሊትር በክልሎች ፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማዕከላት የተመረተ ነዉ፡፡ በሌላ በኩል ፈሳሽ ናይትሮጂን ሥርጭትን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ 365,137 ሊትር ፈሳሽ ናይትሮጂን ለማሠራጨት ታቅዶ 373,498 ሊትር (102%) ፈሳሽ ናይትሮጂን እንዲሠራጭ ተደርጓል፡፡ ከዚህ ውስጥ 306,293 ሊትር በክልሎች የተሠራጨ ሲሆን ቀሪዉ 67,205 ሊትር ደግሞ በኢንስቲትዩቱ የተሠራጨ ነው፡፡ ቀደም ሲል ከውጭ አገር ይገቡ የነበሩ አባለዘር አምራች ኮርማዎችን የዝርያ እና የጤና መስፈርቱን በሚያሟሉ ኮርማዎችን በመረጃ ምዝገባ ቋት ከሚገኙና ፋርሞች በመምረጥ ውስጥ ወደማዕከል ለማስገባት 40 ታዳጊ ኮርማዎችን ለመምረጥ ታቅዶ 40 ኮርማዎች (100%) ግዥ በማካሄድ ከአገር ውስጥ እርባታዎች ማስገባት ተችሏል፡፡

የዝርያ ማሻሻል ሥራን የሚያሳልጡ የአዳቃይ ቴክኒሺያኖች አቅም ግንባታን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ 100 ነባር አዳቃይ ቴክኒሽያኖች የማነቃቂያ ሥልጠና ለመስጠት ታቅዶ 510 አዳቃይ ቴክኒሽያኖች ከሁሉም ክልሎች ከተመረጡ የወተት መንደሮች ለመጡ ከእንስሳትና ዓሳ ሀብት ሴክተር በተገኘ የበጀት ድጋፍ ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ ለወተት መንደሮች አሁን ያሉት አዳቃይ ቴክኒሽያኖች በቂ ባለመሆናቸው በበጀት ዓመቱ 120 አዳዲስ አዳቃይ ቴክኒሽያኖችን ለማሰልጠን ታቅዶ 108 አዳዲስ አዳቃይ ቴክኒሽያኖች (90%) ሥልጠና ከደቡብ፣ ከሲዳማ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ከሶማሌ እና ከድሬዳዋ በማሰልጠን ለወተት መንደሮች ማሠማራት ተችሏል፡፡ በዚህ በጀት አመት 122.66 ሚሊየን ሊትር የተቀነባበረ የወተት ምርት ለሀገር ውስጥ ገበያ ለማቅረብ ታቅዶ 112.64 ሚሊዮን ሊትር በማቅረብ የእቅዱን 91.8 በመቶ ማከናወን ተችሏል፡፡

ለእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች በተሰጣቸው የማማከርና ድጋፍ አገልግሎት ጥራቱን የጠበቀ መኖ ለማቀነበባር ከታቀደው 135,560 ቶን መኖ 123,216.18 ቶን መኖ በማቀናበር የእቅዱን 90.8 በመቶ ለማከናወን ተችሏል፡፡ ከሥጋና ወተት ውጤቶች የወጪ ንግድ አፈጻጸምን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ 28,106 ቶን የተቀነባበረ የእንስሳት ምርት በመላክ -137.83 ሚሊየን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ የሰኔ ወር ኤክስፖርት አፈጻጸም ከጉምሩክ ኮሚሽን ያልቀረበ በመሆኑ በ11 ወር ውስጥ 19,983.4 ቶን ምርት ወደ ውጭ በመላክ 86 ሚሊየን ዶላር ማግኘት የተቻለ ሲሆን ይህ ከአምና ተመሳሳይ ጊዜ አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር ቅናሽ አሳይቷል፡፡ ለአፈጻጸሙ ማነስ ተጠቃሽ ከሆኑ ጉዳዮች ውስጥ ለአገራችን ስጋ ምርት ከፍተኛ የገበያ መዳረሻ ድርሻ የነበረው የሳውዲ ገበያ በተለያዩ ምክንያቶች መቋረጡ፣ የሌሎችን ቄራዎች ተከራይቶ ስጋን የሚልኩ ድርጅቶች እየተበራከቱ በመምጣታቸው የሀገር ውስጥና የዉጭ ገበያ እንዲዛባ መደረጉ፣ የዓሳ ምርት አሁን ባለው ጸጥታ ችግር ምክንያት ብቸኛ ገበያ መዳረሻ ወደ ሆነው ሱዳን መላክ አለመቻሉና የዳልጋ ከብት ስጋ በሀገር ውስጥ ዋጋ ንረት ምክንያት በበጀት ዓመቱ ምንም ዓይነት ምርት ኤክስፖርት አለመደረጉ ዋና ዋና ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

### 4.4የእንስሳት ጤና አገልግሎት ማሻሻል

በ2015 በጀት አመት በስጋት ላይ የተመሰረተ የክትባት አገልግሎት ሽፋን ለማሳደግ የተለያዩ ዋና ዋና ተግባራት በዕቅድ ተይዞ ሲተገበር ቆይቷል፡፡ ከእነዚህም ዋና ተግባር ውስጥ የድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታዎችን ክትባት ማሰራጨት ሲሆን 160 ሚ/ን ዶዝ ለማሰራጨት ታቅዶ 120.35 ሚ/ን ዶዝ (75%) ለማሰራጨት ተችሏል፡፡ ድንበር ዘለል ላልሆኑ በሽታዎች 50 ሚ/ን እንስሳት ለመከተብ ታቅዶ 45.3 ሚ/ን እንስሳት (90.6%) መከተብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 201 ሚ/ን እንስሳትን የድንበር ዘለል በሽታዎች ክትባት ለመከተብ ታቅዶ 151 ሚ/ን እንስሳት (75%) ለመከተብ ተችሏል፡፡ በስጋት ላይ የተመሰረተ የክትባት አገልግሎት ሽፋን ለማሳደግ 92 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 92 በመቶ ማሳካት

ተችሏል፡፡ አጠቃላይ የክትባት አገልግሎት ሽፋን (ድንበር ዘለላ እና ድንበር ዘለል ያልሆነ) ደግሞ 100% በመቶ ለማድረስ ታቅዶ ሙሉ ለሙሉ ማከናወን ተችሏል፡፡

የበጎችና ፍየሎች ደስታ መሰል በሽታን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚካሄደው አገር አቀፍ ትግበራ 15 ሚ/ን በግና ፍየል ለመከተብ ታቅዶ 15.33 ሚ/ን በጎችና ፍየሎችን (100+%) መክተብ ተችሏል፣ በተመረጡ አካባቢዎች 100,000 ውሾችን ለመክተብ 100,000 ዶዝ የዉሾች እብደት ክትባት በማሰራጨት ታቅዶ ሁሉም ክልሎች የክትባት ዘመቻ እንዲያካሂዱ በመደገፍ በራሳቸዉ ግዥና በግል ህክምና አገልግሎት ጨምሮ ከ210,650 በላይ ውሾችን መከተብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በተለያየ ክልል ለባለሙያዎች እና ለህብረተሰቡም ከፍተኛ የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ተሰርቷል፡፡ የተሰራጨዉም የውሻ እብደት በሽታ መከላከያ ክትባት ከብሄራዊ የእንስሳት ጤና ምርምር ኢንስቲትዩት ግዥ በመፈጸም ተሠራጭቷል፡፡

የቆላ ዝንብን የመቆጣጠር ዘዴ በላብራቶሪ የቆላ ዝንብ በማርባትና የመከኑ ወንድ ዝንቦችን የቆላ ዝንቦች በሚኖሩበት ጫካ አካባቢ መልቀቅ ሲሆን በዚህ መሠረትም በዓመቱ ውስጥ በላበራቶሪ የሚረቡ ሴት የቆላ ዝንቦች የግሎሲና ፉስኪፐስ ዝርያዎችን በቁጥር 104,356 ለማድረስ ታቅዶ 58,532 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም 56.1% በመቶ ነው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በተመሳሳይ ሁኔታ የግሎሲና ፓሊዲፐስ ዝሪያ ቁጥርን 338,900 ለማድረስ ታቅዶ 248,899 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙን 73.4% ማድረስ ተችሏል፡፡ መክነው መስክ ላይ የተለቀቁ የቆላ ዝንብ ብዛት የግሎሲና ፉስኪፐስ 186,472 ታቅዶ 147,123 በመከናወኑ አፈጻጸሙም 78.9% የደረሰ ሲሆን እንዲሁም በተመሳሳይ የግሎሲና ፓሊዲፐስ በአመቱ ውስጥ 370,000 ታቅዶ 533,193 የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙንም 144.1% ማድረስ ተችሏል፡ ፡ ሌሎች የቆላ ዝንቦችን የመቆጣጠሪያ መንገዶች ደግሞ የፀረ-ቆላ ዝንብ ኬሚካል በ3,620,000 እንስሳት ጀርባ ላይ ለመቀባት ዕቅድ ተይዞ 1,590,605 እንስሳት መቀባት በመቻሉ አፈጻጸሙ 43.9% ሲሆን ችሏል፡፡ እንዲሁም ለ21,360 እንስሳት የህክምና አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ22,143 እንስሳት የህክምና አገልግሎት መስጠት በመቻሉ ከታቀደው ዕቅድ አንፃር አፈጻጸሙን 103.7% ለማድረስ ተችሏል፡፡

ለኤክስፖርት የቀረቡ ለ14,000 የዳልጋ ከብቶች የኢንስፔክሽን እና ሰርተፍኬሽን ለማድረግ ታቅዶ ለ13,618 (97%) የዳልጋ ከብቶች ምርመራ ተደርጎላቸው ወደ ተቀባይ ሀገራት እንዲላኩ ተደርጓል፡፡ ለውጪ ገበያ ለሚቀርቡ 58,000 በግና ፍየል ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ ለ52,488 (90%) በግና ፍየል ጤና ምርመራ እና የኳራንቲን ጊዜያቸውን ጨርሰው እንዲላኩ ተደርጓል፡፡ ለ13,000 ግመሎች የኢንስፔክሽን እና ሰርተፍኬሽን እና የክትባት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ2,721 (21%) ግመሎች የክትባት አገልግሎት አግኝተውና የተቀባይ ሀገራትን መስፈርት አሟልተው እንዲወጡ ተደርጓል፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት በታቀደዉ መጠን እንስሳት ባለመቅረቡ ነዉ፡፡ የቁም እንስሳት ቅድመ

ዕርድ ምርመራ ለማድረግ ለ1,950,750 ታቅዶ በድምሩ ለ1,341,500 የቁም እንስሳት (68.7%) ምርመራው ተከናውኗል። ለ1,950,000 የታረዱ እንስሳት ድህረ እርድ ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ በ1,284,750 የታረዱ እንስሳት (65.6%) ላይ ምርመራው ተከናውኗል።

የቄራዎችን ሀይጅንና ሳኒቴሽን እንዲጠበቅ ለመቆጣጠር የኢንስፔክሽን አገልግሎት ለ21,000 ቶን የበግ፣ የፍየልና፣ የዳልጋ ከብት ስጋ ምርት ለመስጠት ታቅዶ በድምሩ 12,155.51 (58%) ስጋ እና ተረፈ ስጋ ደህንነቱ ተረጋግጦ እንዲላክ ተደርጓል። ለ6,750 የሥጋ ምርት የደህንነት እና ጤንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በመስጠት ደህንነቱና ጥራቱ የተረጋገጠ የስጋ ምርት ወደ ውጪ ለመላክ ታቅዶ 6,006 (90%) ሰርተፊኬት ተሰጥቷል።

## 4.5 የእንስሳትና ዓሳ ኤክስቴንሽን

የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎች ቁጥር 5,004,000 ለማድረስ ታቅዶ 4,933,900 (98.6%) ማድረስ ተችሏል። ከዚህ ውስጥ 3,387,000 አርሶ አደሮች፣ 1,119,000 አርብቶ አደሮች እና 330,800 ከፊል አርብቶ አደሮች ናቸው። በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ኤክስቴንሽን የሙሉ ፓኬጅ ተጠቃሚዎች ቁጥርን 2,200,000 ለማድረስ የታቀደ ሲሆን 1,886,000 (85.8%) ማድረስ ተችሏል። በዶሮ፣ በስጋ፣ ቆዳ/ሌጦ፣ በወተት፣ በዓሳ፣ በመኖና በንብና ሀር ሀብት ልማት፣ በሥርዓተ-ምግብ ተኮር ግብርና፣ በሥርዓተ ጾታ አዳዲስና የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን የሚቀበሉና ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚተገብሩ፣ እንዲሁም ለሌሎች አርሶና አርብቶ አደሮች አርአያ በመሆን ሥራቸውን በመከታተልና በመደገፍ የተፈጠሩ ሞዴል አርሶ አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሮች ቁጥር 1,500,000 ለማድረስ ታቅዶ 1,307,000 (87.2%) ማድረስ ተችሏል።

## 4.6 የከተማ የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት

የወተት ምርት ፡- 230 ሚ/ን ሊትር ለማምረት ታቅዶ 332 ሚ/ን ሊትር ወተት በማምረት የዕቅዱን 100+ በመቶ ተከናውኗል፤ የስጋ ምርት፡- ከዳልጋ ከብት፤ ከበግ፣ ከፍየልና ከዶሮ 94 ሺህ ቶን ሥጋ ለማምረት ታቅዶ 95.1 ሺህ ቶን የተመረተ ሲሆን አፈፃፀሙ 100+ በመቶ ተከናውኗል፤ የእንቁላል ምርት፡- ከተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎች 768 ሚ/ን በቁጥር ለማምረት ታቅዶ 801 ሚ/ን በቁጥር እንቁላል የተመረተ ሲሆን 100+ በመቶ ተፈጽሟል፤ የዓሳ ምርት፡- 10,150 ኪ/ግ ለማምረት ታቅዶ 11,307 ኪ/ግ አሳ የተመረተ ሲሆን ከዕቅዱ 100+ በመቶ ተከናውኗል፣ የማር ምርት፡- 500 ቶን ማር ለማምረት ታቅዶ 483 ቶን የተከናወነ ሲሆን 96.6 ከመቶ ተፈጽሟል።

## 5. ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም

### 5.1 የተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም

***የተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አፈፃፀም፡-*** *የተፈጥሮ ሀብት ልማት አጠባበቅና አጠቃቀም ተግባራት አፈፃፀምን በተመለከተ አረንጓዴ አሻራና የተፋሰስ ልማትን መሰረት በማድረግ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን የተፈጥሮ ሃብት መመናመንና የአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተፅዕኖን በመከላከል ዘላቂነት ያለው የአረንጓዴ ኢኮኖሚ የመገንባት ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡*

***የአገራችንን የአረንጓዴ*** *ሽፋን ለማሳደግና የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን ለመቋቋም ከፍተኛ አስተዋጽ ያበረክታል ተብሎ እየተተገበረ የሚገኘው የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር በመጀመሪያው ምዕራፍ አራት ዓመታት በአጠቃላይ 20 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ ወደ 20 ሚሊዮን የሚጠጋ የሰው ኃይል እንዲሳተፍ በማድረግ 25 ቢሊዮን ችግኞች የተተከሉ መሆናቸውን በጀት ዓመት በተደረገው ክትትልና ግምገማ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በያዚነው በጀት ዓመት 6 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ 7.2 ቢሊዮን ችግኞች የተተከሉ ሲሆን አፈፃፀሙም 120% ነው፡፡ ከዚህም ውስጥ 3.02 ቢሊዮን የደን ዛፍ፣ 3.3 ቢሊዮን የጥምር ደን-እርሻ፣ 371.9 ሚሊዮን የፍራፍሬ እና 62.9 ሚሊዮን ደግሞ የከተማ ውስጥ ተከላዎች መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ከሀገር ወጭ የጎረቤት አገራት ችግኝ አቅርቦትን በተመለከተ በአረንጓዴ አሻራ ሥራዎች ተሳታፊ በመሆን በጋራ የበረሃማነት መስፋፋትን ለመግታት እየተደረገ ባለው ጥረት ለጂቡቲ 62,000 የፍራፍሬና የዛፍ ችግኞች ተልከዋል፡፡*

***የተተከሉ ችግኞች የአረምና ኩትኳቶ*** *ተግባራት አፈፃፀምን በተመለከተ በተለያዩ ክልሎች የችግኞች እንክብካቤ ከፍተኛ ጥረቶች ተደርጓል፤ እየተደረገም ይገኛል፡፡ በግብርና ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ ደን ልማት ጥምረት በአራት ክልሎች ባደረጉት የክትትል ሥራዎች ግኝት መሠረት 1.8 ሚሊዮን ሄ/ር በሚሸፍን መሬት ላይ የተተከሉ 7.1 ቢሊዮን ችግኞች እንክብካቤ የተደረገላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡*

***የፅድቀት መጠን*** *ምዘና መረጃን በተመለከተ ከክልሎች የተሰባሰበ የጽድቀት ምዘና እና ከፌደራል በተውጣጡ ከፍተኛ ባለሙያዎች ቡድን በተወሰዱ 12 ናሙናዎች መሠረት የአገር-አቀፍ ደረጃ ባለፈው ዓመት የተተከሉ ችግኞች የጽድቀት መጠን በአማካይ 84.83 በመቶ መሆኑን ለማረጋገጥ የተቻለ ሲሆን በየክልሉ ያለው አማካይ የጽድቀት ምጣኔ ሲታይ በኦሮሚያ 88.80%፤ በአማራ 87.30%፤ በደቡብ 80.77% እና በሲዳማ 71% መሆኑን በተደረገው ክትትል ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡*

***የችግኝ ጣቢያዎች*** *የዛፍ ዘር አቅርቦትን በተመለከተ በስድስት ክልሎች (አማራ፣ኦሮሚያ፣ሲዳማ፣ደቡብ፣ ሐረሪ እና ጋምቤላ) የችግኝ ዝግጅት ግብዓት አቅርቦት መረጃ መሠረት 5007.96 ኩ/ል ዘር ለችግኝ ጣቢያዎች የቀረበ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ 1,643 ኩ/ል የችግኝ ዘር ለመሰብሰብና ለማሰራጨት ታቅዶ 5,007.96 የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም ከ100% በላይ መሆኑን*

ያመላክታል። በተመሳሳይ መልኩ በስድስቱ ክልሎች (አማራ, ኦሮሚያ፣ሲዳማ፣ደብ.ብ.ሕ፣ሐረሪ እና ጋምቤላ 3,065 ኩ/ል የፕላስቲክ ቲዩብ ለማቅረብ ታቅዶ 3,065 ኩ/ል (100%) ለማከናወን ተችሏል።

**ችግኞች ዝግጅትን** በተመለከተ ከኦሮሚያ፣ከሲዳማ፣ከደቡብ እና ከሀረሪ ክልሎች ወቅታዊ የችግኝ ዝግጅት አፈጻጸም መረጃን ለመሰብሰብ የተሞከረ ሲሆን ከአማራና ጋምቤላ ክልሎች በስተቀር 221.35 ሚሊዮን የደን፣ መኖ፣ ፍራፍሬ፣ የቀርከሃ፣ ዘርፈ-ብዙ ጥቅም ሰጪ ዝርያዎችና ሌሎች ዝርያዎችን ችግኝ ዝግጅት እየተከናወነ መሆኑን ለመለየት ተችሏል። ነባርና አዳዲስ ችግኝ ጣቢያዎችን ማቋቋምና ወደ ሥራ ማስገባት ተግባራትን በተመለከተ በተደረገው ክትትልና ድጋፍ መረጃ መሠረት 130,935 በነባርና አዳዲስ ችግኝ ጣቢያዎችን ወደ ስራ ለማስገባት ታቅዶ 130,935 (100%) ችግኝ ጣቢያዎች ወደ ሥራ የገባ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል።

**የተፋሰስ ልማት ሥራዎችን** በተመለከተ የስነ-አካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በአግባቡ መከናወናቸውን እና ከወርሃ ጥር ጀምሮ ደግሞ የስነ-አካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች በስፋት እንደተከናወነ ከክልሎች የደረሱን መረጃዎች ያሳያሉ። የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት አብዛኞቹ ክልሎች በቂ የሆነ የዝግጅት ምዕራፍ ሥራዎችን በማከናወን የበጋ ወቅት የተፋሰስ ልማት ሥራዎችን በተጠናከረ ሁኔታ ማከናወን ችለዋል። በዚህ መሠረት ለዚህ የተፋሰስ ልማት ንቅናቄ 13,790,253 ወንዶች እና 9,487,460 ሴቶች በድምሩ 23,277,713 የሰው ኃይል ልየታ ተካሂዶ በ726,174 የልማት ቡድኖች በማደራጀት በተፋሰስ ልማት ሥራ ላይ ማሰማራት ተችሏል። 20,165 የማህበረሰብ ተፋሰሶችን በመለየትና የተፋሰስ ዕቅድ በማዘጋጀት፣ 16,487,120 ልዩ ልዩ የልማት መሠሪያዎችን ለሥራ በማዘጋጀት እንደዚሁም ለ682,608 አርሶ/አርብቶ አደሮች ሥልጠና በመስጠት ወደሥራ ተገብቷል። ዋና ዋና የተፋሰስ ስራዎችን በሚመለከት 500,000 ሄ/ር የማህበረሰብ ተፋሰስ በስነ አካላዊ አፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ ለመሸፈን ታቅዶ 1,804,000 ሄ/ር (100+%) ፣ 500,000 ሄ/ር የሚሸፍን ጥገና፣ እድሳትና ደረጃ ማሳደግ ሥራ ለመሥራት ታቅዶ 928,100 ሄ/ር መሬት (185%) ማከናወን ተችሏል፣ 200,000 ሄ/ር የተጎዳ መሬት ከልሎ ከንክኪ ነጻ በማድረግ ለመጠበቅ ታቅዶ 688,159.3 ሄ/ር መሬት (344%) መከለልና መጠበቅ ተችሏል።

**በተፋሰስ ልማት** ላይ የሚያተኩረው የአየር ለውጥ ተፅዕኖ የመሬት አስተዳደር ፕሮግራም (Climate Action through Landscape Management Program for Result-CALM PforR) ፕሮግራም ካለፉት ሁለት ዓመታት ጀምሮ በ9 ክልሎች እና በድሬዳዋ አስተዳደር ውስጥ የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብት የልማት ተግባራትን እየደገፈ እንደሆነ ይታወቃል። የተለያዩ ሥልጠናዎችና የምክክር መድረኮችን ማካሄድ፣ የDLI #2 እና DLI #3 ስራ በቂ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ማረጋገጫ መስጠት፤ የNDVI ሥራ፣ የCALM PforR የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት አያያዝ ቅኝት እና የሥርዓተ-ጾታና ማህበራዊ ልማት አካታችነት ክትትልና ድጋፍ ሥራዎች በዚህ የትግበራ ወቅት የተከናወኑ የፕሮግራሙ ዋና ዋና ተግባራት ናቸው። በዚህም መሠረት ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ 694 የማህበረሰብ

ተፋሰሶች የሁለተኛውን ገንዘብ አስለቃቂ አመላካች (DLI #2) ማረጋገጫ ለማሰጠት የሚያስፈልገውን መስፈርት ያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይም 582,418 ሄ/ር መሬት የሚሸፍን የዘላቂ መሬት አያያዝ ተግባራት የተከናወኑባቸው 2,800 የማህበረሰብ ተፋሰሶች ሦስተኛዉን ገንዘብ አስለቃቂ አመላካች (DLI #3) ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መስፈርቶችን አሟልተው የማረጋገጥ ሥራውን ለሚያከናወነው ተቋም ለማስረከብ ዝግጁ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

**በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም** የማህበረሰብ ልማት ስራዎችን በተመለከተ በ5ኛው የፕሮግራሙ ምዕራፍ የተቀመጠውን የግብ ውጤትን መሰረት በማድረግ ዓመታዊ ዕቅድን በማዘጋጀት ወደ ትግበራ የተገባ ሲሆን በበጀት ዓመቱ በአቅም ግንባታና ዓውደ ጥናት፣ ሥርዓተ-ግንባታና ስትራቴጂ (System Building & Strategy) በክትትል፤ ድጋፍና ግምገማ ተግባራት ለማከናወን ተችሏል፡፡

በአርብቶ አደር አካባቢዎች በተለይም በአፋር እና በሶማሌ ክልሎች ያለውን በልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የሚተገበረውን የማህበረሰብ ልማት ሥራዎች አፈጻጸም ላይ የሚታየውን አንፃራዊ ውስንነቶችን ለማሻሻል የክልል ተንቀሳቃሽ የድጋፍ ቡድን አተገባበር ለማጠናከር እንዲቻል ከአለም ምግብ ፕሮግራም የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት የሚያስችል የፕሮጀክት ምክረ-ሀሳብ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ የስራ ተመን ክለሳ ለማካሄድ የሚያስችል ቴክኖሎጂዎችን ለመለየት የመነሻ ፕሮፖዛል ተዘጋጅቶ ወደ ክልሎች የተላከ ሲሆን ለግብዓትነት ከክልሎች አስተያየት እየተሰበሰበ ይገኛል፡፡ የማህበረሰብ ስራዎች የመረጃ ቋት የመጨረሻ ፍተሻ በማድረግ ስራውን ከአማካሪ ድርጅቱ ለመረከብ የተቻለ ሲሆን በመረጃ ቋት የተሠሩ ስራዎች አገራዊ እንዲሆን ከማድረግ አንፃር ለተጨማሪ ስራ ይሁንታ በማግኘት ወደ ስራ ለመግባት ተችሏል፡፡

**የአቅም ግንባታ ሥራዎችን** በተመለከተ በፕሮግራሙ በተከሰተው የበጀት እጥረት ምክንያት የበጀት ዓመቱን ዕቅድ ለመከለስና የበጀት ክፍተቱን ለመሙላት ከምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ጋር የምክክር መድረክ በማዘጋጀት የፋይናንስ ክፍተት ለመሙላት በተለይ የካፒታል በጀት አለመኖርን ተከትሎ የክልሎች በጀት መጋራት በማዕቀፍ ተካቶ ዕቅዱን የመከለስ ሥራ ተሠርቷል፡፡ **ድርቅን የመቋቋም አቅም ግንባታ ፕሮጀክት** ስራዎችን በተመለከተ 890 ሄ/ር በፕሮሶፒስ የተወረረ መሬት ከፕሮሶፒስ ወረራ እንዲጸዳ በመደረጉ ከ200 ሄ/ር በላይ የሚሆን መሬት በተመረጡ የመኖ ዘሮች የተሸፈነ ሲሆን 46 ሄ/ር የተፈጥሮ ግጦሹ የተመናመነ መሬት ደግሞ በዘር እንዲሸፈን ተደርጓል፡፡ ከፕሮሶፒስ ነጻ የተደረገ መሬት በመኖ ዘር ለመሸፈን የሚደረገውን ጥረት የሚያግዙ 2 አነስተኛ የዘር ማበጠሪያና 2 የዘር መዝሪያ ማሽኖች ተገዝተው እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡

## 5.2. የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም

በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም የተገልጋዮችን ተሳትፎና እርካታን ለማሳደግ በገጠር መሬት ምዝገባና ሰርተፊኬት አሰጣጥ ላይ ትኩረት በመስጠት ሴቶች እና ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ልዩ ትኩረት በመስጠት በክልሎች እየተካሄደ ያለውን ስራ መደገፍ የገጠር መሬት ሰርተፊኬት አሰጣጥ፣ የገጠር መሬት አስተዳደር የመረጃ ስርዓት፣ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ዝግጅትና አተገባበር ላይ ያተኮሩ ሥራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለ 1.8 ሚሊዮን ማሳዎች ልኬትና ምዝገባ ለማከናወን በዕቅድ የተያዘ ሲሆን ለ2.6 (100⁺%) ሚሊዮን ይዞታዎች ልኬት ተከናውኗል፡፡ ክንውኑ ከዕቅድ በላይ የሆነበት ምክንያት በመጀመሪያ ሩብ ዓመት የተወሰኑ ስራዎች አስቀድመው በመሰራታቸው ነው፡፡ እንዲሁም የይዞታ ማረጋገጫ ሠርተፍኬት ለ2.1 ሚሊዮን ማሳዎች ለመስጠት ታቅዶ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለ2.44 ሚሊዮን ማሳዎች የመስጠት ስራ ተከናዉኗል፡፡ እንደዚሁም ለ600 ሺህ (420 ሺህ አባወራ እና 180 ሺህ እማወራ) ባለይዞታዎች የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋጫ ሰርቲፍኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ700 ሺህ (500 ሺህ አባወራ እና 200 ሺህ እማወራ) ባለይዞታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የተሰጣቸው ሲሆን አፈፃፀሙም ከመቶ በላይ ነው፡፡

በዚሁ በጀት ዓመት 79 ወረዳዎች የብሔራዊ የገጠር መሬት አስተዳደር የመረጃ ስርዓትን (NRLAIS) ለመዘርጋት ታቅዶ በ94 ወረዳዎች የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙም ከመቶ በላይ ነዉ፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ለስራዎቹ ከፍተኛ የሆነ ትኩረት በመስጠትና ተከታታይ የሆነ ክትትል በማድረግና ግብረመልስ በፍጥነት የመስጠት ስራ በመሰራቱ ነው፡፡ ይኼውም ከላይ የተጠቀሱ የማሳ ልኬትና ምዝገባ፤ ለማሳዎች የይዞታ ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ለመስጠት፤ ባለይዞታዎች የሁለተኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋጫ ሰርቲፍኬት የመስጠት እና የብሔራዊ የገጠር መሬት የመረጃ ሥርዓት ዝርጋት አፈፃፀም በጣም ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት የተቀናጀ የክትትልና ድጋፍ ስራ በክልልና ወረዳ ደረጃ በመሰራቱ፣ በክልሎች መካከል ጤናማ የሆነ የፉክክር መንፈስ እንዲፈጠር ለማስቻል ከክልል እስከ ወረዳ ድረስ ለሥራው ስኬት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ባለሙያዎች እና ኃላፊዎች የተለያዩ የማበረታቻ ሥራዎችን ተግባራዊ ከማድረግም በተጨማሪ መረጃ ከክልል ክልል የማሳወቅ ሥራ በተከታታይ በመካሄዱ እና የክልሎች አፈፃፀም ላይ መሠረት በማድረግ በየሳምንቱ ግብረ-መልስ የመስጠት ስራ ተጠናክሮ በመቀጠሉ ነው፡፡

የሁለተኛ ደረጃ ሰርቲፍኬትን በመጠቀም በወረዳ ደረጃ የተመዘገቡና የተከናወኑ የመሬት ግብይት ብዛት በአጠቃላይ በ283 ወረዳዎች 474,391 የመሬት ግብይቶች የተከናወኑ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

መረጃዎችን በመሬት ፒ.ከ. ኤስ በ (Land PKS) የሞባይል መተገበሪያን በመጠቀም በሶስት ክልሎች (አማራ፣ኦሮሚያ እና ደቡብ) ውስጥ በሚገኙ 14 ቀበሌዎች የማሳዎችን የማምረት አቅም የመለየት ጥናት ተካሂዷል፡፡

አሳታፊ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ዝግጅትን በተመለከተ ለ392 ቀበሌዎች አሳታፊ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ለማዘጋጀት ታቅዶ ለ410 ቀበሌዎች ተዘጋጅቷል፡፡ አፈፃፀሙም 104 ከመቶ ነው፡፡ በተጨማሪም ለ424 ቀበሌዎች አሳታፊ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድን ለማስተግበር ታቅዶ በ412 ቀበሌዎች ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙም 97 ከመቶ ነው፡፡ የተለያዩ ሠነዶች ዝግጅትን በቀጣይ ለሚሰሩት የፓይለቲንግ ስራዎች እንደመመሪያ የሚያገለግል ረቂቅ standard for Land valuation and Land use planning using Land-PKS and SLLC ስታንዳርድ ተዘጋጅቷል፡፡ የአቅም ግንባታ ሥልጠናን በተመለከተ ከመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጋር ተያያዥነት ባላቸው ርዕሶች ለክልሎች በአጠቃላይ 3,892 አመራሮችና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠና፤ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የልምድ ልውውጥ ሥራዎችን ለማከናወን ተችሏል፡፡

## 5.3. የአፈር ሀብት ልማት

የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ጤንነቱና ለምነቱ የተጠበቀ መሬት ሽፋን በማሻሻል የግብርና ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ከዚህም አንፃር የአፈር ዓይነት መጽሐፈ ካርታ ዝግጅትን በተመለከተ የተንቀሳቃሽ አፈር ላብራቶሪን በመጠቀም የአፈር ለምነት ምጥን ማዳበሪያ ለማዘጋጀት ከሞሮኮ-ኦሲፒ (OCP) ፕሮጀክት እና ከግብርና ሚኒስቴር ጋር የመግባቢያ ሰነድ (Specific Corporate Agreement) ተዘጋጅቶ ለሚኒስትር መ/ቤቱ የህግ ሥራ ክፍል ቀርቦ ተተችቶ ለሚመለከተው አካል ተልኳል፡፡ የአፈር ቅየሳና ካርታ ዝግጅት ሥራዎችን ለማከናወን የጂ.ኦ.ስፓሻል ቴክኖሎጂን በመጠቀም በአፈር ምርመራ ውጤት ላይ የተመረኮዘ የአፈር ሀብት ጤንነትና ለምነት ሁኔታ እና ምክረ-ሀሳብ ካርታዎችን በማዘጋጀት በሚፈለገው ጊዜ፣ ቦታ፣ ዓይነትና መጠን ለማቅረብ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና የልማት አጋር ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት በ171 ወረዳዎችን የኮተቻ አፈር ካርታ ለማዘጋጀት ታቅዶ ለ171 ወረዳዎች የተዘጋጀ ሲሆን አፈፃፀሙም 100% ነው፡፡ እንዲሁም የATA-ETHIOSIS መረጃን በመጠቀም ለ560 ወረዳዎች አሲዳማነት ካርታ ለመስራት ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በጂ.ኦ.ስፓሻል እና በአፈር ሀብት ልማት የባለሙያዎችን አቅም ከመገንባት አንፃር በዚህ በጀት ዓመት በተለያዩ ርዕሶች የክህሎት ክፍተቶችን በስልጠና ለመሙላት ለ150 ባለሙያዎች የሰልጣኞች እና የክህሎት ደረጃቸዉን በመለየት ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 100% ተከናውኗል፡፡

የጨዋማ አፈር ካርታ ዝግጅት ሥራን በተመለከተ በደብብ ክልል በተመረጡ በ3 ወረዳዎች የአፈር ጨዋማነት ካርታ ለማዘጋጀት የመሰረታዊ ካርታ (Base Map) የማዘጋጀት ስራ በዕቅዱ መሠረት 100

በመቶ ተከናውኗል፡፡ የአፈር ናሙና ለመሰብሰብ የሆኑ ወካይ ቦታዎችን መምረጥና የማዘጋጀት ስራ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡ የአፈርና አግሮኖሚ መረጃ አያያዝና ልውውጥ ረቂቅ መመሪያ ማጠናቀቅን አስመልክቶ የሚኒስቴር መ/ቤታችን የበላይ አመራር በተሰጠው የውሳኔ አቅጣጫ መሰረት ከህግ ሥራ ክፍል ጋር በመተባበር ረቂቅ መመሪያው ተዘጋጅቶ ለተጨማሪ አስተያየት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ማስታወቂያ በማውጣት እና ከባለድርሻ አካላትም ጋር በተካሄደ ምክክር መድረክ ከዳበረ በኋላ የተገኘውን ግብዓት በማካተት በመጨረሻም የጸደቀ ሲሆን፣ አፈፃፀሙም 100% ነው፡፡

የኮትቻ አፈር ለማንጣፈፍ የሚያገለግሉ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የአርሶ አደሮችን ግንዛቤ በማሳደግ 655,000 ሄ/ር ለማልማት ታቅዶ 655,000 ሄ/ር መሬት ለማልማት የተቻለ ሲሆን፣ አፈፃፀሙም ከ100% በላይ ነው፡፡ ኮትቻ አፈር ለማንጣፈፍ በአይ.ባር ኢንጅነሪንግ ኃ.የተ.የግ.ማህ.ትራክተር ላይ ተገጥሞ የሚያንጣፍፍ ማሽን የመጀመሪያ ዙር ሙከራ በማድረግ ለሁለተኛ ጊዜ ማሽኑን ማሻሻያ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በተመሳሳይ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ የመጣውን የጨዋማ አፈርን ከማከም አንፃር ጨዋማነትን የሚቋቋሙ የመኖ እና የሰብል ዝርያዎችን በተመረጡ ክልሎች በ189 ሰርቶ ማሳያ (9.24 ሄ/ር) በአርሶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደሮች ማሳ ላይ ለመስራት ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡ ጨዋማ አፈርን የሚቋቋሙ የመኖና የሰብል ዝሪያዎችን 121.26 ኪ.ግ ዘር በኦሮሚያና በአፋር ክልሎች በሚገኙ አራት ወረዳዎች በማሰራጨት 13.48 ሄ/ር ላይ ተዘርተዋል፡፡ በተጨማሪም የተለያያ ጨዋማነትን የሚቋቋሙ ዘሪያዎች 4,758 ኪ.ግ በመቂ ዩኒዬንና በአርሶአደር ማሳ ላይ በማባዛት ጨዋማ የሚበዛት አካባቢ ለማሰራጨት ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡ ከደቡብ ክልል በሀመር ወረዳ 96 የጫዋማ አፈር ናሙና በማሰባሰብ ለብሔራዊ አፈር ምርምራ ማዕከል ለትንተና ተልከዋል፡፡ አሲዳማነትን በመቋቋም የሰብሎች ምርታማነትን የሚያሻሽል በምርምር ማዕከል ተረጋግጦ የወጣ የካልሽየም ኦክሳይድ (CaO) ውህድ ማዳበሪያ በተመረጡት አምስት ክልሎች በአርሶ አደር ማሳ ላይ 520 ሰርቶ ማሳያዎችን ለመስራት ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተከናውኗል፡፡ በተያያዘም የአፈር ለምነትና ጤንነትን ለማሻሻል በጥናት የተረጋገጡ እንደ ግብርና ኖራና ሌሎች ለምነትንና ጤንነትን ለመመለስ የሚያግዙ ግብዓቶች የሚቀርቡበትን ሰንሰለት ለማበጀትና የግብርናን ምርታማነት በዘላቂነት ለማረጋገጥ የተዘዋዋሪ ብድር ፈንድ የህግ ማዕቀፍ እና ሀገራዊ "አፈራችንን እናድን" የንቅናቄ ሰነድ የማጠናቀቅና ቀጣይ ትግበራዉን በዘላቂነት ለማስቀጠል የሚያግዙ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችም በበጀት ዓመቱ ተከናዉነዋል፡፡

የአሲዳማ አፈርን ችግር ለመቅረፍ ከፍተኛ የፌዴራል እና የክልል አመራሮችን ጨምሮ ከ150 ተሳታፊዎች በላይ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቦንጋ ከተማ "የቦንጋ ድክላሬሽን" በሚል የንቅናቄ መድረክ ተካሄዶ የመጀመሪያ ረቂቅ ሰነድ (action plan) ተሠርቶ ለሚመለከተዉ አካላት ቀርቧል፡፡ በተጨማሪም በኦሮሚያ፣አማራና በደቡብ ክልሎች የሚገኙትን የመንግስት የግብርና ኖራ ፋብሪካዎች ድጋፍና ክትትል በማድረግ 126 ሺህ ኩንታል በላይ የግብርና ኖራ ተዘጋጅቶ የአሲዳማነት ችግር ያለባቸዉ ክልሎች

የየራሳቸዉን የአቅርቦት አማራጮችን በመጠቀም ለአርሶአደሮች የማሰራጨት ሥራ በመከናወን ላይ ነዉ፡፡

ከኢትዮጵያ ማዕድን ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት የግብርና ኖራ ጥሬ ዕቃ የሚገኝበት ቦታ የመለየት ስራ ተስርተዋል፡፡ ለአሲዳማ አፈር ልማት የሚውል 30 ሚሊዮን ብር ለደቡብ፣ኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች ተስጥቷል፡፡ ከጂ.አይ.ዜድ አይ.ኤስ.ኤፍ. ኤም በተገኘ ድጋፍ አሲዳማ አፈርን የሚቋቋም 10 ኩ/ል የግብጦ ዘር ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ተሰራጭቷል፡፡

የተፈጥሮ ማዳበሪያን በመጠቀም የአፈር ጤንነትና ለምነትን ከማሻሻል አኳያ በበጀት ዓመቱ 5.26 ሚ/ን ሄ/ር የእርሻ መሬትን በአርሶ አደር ደረጃ ለማልማት ታቅዶ፣ በመኸርና በበልግ የእርሻ ወቅት ከ7.48 ሚ/ን ሄ/ር በላይ መሬት ለማልማት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 142 በመቶ ነው፡፡ የተፈጥሮ ማዳበሪያን የመጠቀም ልምድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን አመላካች ነዉ፡፡ የቨርሚ ኮምፖስት አዘገጃጀት ቴክኖሎጂን በመጠቀም 300 ሺህ ኩ/ል በማዘጋጀት 10,000 ሄ/ር ለማልማት ታቅዶ፣ 349,980 ኩ/ል በማዘጋጀት 11,666 ሄ/ር መሬት ማልማት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም >100% ነው፡፡ በሕየወ ማዳበሪያ (Bio-fertilizer) ቴክኖሎጂ 170,000 ሄ/ር መሬትን ለማልማት ታቅዶ፣ 197,565 ሄ/ር እንዲለማ የተደረገ ሲሆን አፈፃፀሙም 116.2 በመቶ ነው፡፡ ለቀጣይ ምርት ዘመን የአፈር ጤንነትና ለምነትን ለማሻሻል ይረዳ ዘንድ ለሱሉልታ ወረዳ 10 ኪ.ግ የቨርሚ ትል ከአፈር ሀብት ልማት በኩል ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፡፡ በባዮስላሪ ኮምፖስት 58,000 ሄ/ር ለማልማት ታቅዶ፣ 95,000 ሄ/ር መሬት ለማልማት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 162 በመቶ ነው:: የዕቀባ እርሻ ቴክኖሎጂን በተመለከተ 25,000 ሄ/ር መሬት ለማልማት ታቅዶ፣ 25,724.4 ሄ/ር መሬት ለማልማት የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም 103 በመቶ ነው፡፡ የእርሻ መሬትን በኮምፖስት ለማልማት 570 ሚ/ን ኩ/ል ለማዘጋጀት ታቅዶ 611.3 ሚ/ን ኩ/ል የተዘጋጀ ሲሆን አፈፃፀሙም 107 በመቶ ነው፡፡ በሰው ሰራሽ ማዳበሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ በአምስት ክልሎች የተቀናጀ የማዕድንና የተፈጥሮ ማዳበሪያ ሰርቶ ማሳያ በ500 አርሶ አደሮች ማሳ ላይ ለመስራት ታቅዶ 500 ሰርቶ ማሳያ የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም 100% ነው፡፡ እንዲሁም በ2015/16 ምርት ዘመን ለሚገዙ የማዳበሪያ ዓይነቶች (NPS, NPSB, NPSZn, NPSZnB እና UREA) መስፈርት እንዲኖር ከማድረግ አንፃር አንድ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

የአፈር ማዳበሪያና ጤንነት ማሻሻያ ግብዓት ምርት ግብይትና አጠቃቀም ቁጥጥር አዋጅ ከግብርና ሚኒስቴር አመራር በተሰጠው አስተያየት መሰረት ተስተካክሎ ለሚመለከተው አካል ቀርቧል፡፡ የተቀናጀ የአፈር ጤንነትና ለምነት አያያዝ ላይ ማኑዋል እና በተፈጥሮ ማዳበሪያ ዙሪያ ዶክምንታሪ ፊልም በማዘገጀት በግብርና ሚኒስቴር ዌብሳየት ላይ እንደለቀቀ ተደርገዋል፡፡ለስምንት ክልሎች (ኦሮሚያ፣ ደቡብ፣ደቡብ ምዕራብ፣ሲዳማ፣ሀረሪ፣ድሬዳዋ፣ቤንሻንጉል ጉሙዝ እና ጋምቤላ) እና ከ43 ዞኖች ለተወጣጡ የአሰልጣኞች ስልጠና በአጠቃላይ ለ200 ባለሙያዎች በአፈር ጤንነትና ለምነት ማሻሻያ ቴክኖሎጂ እና በድጅታል አፈር ካርታና ቅየሳ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ተሰጥቷል፡፡

## 5.4. የአነስተኛ ይዞታ መስኖ ልማት

የአነስተኛ ባለይዞታዎች የተለያዩ ውሀ አማራጮችን (የቅርብ ጥልቀት ዉኃ ጉድጓድ፣ የቤተሰብ ኩሬ፣ የወንዝ ጠለፋን) በመጠቀም የመስኖ ሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የመስኖ ውሀ አቅርቦት ላይ ሰፊ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ከዚህም አንፃር አማራጭ የመስኖ ውሀ አቅርቦትን ከማሳደግ አኳያ ምንም እንኳን የግንባታ እቃዎች አቅርቦት እጥረትና ዋጋ መናር ከፍተኛ ተግዳሮት ቢሆንም በክልሎች በግንባታ ሂደት ላይ የነበሩ 193 አዳዲስ የመስኖ አውታሮች ግንባታ ለማጠናቀቅ ታቅዶ 120 የተከናወነ ሲሆን፣ አፈፃፀሙም 62 በመቶ ነው፡፡ በቤተሰብ ደረጃ የውሀ አማራጮችን ከማዘጋጀት አንጻር 77 ሺህ ለማዘጋጀት ታቅዶ 63 ሺህ የመስኖ ውሀ አማራጭ ዝግጁ ሆኗል፡፡ አፈፃፀሙም 82 በመቶ ነው፡፡ በዚህም 29 ሺህ ሄ/ር የመስኖ መሬት ዝግጁ ለማድረግ ታቅዶ 44.08 ሺህ ሄ/ር የተከናወነ ሲሆን አፈፃፀሙም 100+ በመቶ ነው፡፡ እንዲሁም 114 ሺህ አ/አደሮችን ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ 114 ሺህ አ/አደሮችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም 100 በመቶ ነው፡፡ የባለሙያዎችን እውቀትና ክህሎት ከማሳደግ አንፃር በታቀደው መሰረት በየደረጃው ለሚገኙ ለ147 (13 ሴት) ባለሙያዎች በንድፈ ሀሳብና በተግባር የተደገፈ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ አነስተኛ መስኖ ልማት ሽፋን ለማሳደግ የሚደግፉ ፕሮጀክቶች (DRDIP, PASIDP, AGP, SHIDP, SDG) ስራዎችን በቅንጅት ለመምራት የሚያስችል የአሰራር ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

የባለአነስተኛ ይዞታ መስኖ ልማት ፕሮጀክት (SHIDEP) ተግባራትን በሚመለከት በያዝነው በጀት ዓመት 56 ፕሮጀክት 2,900 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ ጥናትና ዲዛይን ሰነድ ግምገማ ለማካሄድ ታቅዶ በበጀት አመቱ 2,082.2 ሄ/ር ማልማት አቅም ያላቸው 25 ፕሮጀክቶችን ዲዛይን ማከናወን ተችሏል፡፡ በ2015 በጀት ዓመት 1,965 ሄ/ር የማልማት አቅም ያላቸውና 5,305 አ/አደር ተጠቃሚ የሚያደርጉ 27 አውታሮችን በዚህ ዓመት የታቀደ ሲሆን አማካይ አፈፃፀማቸው 82% ደርሷል፡፡ እስካሁን 1,332.07 ሄ/ር ማልማት አቅም ያላቸው እና 3,787 ማህበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደረጉ 18-ፕሮጀክቶች ማጠቃለል እና ለልማት ዝግጁ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በግንባታ ላይ ያሉ 46 ፕሮጀክቶችን ደግሞ የፊዚካል አፈፃፀም ደረጃቸው በአማካይ 68.82% ላይ ይገኛሉ፡፡ የውሃ መሳቢያ ቴክኖሎጂዎችን ከማቅረብ አኳያ በፀሐይ ኃይል የሚሰራ 150 ሄ/ር ማልማት የሚችሉ 60 የውሀ መሳቢያ ፓምፖች የግዥ ተከናውኗል:: በቀጣይ ዓመት የተከላና የማስተዋወቅ ስራ ይሰራል፡፡ በተጨማሪም የአነስተኛ ጉድጓድ መቆፈሪያ ማሽን እና ሌሎች ለውሃ አጠቃቀም አጋዥ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች ግዥ ተከናወኗል፡፡ የመስኖ ልማት ዘላቂነትን ለመከታተልና ለመደገፍ እንዲያስችል የመስኖ አውታሮች በውሀ አጠቃቀም ችግር የሚከሰተውን የጨዋማነት ደረጃን ለማወቅ ጥናት በተካሄደባቸው የመስኖ አውታሮች የጨዋማነት ደረጃ በአጠቃላይ ከ40 በመቶ በላይ ከፍተኛ የጨዋማነት መስፋፋት እንደታየባቸው አመላካች ውጤት ተገኝቷል፡፡

## 6. የደን ልማት

የደን ሀብት በርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ጥቅሞችና ግልጋሎቶች አሉት። ይህንን ግልጋሎት ለማሳደግ በ2015 በጀት ዓመት በርካታ ተግባራትን ለማከናወን በዕቅድ ተይዞ ወደስራ ተገብቷል። ከተከናወኑ ዋና ዋና ስራዎች ከሮያሊቲ እና ከተወረሱ የደን ምርት ውጤቶች ሽያጭ 250 ሚልዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች በተሰራው ስራ 329.33 ሚ/ን ብር የተሰበሰበ ሲሆን አፈፃፀሙ ከእቅዱ በላይ ነው። ከእቅድ በላይ እንዲሆን ያደረገው ምክንያት የተሻለ ክትትልና ድጋፍ በመደረጉ እና ክልሎችም ትኩረት ስለሰጡት ነው።

በበጀት አመቱ ውስጥ ለ250,000 ዜጎች የስራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በደን ጥበቃ፣ የደን ምርቶችን በመጫን፣ በማጓጓዝና በማውረድ፣ በችግኝ ተከላና እንክብካቤ፣ በእንጨት ኢንዱስትሪ እና ኢንተርፕራይዞች በመሰማራት፣ የደን ምርት ውጤቶችን በማቅረብ፣ በመቸርቸር እና በመላክ፣ በከሰል ማክሰል (አማራ ክልል) እና የመሳሰሉት የስራ መስኮችን በአጠቃላይ ለ496,583 ዜጎች (በቋሚ 39,713 እና ጊዜያዊ 456,870) የስራ ዕድል ለመፍጠር የተቻለ ሲሆን አፈፃፀም ከእቅዱ በላይ ነው። አፈፃፀሙ ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት በአረንጓዴ አሻራ ስራ ከመንግስት እስከ ህበረተሰቡ ድረስ ትኩረት በማግኘቱ እንዲሁም በግለሰቦች፣ በኢንተርፕራይዞች እና ኢንዱስትሪዎች በኩል የደን አጠቃቀሙ ስራ ከጊዜ ወደ ጊዜ እተሻሻለ በመምጣቱና የስራ ዕድል በመፈጠሩ ነው።

የአገራዊ የደን ሽፋንን ለማሳደግ ይቻል ዘንድ 0.6 ሚ/ን ሄ/ር የተከላ መሬት ለመለየት ታቅዶ በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች በተደረገው የመስክ ክትትልና ድጋፍ 0.748 ሚ/ን ሄ/ር ማዘጋጀት የተቻለ ሲሆን፣ አፈፃፀሙም ከእቅዱ በላይ ሆኗል። ከዚህም ውስጥ የቀርከሀ ደን ሽፋን 20,000 ሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 77,413.44 ሄ/ር ማድረስ የተቻለ ሲሆን አፈፃፀሙም ከእቅዱ በላይ ነው። አፈጻጸሙ ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት ለቀርከሀ ልማት የተሰጠው ትኩረት ከፍተኛ በመሆኑና ከመደበኛ በተጨማሪ የፕሮጀክቶች እና የተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተሳትፎ ከፍተኛ በመሆኑ ነው። 3 ቢሊዮን ደረጃቸውን የጠበቁ ችግኞች ተፈልተው እንዲተከሉ ለማድረግ ታቅዶ 3.415 ቢሊዮን ከእቅድ በላይ የደን ችግኞች መትከል ተችሏል። ከዚህ ውስጥ 48.383 ሚሊዮን የቀርከሀ ችግኝ ነው።

የተተከሉ ችግኞችን የጽድቀት መጠንን ለማሳደግ ይቻል ዘንድ የተለያዩ የድህረ ተከላ የእንክብካቤ፣ የአረምና ኩትኳቶ እና አልፎ አልፎ ፍግ መጨመርና ውሃ የማጠጣት ስራ በተደረገው የመስክ ድጋፍና ክትትል ለማየት የተቻለ ሲሆን፣ የዓመቱ የመጀመሪያ ዙር የጽድቀት መጠን 85 በመቶ ለማሳደግ ታቅዶ ከክልሎች በተገኘው መረጃ መሰረት በአማካኝ 84.83 በመቶ የችግኝ የጽድቀት መጠን ተመዝግቧል። 18.68 ሚ/ን ሄ/ር ነባር የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ደኖችን ለመጠበቅ፣ ለመንከባከብና በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስችል ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል። 2.48 ሚ/ን ሄ/ር ነባር የተፈጥሮ ደኖች ላይ አሳታፊ የደን አስተዳደር ስርዓትን በመተግበር በዘላቂነት እንዲጠበቁና ተገቢውን ግልጋሎት እንዲሰጡ በሚመለከታቸው አካላት በየደረጃዉ ለማድረግ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል። በአመቱ

ለ200,000 ሄ/ር ደኖች የማኔጅመንት ፕላን እንዲዘጋጅና እንዲተገበር ለማድረግ ታቅዶ 188,331.65 ሄ/ር ደኖች የማኔጅመንት ፕላን የተዘጋጀላቸው ሲሆን አፈጻጸሙም 94.17 በመቶ ተሸፍኖዋል፡፡ በምርምሩ ዘርፍ በአመቱ 48 የምርምር ውጤቶችን (መረጃዎች) ለማውጣት ታቅዶ 39 የምርምር ዉጤቶችን በማዉጣት አፈጻጸሙን 81.25 በመቶኛ ማድረስ ተችሏል፡፡

## 7. የብዝሀ ህይወት ጥበቃ አጠቃቀም

የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት አገሪቷ ያላትን የእፅዋት፣ የእንስሳትና የደቂቅ አካላት ብዝሀ ሕይወትና ተያያዥ ነባር የማህበረሰብ ዕውቀት፣ እንዲሁም እነዚህን አቅፎ የያዘውን ስርዓተ-ምህዳር የመጠበቅ፤ የማልማትና በዘላቂነት ጥቅም ላይ እንዲውል ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው፡፡ የሀገሪቱን የብዝሀ ሕይወትና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀቶች በማሰስና በመቃኘት ተለያይነትንና ስርጭትን፣ ዋጋማነትን እና የመመናመን አደጋዎችን በምርምር የመለየት ተግባራትን በማስፋትና መዝግቦ በመያዝ በዘርፉ ያለውን ዕውቀት ማሳደግና በባለቤትነት እንዲታወቁ **አሰሳና ቅኝት ማድረግን** በተመለከተ 4 (አራት) ለጥቅም ተጋሪነት የሚዉሉ ዝርያዎች ፍላጎት ለመለየት አሰሳና ቅኝት ጥናት ለማድረግ ታቅዶ 3 ዝርያዎች ተለይተዉ የሁለት (Pseudomonas putida እና Rhizopus oryzae) የተባሉ ዝርያዎች ተለይተው የጽሑፍ ሥራ ተጠናቋል፡፡ የባዮስፌር ሪዘርቭ ላይ አሰሳ፣ ቅኝትና ቆጠራ ለማካሄድ ታቅዶ በጣና ባዮስፌር ላይ እምቦጭ ያለበትን ሁኔታ ለማወቅ የሚያስችል የዳሰሳ ጥናት ተሰርቷል፡፡ የደንና ግጦሽ መሬት ዕፅዋት ያሉበትን ደረጃ ለመለየት በአምስት የደን ቦታዎች ላይ አሰሳ ቅኝት እና ቆጠራ ለማድረግ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት በደቡብ ክልል ጉራጌ ዞን (የሺቤትይ አምባን) በወላይታ ዞን (አቻ ደን) በባሌ ዞን (ጊኒር እና ጎሮ ) እና በምእራብ ሸዋ (ቱሉ ኮርማ) ዞኖች ደን ላይ 100% ተከናውኗል፣ የደንና ግጦሽ መሬት ዕፅዋት ዝርያ የስብጥር ለዉጥ ጥናት በሁለት ቦታዎች ላይ ለማካሄድ ታቅዶ በደቡብ ክልል አርጎ ጥብቅ ደን እና በአማራ ክልል በዕቅዱ መሰረት 100% ተከናዉኗል፡፡ በእንስሳት ብዝሀ ሕይወት በአምስት ቦታዎች አሰሳ፣ ቅኝትና ቆጠራ ለማካሄድ ታቅዶ በእቅዱ መሰረት 100% ተከናውኗል፡፡ 425 የሄርባርየም ናሙናዎችን ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለመሰብሰብ ታቅዶ 425 (>100%) ናሙናዎች ተሰብስቧል፡፡ እንዲሁም ለእንስሳት ቤተ-መዘክር (Zoological Museum) የዱርና የውሃ ውስጥ እንስሳት ከ150 ዝርያዎች (Species) 1,500 ናሙናዎች ለመሰብሰብ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት 100% ተከናዉኗል፡፡

**ተለያይነትና ስርጭትን** 707 የአዝዕርትና ሆርቲካልቸር ናሙናዎችን ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለመሰብሰብ ታቅዶ 821 ናሙናዎች ተሰብስቧል (>100%) ፣ የ3,025 የአዝዕርትና ሆርቲካልቸር ናሙናዎችን የተለያይነትና የባህሪ ትንተና ለማድረግ ታቅዶ 2,940 (95%) ተከናዉኗል፣ የአራት መኖ ዕፅዋት ዝርያዎችን ውጫዊና ውስጣዊ ባህርያትን የማወቅና የመተንተን ስራ ለማከናወን ታቅዶ በዕቅዱ

መሰረት ተከናዉኗል፣ የሶስት ደን እፅዋት ዝርያዎች የክምችት ባህሪ ለማጥናት (ለማወቅ) ታቅዶ የሶስት ዝርያዎች (Acanthus *sennii, Crotalaria roseni and sapium ellipticum*) ዘር ለመሰብሰብ፣ የእርጥበት ልኬት እና የአበቃቀል ዘዴ ጥናት ለማከናወን ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት (100%) ተከናዉኗል፣ የሁለት ለማዳ እንስሳት ንዑስ ዝርያዎችን ባህሪ ግምገማና ትንተና ለማድረግ ታቅዶ በታቀደዉ መሰረት 100% ተከናዉኗል፤ አንድ በማይክሮ አልጌና አንድ ሞሉኩላርን በተመለከተ የደቂቅ አካላት ዝርያዎች ባህሪ ትንተና ጥናት ተካሂዷል፡፡ አንድ የተለያይነትና ስርጭት አካላዊ እና የሞለኩላር ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ በዕቅዱ መሰረት 100% ተከናዉኗል፣ አንድ የማህበረሰብ ዕዉቀት አሰሳና ምዝገባ ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ 100% ተከናዉኗል::

***ዋጋማነት ጥናትን*** በበጀት አመቱ አምስት የዋጋማነት ጥናት ለማካሄድ ታቅዶ አምስቱም ተከናዉኗል፡፡ እነሱም፤-የአዝ/ሆርቲካልቸር ዝሪያዎች አንድ የዋጋማነት ትመና ጥናት ማካሄድ ታቅዶ 100% ተከናዉኗል፣ የባዮስፌር ሪዘርቭ አገልግሎት በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዙሪያ በተመለከተ የዋጋማነት ጥናት አንድ ታቅዶ አንድ (በሸካ ባዮስፈር ሪሰርቭ ላይ) 100% ተከናዉኗል፣ በደን ስርዓተ-ምህዳር ላይ አንድ የዋጋማነት ጥናት ለማድረግ ታቅዶ በቀይ አፈር አርጎ ጠብቅ ደን ላይ 100% ተከናዉኗል፣ በእንስሳት ዝርያዎች/ንዑስ ዝርያዎች አንድ የዋጋማነት ትመና ጥናት ለማድረግ ታቅዶ በሶማሌ ክልል የኦጋዴን ግመል ንዑስ ዝርያ የዋጋማነት ትመና ጥናት 100% ተደርጓል፣ ለጥቅም ተጋሪነት የሚውል (balanitus aegeptica) የተባለ ዝርያ ለመለየት አንድ የዋጋማነት ጥናት ለማድረግ ታቅዶ 100% ተከናዉኗል::

በምርምር በመታገዝ የሀገሪቱን ብዝሀሕይወትና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀቶች በዘለቄታዊነት መጠቀም፣ ማበልጸግና ከሀብቱ የሚገኘውን ጥቅም ማሳደግን በሚመለከት በአንድ ወራሪ መጤ ዝርያዎች የተፅእኖ ግምገማ ስራ ለማከናወን ታቅዶ የብዝሀ ሕይወት ማዕከላትን በማስተባበር ስድስት ዝርያዎች ላይ ተከናውኗል፡፡ በአመቱ 10,000 ሄ/ር ቦታዎችን ከወራሪ መጤ ዝርያዎች ለማፅዳት ታቅዶ 22,311 ሄ/ር ሽፋን ቦታዎችን ከወራሪ መጤ ዝርያዎች የማፅዳት ስራ ማሳካት ተችሏል:: ከተፈጥሮ አካባቢያቸው የጠፉትን የአገር-በቀል የደንና ግጦሽ መሬት እፅዋት አምስት ዝርያዎችና 500 ናሙናዎችን እንዲሁም የተመናመኑ /የጠፉ የአዝዕርትና ሆርቲካልቸር ሁለት ዝርያዎች አራት አይነቴዎች በድምሩ 7 ዝርያዎች እና 504 ናሙናዎች መልሶ የመተካት ስራ ለማከናወን ታቅደ የአገር-በቀል የደንና ግጦሽ መሬት እፅዋት አምስት ዝርያዎችና 500 ናሙናዎችን እና የአዝዕርትና ሆርቲካልቸር ሁለት ዝርያዎች ስድስት አይነቴዎች በድምር 7 ዝርያዎችና 506 ናሙናዎች መልሶ የመተካት ሥራ ተከናውኗል፡፡ 40 ዝርያዎችና 6,465 የአዝዕርትና ሆርቲካልቸር የደንና ግጦሽ መሬት ዕፅዋት፤ የእንስሳት እና የደቂቅ አካላት ዝርያ/ናሙናዎችን ለምርምርና ለቀጣይ ልማት ለማሰራጨት ታቅዶ 37 ዝርያዎችና 7,650 ናሙናዎች ለማሰራጨት ተችሏል፡፡

የአርክቦትና ጥቅም ተጋሪነት ሥርዓትን በምርምር በመታገዝ ተግባራዊ በማድረግ ሀገሪቱና ማህበረሰቦቿ ከብዝሀ ሕይወትና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀቶች ከሚገኘው ጥቅም ፍትሃዊና ሚዛናዊ ድርሻ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣ 118 የአርክቦት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ 170 ፈቃድ (>100) ለመስጠት ተችሏል፤ ህገ-ወጥ የጀነቲክ ሀብት ዝውውር ቁጥጥር 12 ድርጅቶች ላይ ለማድረግ ታቅዶ አስራ አራት የተከናወነ ሲሆን ለሁለት ድርጅቶች የማስጠንቀቅያ ደብዳቤ ተፅፏል፣ 120 የአርክቦት ፈቃድ መረጃ ወደ ሀገራዊ የመረጃ ቋት ለማስገባት ታቅዶ 170 መረጃ ለማስገባት ተችሏል፣ የጥቅም ተጋሪነት የአርክቦት ፈቃድ ለንግድ አላማ የሚውሉ ስምምነት 3 የአርክቦት ውሎችን ለመፈራረም ታቅዶ እቅዱ 100% ተከናውኗል (የዶኮሞ ፒኤልሲ ጋር በቀረጥ እጽዋት አጠቃቀም ውል ማራዘሚያ፣ ከጥሁር ፒኤልሲ ጋር በደቂቅ አካላት ሕያው ማዳበሪያ ምርት) ፣ የአርክቦት ቅድመ ክፍያ ብር 200 ሺህ ለመሰብሰብ ታቅዶ ብር119 ሺህ በመሰብሰብ የእቅዱ 60% ተከናውኗል (የዶኮሞ ፒኤልሲ ውል ማራዘሚያ ቅድመ ክፍያ ባለመኖሩ እቅድ ክንውኑ ዝቅ ሊል ችሏል) ፣ በ12 ወራት ውስጥ 2 ረቂቅ መመሪያዎችን ለማዘጋጀትና በህዝብ ለማስገምገም ታቅዶ 3 መመሪያዎች (የአርክቦት ፈንድ ረቂቅ መመሪያ፤ የጄነቲክ ሀብት ዝውውር ረቂቅ መመሪያ፤ የብዝሀ ሕይወት ናሙና ክፍያ ረቂቅ መመሪያ) በማዘጋጀት ለህዝብ አስተያየት በኢንስቲትዩቱ ድረ ገፅ ተደራሽ ተደርገዋል፤ ለሚመለከታቸው አካላትም ተልከዋል።

## 8. የግብርና ኢንቨስትመንትና ግብርና ግብይት

### 8.1 የሰፋፊ አርሻና እንስሳት ልማት የግል ኢንቨስትመንት

በ2014/15 የምርት ዘመን ከክልሎች ጋር በመቀናጀት 200 ሺህ ሄክታር መሬት በጥናት ለመለየት ግብ የተጣለ ሲሆን በ6 ክልሎች (በአፋር፣ አማራ፣ ደቡብ ብ/ብ/ህ/፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ኦሮሚያ እና ሶማሌ) በድምሩ 146.73 ሺህ ሄክታር መሬት ተለይቷል፤ አፈጻጸሙም 73.76% ነው። እንዲሁም በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 145 ሺህ ሄክታር መሬት ለባለሃብቶች ለማስተላለፍ የታቀደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 94.60 ሺህ ሄክታር መሬት (አፈጻጸሙ 65.20%) በ6 ክልሎች (ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ደቡብ ብ/ብ/ሕ/፣ ሶማሌ፣ጋምቤላ) ለባለሃብቶች እንዲተላለፍ ተደርጓል። ከመሬት ዝግጅትና ማስተላለፍ ዕቅድ አፈጻጸሙ ማነስ ጋር በተያያዘ ከሚጠቀሱ ምክንያቶች መካከል ባለፉት ወራቶች በሃገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች የተከሰቱት የፀጥታ ችግሮች በባለሀብት እንቅስቃሴ ላይ ጫና መፍጠር፣ በክልል ያለው የመረጃ ፍሰት ከፌደራል አደረጃጀት ጋር አለመናበብ፣ አብዛኞቹ ክልሎች ዘርፉን የሚደግፍ አደረጃጀት አለመዘርጋታቸው፣ የመሬት ጥናትና ልየታ ተግባራትን በብቃት የሚፈጽም ባለሙያ በበቂ ደረጃ በፌደራልና በክልል የተደራጀ አለመሆንና ለጥናት ሥራ የሚያስፈልጉ የቴክኒክ መሳሪያዎችም የተሟሉ አለመሆን ከሚጠቀሱ ምክንያቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በሰፋፊ እርሻ የተሰማሩ የግል ባለሃብቶችን ወቅታዊ መረጃ በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ዘዴ (kobotoolbox) በመጠቀም በ3 ክልሎች ለማደራጀት በተያዘው ግብ መሰረት ዕቅዱ 100% ተከናውኗል፡፡ በዚህ መሰረት በደቡብ ምዕራብ ክልል ለ322 ባለሃብቶች የተላለፈው 118,589 ሄ/ር መሬት በሲዝ ሲተላለፍ ከዚህ መሬት ውስጥ 58% ያህሉ የለማ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም በአማራ ክልል የግል ባለሃብቶቹ ከሚገኙባቸው 12 ዞኖች መካከል 90 በመቶ የእርሻ ኢንቨስትመንት በሚገኝበት በ5 ዞኖች ለ1,309 ባለሃብቶች 221,309 ሄክታር መሬት የተላለፈና ወደ ልማት የገባ መሆኑን የሚያመላክት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በደ/ብ/ብ/ህ/ክልል በ8 ዞኖችና በ4 ልዩ ወረዳዎች ለ286 ባለሃብቶች 98,799 ሄክታር መሬት የተላለፈና ወደ ልማት የገባ 47,759 ሄክታር መሬት የሚያሳይ መረጃ በዘርፉ እየተስተዋሉ ያሉ የመሰረተ ልማት (መንገድ፣ ሃይል፣ መስኖ አውታር) ፣ የፋይናንስ ብድር፣ የግብዓት አቅርቦትና የመሳሰሉት ተግዳሮቶች ጭምር እንዲሰበሰብ ተደርጓል፡፡

የህግ ማዕቀፍ ዝግጅት/ማሻሻያ አሰራር ስርዓት በተመለከተ የሰፋፊ እርሻ ኢንቨስትመንት አሰራርን በማሳለጥ ዘርፉን ለማሳደግና ውጤታማ ለማድረግ ኃላፊነት የተሞላበት የግብርና ኢንቨስትመንት የአሰራር ስርዓት ጋይድላይን እና በእርሻ ኢንቨስትመንት ተሰማርተው የተሻለ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ባለሃብቶችን ለመለየት የሚያስችል የምርጥ ተሞክሮ (የቤንች ማርክ) የአሰራር ስርዓት መዘጋጀቱ፣ የክትትልና ድጋፍ ማኑዋል ለማዘጋጀት በተያዘው ዕቅድ እንዲጠናቀቅ የተደረገ ሲሆን አፈጻጸሙ 100% ሆኗል፡፡

በሃገር አቀፍ ደረጃ የግብርና ኢንቨስትመንት ባለድርሻ አካላት የምክክር መድረክ 2 ዙር ለማካሄድ በታቀደው መሰረት 2 ዙር ተካሂዷል፡፡ በዚህም የፌደራልና የክልል ባለድርሻ አካላት የስራ ሃላፊዎችና ባለሙያዎች፣ የባለሃብት ማህበራት አመራር አካላትና ባለቤቶች የተሳተፉበት የምክክር መድረክ በአዲስ አበባ ከተማ የተካሄደ ሲሆን በምክክር መድረኩ የኢንቨስትመንት መሬት አስተዳደርና ዘላቂ ልማት፣ የግብርና ኢንቨስትመንት ፖሊሲ በኢትዮጵያ፣ ኃላፊነት የተሞላበት የግብርና ኢንቨስትመንት በኢትዮጵያ እና የባለሀብት ማህበራት ማጠናከር አስፈላጊነት አጀንዳዎች ላይ ውይይት በማድረግ በቀጣይ በዘርፉ የሚስተዋሉ የመሬት፣ የፋይናንስና የቴክኖሎጂ አቅርቦት በማሻሻል ረገድ ባለድርሻ አካላት የዕቅዳቸው አካል በማድረግ መስራት እንደሚጠበቅባቸው ስምምነት ላይ የተደረሰ ሲሆን የምክክር መድረኩ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ በክልል ደረጃ የሚካሄድ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል የፍራፍሬ ልማት ማለትም አቮካዶ፣ ሙዝና ፓፓያ የሚመረትበትን ቦታ እና በልማት የተሸፈነ መሬት በዲጂታል ዘዴ (kobotoolbox) በመጠቀም ለመለየት ጥናት በማድረግ በሲዳማ ብ/ክ/መ 21 ክላስተር 15,652 ሄ/ር ማሳ፣ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ 65 ክላስተር 1,231.4 ሄ/ር፣ በአማራ 68 ክላስተር 1,453.87 ሄ/ር እና ደቡብ ብ/ብ/ክልል በ5 ዞኖች 3,891 ሄ/ር መሬት በአቮካዶ፣ ሙዝና ፓፓያ የለማ መሬት መረጃ እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡

በእንስሳትና ዓሳ ኢንቨስትመንት የተሰማሩ ባለሀብቶችን ለመከታተልና ለመደገፍ የሚያስችሉ የአሰራር ስርአቶች የተዘጋጁ ሲሆን፣ ዋና ዋናዎቹም የንብ ምርቶች ግብይት፣ የወተት ምርቶች ግብይትና የዶሮ ምርቶች የግብይትና ልማት የህግ ማዕቀፎች፣ አዋጆች፣ የአትክልትና ፍራፍሬ፣ እና የመኖ የግብይት መመሪያዎች እና ሌሎችንም ለማዘጋጀት ጥረት ተደርጓል።

በምርት ዘመኑ የግብርና ምርት ውል አሰራርን ለማስፋት የሚያስችሉ የተለያዩ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች የተከናወኑ ሲሆን፣ በዚህም 135,749 አርሶ አደሮች ከተለያዩ ኩባንያዎች ጋር በግብርና ምርት ውል ትስስር በመፍጠር 589,113.5 ምርት ቶን የሰብል ምርት ተመርቷል። በ2015 በጀት ዓመት ተቋማትን በማስተባበር በቁጥር ከ60 በላይ የሆኑ የአበባ ኩባንያዎችን እና ከ25 በላይ የአትክልትና ፍራፍሬ ኩባንያዎችን ማነቀ በመፍታት፣ በመስክ ደረጃ ተከታታይ የቴክኒክ ድጋፍ በማድረግ እንዲሁም ገቢን ለማሳደግ የሚያስችሉ ድጋፎችን ተደርገዋል።

## 8.2 የግብርና ዘርፍ የወጪ ንግድ

### አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ

የወጪ ንግድ በመጠንና በገቢ ማሳደግ በተመለከተ በአመቱ 526,246.95 ቶን የሆርቲካልቸር ምርት በመላክ 770.24 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት ታቅዶ 288,313 ቶን የሆርቲካልቸር ምርት በመላክ 658.3 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማግኘት ተችሏል። አፈጻጸሙ ከዕቅዱ ጋር ሲነጻጸር በመጠን 54.8 በመቶ ሲሆን በገቢ 85.5 በመቶ አፈጻጸም ተመዝግቧል። ከ2014 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር በመጠን 14.1 በመቶ ቅናሽ ሲያሳይ በገቢ 4.7 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል።

የበጀት ዓመቱን ዕቅድ ለማሳካት በርካታ የድጋፍ ስራዎች የተከናወኑ ሲሆን ከእነዚህ መካከል የአትክልት እና ፍራፍሬ ዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ ወለል በጥናት ተከልሶ ተግባራዊ መደረጉ፣ ከቁልፍ ባለድርሻ አካላት ጋር ስትራቴጂካዊ አጋርነትን በመፍጠር የቅንጅት ስራን በመስራት የኩባንያዎችን ማነቀ በተሻለ ደረጃ መፍታት፣ በሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ተሰማርተው የተሻለ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ባለሃብቶችን ለመለየት የሚያስችል የምርጥ ተሞክሮ (የቤንች ማርክ) የአሰራር ስርዓት መዘጋጀቱ፣ የአበባ ኤክስፖርት ምርት የምርት ጥምርታ ስታንዳርድ መዘጋጀቱ፣ የኮንሶሊዴሽን መመሪያ ተዘጋጅቶ በኢንቨስትመንት ኮሚሽን በኩል እንዲጸድቅ መላኩ፣ በተመረጡ የፍራፍሬ ሰብሎች ማለትም የአቮካዶ፣ ሙዝና ፓፓዬ ምርቶችን በግል ባለሃብቶችንና በክላስተር ደረጃ የተተከሉትን ወቅታዊ መረጃ በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ዘዴ (kobotoolbox) በመጠቀም በ5 ክልሎች (ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ እና ሲዳማ) ለማደራጀት ጥረት መደረጉ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል በትኩረት የተለያዩ

ድጋፍ ስራዎች መሰራታቸው፣ የኩባንያዎች የስራ ተነሳሽነት መኖር ለዕቅዱ መሳካት አስተዋጽዖ አበርክቷል፡፡

## ቡና ሻይና ቅመማ ቅመም

የቡና ኤክስፖርት መጠንና ገቢ እንዲያድግ ከአምራች እስከ ገበያ መዳረሻ በማስተባበር፣ በመከታተል፣ በመደገፍና በመምራት በበጀት ዓመቱ 360,144.49 ቶን ቡና በመላክ 1,800.72 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 240,369.21 ቶን (ከዕቅዱ 67%) በመላክ 1,331.78 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር (ከዕቅዱ 74%) ገቢ ተገኝቷል፡፡ አፈጻጸሙ ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በመጠን 62,393.11 ቶን (-20.61%) እና በገቢ 92.78 ሚሊዮን ዶላር (-6.51%) ቅናሽ ተመዝግቧል፡፡

የኤክስፖርት ቡና መጠን ከዕቅዱ የቀነሰበት ምክንያቶች መካከል፣ የዓለም ቡና ዋጋ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በአማካኝ በየወሩ በ5 በመቶ እየቀነሰ በመምጣት 32 በመቶ ቅናሽ ላይ ደርሷል፡፡ በዚህ ምክንያት ገዢዎች የተፈራረሙትን 394 ኮንትራት መጠኑ 28,209.53 ቶን እና ጠቅላላ ገቢው 133,223,654.78 የአሜሪካን ዶላር አለመፈጸማቸው፡፡ ለማሳያ 344 ቶን ኤል ሲ ተከፍቶ ሳይላክ ቀርቷል፡፡ በብዛት ኤል ሲ ከፍቶ ቡናዉን ለመዉሰድ ፍላጎት ያጡ የአረብ ሀገራት ገዢዎች ሲሆኑ ሌላው የሀገር ውስጥ የቡና መሸጫ ዋጋ መጨመር ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

በበጀት ዓመቱ 1,879.38 ቶን የሻይ ምርት በመላክ 3.19 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 899.60 ቶን (ከዕቅዱ 48%) በመላክ 2.03 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር (ከዕቅዱ 64%) ገቢ ተገኝቷል፡፡ አፈጻጸሙ ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከተላከው ጋር ሲነጻጸር በመጠን 3.20 ቶን (-0.35%) ቅናሽ እና በገቢ 0.18 ሚሊዩን ዶላር (9.49%) ጭማሪ አሳይቷል፡፡
በበጀት ዓመቱ 14,896 ቶን የቅመማ ቅመም ምርት በመላክ 20.37 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 6,323 ቶን (ከዕቅዱ 42%) በመላክ 10.48 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር (ከዕቅዱ 51%) ገቢ ተገኝቷል፡፡ አፈጻጸሙ ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በመጠን 2,208.8 ቶን (-25.89%) እና በገቢ 6.33 ሚሊዩን ዶላር (-37.65%) ቅናሽ አሳይቷል፡፡
በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ 376,919.87 ቶን የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርት በመላክ 1,824.28 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 247,591.81 ቶን (ከዕቅዱ 66%) በመላክ 1,344.3 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር (ከዕቅዱ 74%) ገቢ ተገኝቷል፡፡ አፈጻጸሙ ባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከተላከው ጋር ሲነጻጸር በመጠን 64,605.11 ቶን (-20.69%) እና በገቢ 98.94 ሚሊዩን ዶላር (-6.86%) ቅናሽ ተመዝግቧል፡፡

የስጋና ስጋ ተረፈ ምርት፣ ወተት፣ ማር እና ሰም ምርቶች የወጪ ንግድ አፈጻጸም ሲታይ በአመቱ 100.3 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ 74.3 ሚ/ን የአሜሪካን ዶላር ወይም የዕቅዱን 74 በመቶ ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡

## 8.3 የግብርና ግብዓት አቅርቦት

### ማዳበሪያ አቅርቦት እና ስርጭት

ለ2015/16 ምርት ዘመን ከክልሎች የቀረበ የአፈር ማዳበሪያ ፍላጎት 2,213,579 ሜ/ቶን ሲሆን 1,287,552 ሜ/ቶን (500,000 ሜ/ቶን UREA፣ 218,894 ሜ/ቶን NPS እና 568,658 ሜ/ቶን NPSB) ግዥ የተፈጸመ ሲሆን በተጨማሪም የትግራይ ክልል ባሳወቀት ፍላጎት መሠረት 80 ሺህ ሜ/ቶን እና ለመጠባበቅያ 30 ሺህ ሜ/ቶን ተጨምሮበት:: በዚሁ መሰረት ለምርት ዘመኑ የተፈቀደውን የብድር መጠን እና የውጭ ምንዛሬ ታሳቢ በማድረግ  የ1,397,552.00 ሜ/ቶን አፈር ማዳበሪያ ግዥ ተፈፅሟል፡፡ የከረመውን 220,141.51 ሜ/ቶን ጨምሮ ለምርት ዘመኑ 1,617,693.51 ሜ/ቶን ለተጠቃሚዎች እንደሚቀርብ ታቅዶ በዚሁ መሠረት 859,936.2 (83.7%) ሜ/ቶን የአፈር ማዳበሪያ ወደ ሀገር ውስጥ የቀረበ ሲሆን (አዲስ ከገባና የከረመ ጨምሮ) 965,144.75 (89.3%) ሜ/ቶን  ወደ የክልሎች ተሰራጭቶ ለአ/አደሩም ተሰራጭቷል፡፡

ለበጋ መስኖ ስንዴ ልማት እንዲውል ከኦ.ሲ.ፒ.ኤስ.ኤ (OCP SA) በልገሳ የተገኘውን 50,000 (ሀምሳ ሺህ) ሜ/ቶን ኤን.ፒ.ኤስ. ቦሮን (NPSB) የአፈር ማዳበሪያ ክልሎች የሚያለሙትን የመሬት ስፋት ከግምት ውስጥ በማስገባት ለኦሮሚያ፣ ለአማራ፣ ለደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ለአፋር፣ ለቤንሻንጉል ጉምዝ፣ ለሲዳማ እና ጋምቤላ ክልሎች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

ለምርት ዘመኑ ግብዓት መግዣ ብድር ከክልሎች የተሰበሰበው ፍላጎት 118.078 ቢ/ን ብር ቢሆንም በብሔራዊ ባንክ በኩል የተፈቀደው 56.7 ቢ/ን ብር (48%) እና 1.0 ቢ/ን ዶላር ብቻ ነው፡፡ በተጨማሪም ለትግራይ ክልል 6.245 ቢ/ን እና 0.059 ቢ/ን ዶላር የተፈቀደ ሲሆን ባጠቃላይ 62.945 ቢ/ን ብር (53.3%) እና 1.059 ቢ/ን ዶላር ተፈቅዷል፡፡ የተፈቀደውን የብድር መጠን እና የውጭ ምንዛሬ ከግምት ውስጥ በማስገባት ከላይ የተጠቀሰውን መጠን ያክል ብቻ መግዛት ተችሏል፡፡ በ2015 ለማስመለስ ከታቀደው 33.19 ቢ/ን ብር 37.1 ቢ/ን ብር (147.1%) እንዲመለስ ተደርጓል፡፡

### ምርጥ ዘር አቅርቦት እና ስርጭት

2015/16 ምርት ዘመን የክልሎች የሰብል ምርጥ ዘር ፍላጎት 1,836,832 ኩ/ል የተሰበሰበ ቢሆንም በምርት ዘመኑ 1,500,000 ኩ/ል ቀርቦ 1,000,000 ኩ/ል ለማሰራጨት በዕቅድ ተይዟል፡፡ በፌደራል እና በክልል ዘር አቅራቢዎች የተመረተ ዘር ምርት ግምት 1,796,840.12 ኩ/ል (97.8%) ሲሆን

1,125,235.43 ኩ/ል (62.6%) ዘር ምርት ተሰብስቧል፣ ከዚህ ውስጥም 820,445.7 ኩ/ል (54.7%) ቀርቧል ፣ 622,810.2 (62.3) ተሠራጭቷል። የአቅርቦትና የስርጭት አፈጻጸሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት ተግባሩ እስከ ታህሳስ 2016 ድረስ የሚቀጥል በመሆኑ ነዉ።

### የኖራ አቅርቦትና ስርጭት፤

አሲዳማ መሬትን ለማከም ለ2015/16 ምርት ዘመን የግብርና ኖራ አቅርቦትና ስርጭት የማስፈጸሚያ ስልቶች ላይ ውሳኔ ላይ ለመድረስ እንዲቻል ከአምስት ክልሎች የኖራ አቅርቦትና ስርጭት የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቶ በምርት ዘመን አገልግሎት ላይ የሚውል1,056,804 ኩ/ል ለማቅረብ በእቅድ ተይዞ ወደ ሥራ ተገብቷል። በዚህም ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ሲዳማ እና ደቡብ ምዕራብ ክልሎች በድምሩ 176,421 ኩ/ል ኖራ የቀረበ ሲሆን 150,611 ኩ/ል 85.4% ለአርሶ አደሩ ተሰራጭቷል።

### የፀረ-ተባይ ኬሚካል አቅርቦትና ስርጭት

ለ2015/16 ምርት ዘመን ከክልሎች የተሰበሰበ የአግሮ ኬሚካል ፍላጎት 3,594,613 ሊ/ኪ/ግ የነበረ ሲሆን የኬሚካል አቅርቦትን በተመለከተ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን 30 ሚ/ን ዶላር እና ለኦሮሚያ ህ/ስ/ማ/ፌዴሬሽን 30 ሚ/ን ዶላር ለአምባሰል ኃ/የተ/የግ/ማ 7 ሚ/ን ዶላር እና ለጃራ ሆልዲንግስ አ/ማ 2 ሚ/ን በድምሩ 69 ሚ/ን ተፈቅዶ ኬሚካሎች ወደ ሃገር ውስጥ እንዲያስገቡ ተደርጓል። በዓመቱ 1.5 ሚ/ን/ሊ/ር የተሰበሰበ የክልሎች ፍላጎት ውስጥ 1.3 ሚ/ን ሊትር (86.7%) ማቅረብ ተችሏል።

### የእንስሳት ጤና ግብዓት አቅርቦትና ስርጭት

በ2015 በጀት ዓመት 160 ሚ/ን ዶዝ የድንበር ዘለል በሽታ መከላከያ ክትባት ለማቅረብ ታቅዶ የነበረ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 145.6 ሚ/ን ዶዝ የቀረበና የተሰራጨ ሲሆን አፈጻጸሙ 91% ነው። ድንበር ዘለል ላልሆኑ የእንስሳት በሽታ መከላከያ ክትባት 50 ሚ/ን ዶዝ ለማቅረብ ታቅዶ የነበረ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በዓመቱ ለማቅረብና ለማሰራጨት ከታቀደው ውስጥ 45.3 ሚ/ን ዶዝ የቀረበና የተሰራጨ ሲሆን አፈጻጸሙ 90.6% ነው። አንድ መቶ (100) ሺ.ህ ዶዝ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላፉ በሽታዎች ክትባት ታቅዶ የነበረ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በዓመቱ ለማቅረብና ለማሰራጨት ከታቀደው ውስጥ 214 ሺ.ህ ዶዝ ቀርቦ የተሰራጨ ሲሆን አፈጻጸሙም 214% ነው።

### የእንስሳት ግብዓት አቅርቦት እና ስርጭት

በአመቱ የአንድ ቀን የዶሮ ጫጩት 34.49 ሚ/ን ለማቅረብ ታቅዶ 35.5 ሚ/ን (100+%) ቀርቦ የተሰራጨ ሲሆን የ45 ቀን ቄብ 21.5 ሚ/ን ለማቅረብ ታቅዶ 26.3 ሚ/ን (100+%) ቀርቧል፤ የንብ-ህብር በቁጥር 55,801 ለማቅረብ ታቅዶ 105,049 (100+%) የቀረበ ሲሆን የሽግግር ቀፎ 81,625

ለማቅረብ ታቅዶ 116,730 (100+%) እንዲሁም ዘመናዊ ቀፎ 366,126 ቁጥር ታቅዶ 291,697 (79.7%) ቀርቧል፡፡ የሐር ትል 1,240,303 በቁጥር ታቅዶ 1,139,503 (91.9%) ቀርቧል:: የአሳ ጫጩት 1.79 ሚ/ን ለማቅረብ ታቅዶ 942,761 (52.6%) ቀርቧል፤ የእንስሳት መኖ ዘር 2,754.5 ቶን ለማቅረብ ታቅዶ 2,833.8 ቶን (100+%) ቀርቧል፤ የተቀነባበረ የእንስሳት መኖ 260,445 ቶን ለማቅረብ ታቅዶ 162,566.1 (62.42%) ቀርቧል፤ አባለዘር 1.3 ሚ/ን ዶዝ ለማቅረብ ታቅዶ 1.44 ሚ/ን ዶዝ (100+%) ቀርቧል፤ ፈሳሽ ናይትሮጂን 341,500 ሊ/ር ለማቅረብ ታቅዶ 220,900 (64%) ቀርቧል፤ ክልስ ጊደር 922 ለማቅረብ ታቅዶ 685 (74.2%) ቀርቧል፤ ክልስ ኮርማ 232 ለማቅረብ ታቅዶ 314 (100+%) ቀርቧል፣ የተዳቀለ የበግ ኮርማ 16,638 ለማቅረብ ታቅዶ 17,656 (100+%) ቀርቧል፤ የተዳቀለ የፍየል ኮርማ 19,119 ለማቅረብ ታቅዶ 4803 (25%) ቀርቧል፤ የማድረያ (ሲንክሮናይዚንግ) ሆርሞን 359,490 ዶዝ ለማቅረብ ታቅዶ 280,646 ዶዝ (78%) ቀርቧል::

## 8.4 የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት

በበጋ መስኖ የስንዴ ማሳ 563,000 ሄ/ር መሬት ከተዘጋጀው፣ 156,325 ሄ/ር መሬት በመስመር መዝሪያ የተዘራ ሲሆን 113,725 ሄ/ር ምርት የበልግ ምርት ስብሰባ በኮምባይነር ለማከናወን ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በሀገር ደረጃ በመካሄድ ላለው መስኖ ስንዴ ልማት ስራዎች ላይ ባለሙያዎችን በመመደብ የማሽነሪ አጠቃቀም እና አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ ላይ ቴክኒካል ድጋፍ ተደርጓል::

በተለያዩ የቅድመ ምርት እና ድህረ ምርት ማሽነሪዎች ላይ በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ ምእራብ፣ በሶማሊ፣ ኦሮሚያ፣ በአማራ ክልሎች በትራክተሮች እና ሌሎች ቴክኖሎጂዎችና አቅርቦትና ቴክኒካል ድጋፍ በመስጠት 1,066 ትራክተሮች፣ 3,201 የድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎች (ኮምባይነሮች፣ ሁለገብ መውቂያዎችን እና መፈልፈያዎችን የመሳሰሉት) በግል ባለሀብቶች፣ መንግስትታዊ ድርጅቶች አቅራቢዎች፣ በማህበራትና በአምራች ድርጅቶች በኩል እንዲቀርብ ድጋፍ ተደርጓል:: እንዲሁም 50,000 የመስኖ ፓምፖች እንዲቀርቡ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ታቅዶ 49,283 ፓምፖች (80%) በማቅረብ አርሶ አደሩን ተጠቃሚ ለማድረግ ተችሏል፡፡

የእርሻ መሣሪያዎች የኪራይ አገልግሎት ትሥሥርን በተመለከተ 702 ትራክተሮች የኪራይ አገልግሎት አቅርቦትና ትስስር እንዲፈጠር ታቅዶ 834 ትራክተሮች (100+%) የኪራይ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል::

ለግብርና አገልግሎት የሚውሉ የግብርና ሜካናይዜሽን ማሽነሪዎች፣ ቴክኖሎጂዎች እና እቃዎች-- ትራክተር ከነተቀጽላዎች፣ ኮምባይነር እና ሁለገብ መውቂያ፣ ቤለር፣ እንኩቤተር፣ የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ፣ የቡና መፈልፈያ ከአክሰሰሪው፣ የውሃ ፓምፖች ከነአክሰሰሪ፣ የወተት ማለቢያ ከአክሰሰሪው፣ ስፕሬየር እና ሌሎች ለግብርና አገልግሎት የሚውሉ ማሽነሪዎች ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ

በ137 አስመጪዎች በኩል በድምሩ በቁጥር 1,221,718 ቴክኖሎጂዎች እና መለዋወጫዎች ከቀረጽ ነጻ እንዲገቡ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

በክልል ለሚገኙ ማሽነሪ ኦፕሬተሮች፣ በመስኖ ፓምፖች አጠቃቀም እና ጥገና ዙሪያ ለ392 ባለሙያዎች፣ ኦፕሬተሮች፣ እና ጥገና ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰቷል:: ከስራና ክህሎት ሚኒስቴር እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በዘርፉ ከፍተኛ ልምድና ዕውቀት ያላቸውን ባለሙያዎች በማሳተፍ በማሽነሪ ኦፕሬሽንና ማሽነሪ ጥገና ከሌቭል 1-4 የሙያ ደረጃ እና ካሪኩለም ለማዘጋጀት ተችሏል፡፡

በኮሪያ መንግስት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በቁጥር አንድ የሜካናይዜሽን ልህቀት እና ፍተሻ ማእከል ለማቋቋም ታቅዶ የተቋም ግንባታ ቦታ ማዘጋጀት እና የዲዛይን ማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም ለ71 ባለሙያዎች የክህሎት ስልጠና ከኮሪያ በመጡ አሰልጣኞች እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

## 9. ህብረት ስራ ማህበራት

የኅብረት ሥራ ማህበራትን ከማጠናከርና ከማዘመን አንጻር የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት እድገት በገጠር 52 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ 52 በመቶ ማድረስ ተችሏል፡፡ አዳዲስ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትን በማደራጀት እና ነባሮችን በማጠናከር አዳዲስ አባላትን ማፍራት በዓመቱ 1.7 ሚ/ን (ወንድ 850,000 ሴት 850,000 ከዚህ ውስጥ ወጣት 200,000) ታቅዶ በክንዉን ደረጃ 1,919,617 (ወንድ1,191,809 (ከ100% በላይ)፣ሴት 727,808 (85.6%) ከዚህ ውስጥ ወጣት 255,641 (ከ100% በላይ)) የተከናወነ ሲሆን ከክንዉኑም በአባላት ተሳትፎ በወንድ 62.1%፣ በሴት አባላት ተሳትፎ 37.9% ማከናወን ተችሏል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት በገጠርም ሆነ በከተማ የሚኖረውን የሕብረተሰብ ክፍል የቁጠባ ባህል እንዲዳብርና የአባላቱ ገቢ እንዲጨምርም ሆነ የአገር ኢኮኖሚ ግንባታ እንዲያድግ የሚያደርገው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ በፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰበሰበው የቁጠባ መጠን በ2014 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት ብር 24.5 ቢሊዮን በ 5 ቢሊዮን በማሳደግ በ2015 ዓ.ም መጨረሻ ወደ ብር 29.5 ቢሊዮን ለማድረስ ግብ የታጣለ ሲሆን 5 ቢሊዮን ለማስቆጠብ ታቅዶ ብር 9.31 ቢ/ን ብር በመሰብሰብ ከ100% በላይ ማከናወን ተችሏል ፡፡

በፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት ለአባላት የሚቀርበውን የብድር መጠን በ2014 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት ብር 28.85 ቢሊዮን በ6 ቢሊዮን በማሳደግ በ2015 ዓ.ም መጨረሻ ወደ ብር 32.85 ቢሊዮን ለማድረስ ግብ የተጣለ ሲሆን ዓመቱ 6 ቢሊዮን ለማሰራጨት ታቅዶ በክንዉን ደረጃ ብር **15.75** በማሰራጨት ከዕቅዱ ጋር ሲነፃፀር 100+% በላይ ማከናወን ተችሏል:: በዚህም ከ577,767 አባላት በላይ ብድር አሰራጭተው በተለያዩ የልማት ሥራዎች ላይ ውሏል፡፡

በአጠቃላይ የኅብረት ሥራ ማህበራትን በተሰማሩበት ዘርፍ ጠንካራ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የውስጥ የካፒታል አቅማቸዉን ለማሳደግ የማጠናከር ሥራ በመስራት እንዲሁም አዳዲስ ኅብረት ሥራ ማህበራት በጠንካራ የካፒታል አቅም ለማቋቋም በዓመቱ ብር 2,280,000,000 የካፒታል አቅማቸዉን ማሳደግ ታቅዶ በክንዉኑም በብር 4,743,961,799.21 አቅማቸዉን ማሳደግ የተቻለ ሲሆን አፈጻጸሙም ከዕቅዱ (100%) በላይ ማከናወን ተችሏል ፡፡ አፈጻጸሙም ከፍተኛ ሊሆን የቻለው በ4ኛ ሩብ ዓመት የተደራጁ ማህበራት ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑና የውስጥ ካፒታል የማመንጨት አቅማቸው የጨመረ በመሆኑ ነው፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራትን የአገር ውስጥ የግብርና ምርት የግብይት ተሳትፎ እና ድርሻ ለማሳደግ በ2014 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 22.3 ከመቶ በ2015 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 28 በመቶ ለማድረስ ግብ የተጣለና የግብርና ምርቶችን ለአገር ውስጥ ገበያ በማቅረብ በዓመቱ 1,720,000 ሚሊዮን ቶን ለማቅረብ ታቅዶ ክንዉን 1,804,923.51 ሺህ ቶን ምርት ለአገር ዉስጥ ግብይት በማቅረብ የዕቅዱን 100% በላይን ማከናወን ተችሏል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራትን የውጭ ግብይት ድርሻ በ2014 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት በመጠን 7% ከነማካካሻው በዓመቱ 16 በመቶኛ ፣ በዶላር (በገቢ) 17 በመቶኛ ገቢ ለማስገኘት ታቅዶ በክንዉኑም የእቅድ አፈጻጸሙ በምርት መጠን 22.9% እና በተገኘ ገቢ ከዶላር ግኝት አንጻር 36.1% ማከናወን ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብይት ተሳትፎ እና ድርሻ በማሳደግ በኅብረት ሥራ ማህበራት ቀርቦ የሚሠራጨውን የአፈር ማዳበሪያ ግብዓት ስርጭት ድርሻ በ2014 ከደረሰበት 98.35% ወደ 100% ማቅረብ ችሏል፡፡ በዚህም መሰረት 2014/15 ምርት ዘመን የተሰራጨ ማዳበሪያ 1,386,851.55 ሜ/ቶን ከዚህ ውስጥ 542,573.44 ሜ/ቶን ማዳበሪያ በኅብረት ስራ ማህበራት እንዲሰራጭ የተለያዩ ድጋፎች ተደርገዋል፡፡

የውጭ ግብይት የእቅድ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት የምርት ግዥ ዋጋ ከፍተኛ መሆን እና የአለም ዋጋ ጋር መወዳደር አለመቻል፣ ቡና እና ሌሎችም ምርቶች በሚሰበሰቡበት ወቅት ለመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት በወቅቱ ፋይናንስ አለመልስጠት እና ምርት አለመሰብሰብ ያላቸውም የግብይት ግንኙነት ደካማ መሆን፣ የአገር ውስጥ ያለው የዋጋ ግሽበት ወደ ውጭ የሚወጡ ምርቶች ላይ ከፍተኛ ተጽኖ ማሳደሩ፣ የውጭ ግብይት አሰራር ሂደት ረጅም እና ከፍተኛ ወጭ እና ጊዜ የሚጠይቅ መሆኑ፣ ባለልዩ ጣዕም የሀረር ቡና ገዥዎች ፍላጎት በመጥፋቱ ይህን የሚልኩ ኅብረት ስራ ማኀበራት ከገበያ መውጣት እና ሰላም ዕጦት በአብዛኛው የሃገሪቱ ክፍሎች ላይ መኖሩና ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ውጤታማነትን ከማሳደግ እና ከማስፋፋት አኳያ አርሶ አደሩ ያመረተውን ምርት እሴት ለመጨመር የግብርና ኅብረት ሥራ ማህበራት የአካባቢያቸውን ፀጋ መሠረት አድርገው የሚያቋቁሟቸውን የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ቁጥር በ2014 ከተደረሰበት 1,719 በቁጥር በ74 በማሳደግ በ2015 በጀት ዓመት መጨረሻ ወደ 1,793 ለማድረስ በዓመቱ 74 የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች 74 ማቋቋም ታቅዶ በሲዳማ ክልል 87 የእርጥብ ቡና መፈልፈያ ኢንዱስትሪዎች ፤1 ማዳበሪያ ከረጥት ፋብሪካ የወተት ተዋፅኦ ማቀነባበሪያ 1 የማር ማቀነባበሪያ 1 የመኖ ማቀነባበሪያ 1 ዘር ማበጠሪያ 3 በድምሩ 7 እና በኦሮሚያ ክልል 1 የመኖ ማቀነባበሪያ 15 የእርጥብ (ቀይ) ቡና መፈልፈያ በድምሩም 120 ኢንዱስትሪዎች ማቋቋም ተችሏል፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ከመፍታት ባሻገር አሁን ከደረሱበት የዕድገት ደረጃ በጊዜአዊነትና በቋሚነት ለዜጎች ዋና የሥራ ዕድል መፍጠሪያ ተቋማት ናቸው፡፡ አባላት የሚወስዱት ብድር ለልማት ሥራዎች በማዋል የሥራ እድል ለመፍጠር በበጀት ዓመቱ ለ1.2 ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ በክንዉኑም 528,724 ዜጎች (ወንድ 340,214 ሴት 188,510) ዜጎች በላይ የሥራ ዕድል መፍጠር የተቻለ ሲሆን በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ በኅ/ሥራ ማህበራት ለ 49,331 ዜጎች ቋሚ የስራ እድል ለመፍጠር ተችሏል፡፡

## 10. ግብርና ምርምር

ከምርምር ሙከራዎች አንጻር በ2015 የበጀት ዓመት 2,213 የምርምር ሙከራዎችን ለመተግበር ታቅዶ በበጀት ዓመቱ ውስጥ 2,175 (98 በመቶ) ሙከራዎች ተካሂደዋል፡፡ ከተካሄዱት ውስጥ 905ቱ የተጠናቀቁ ሲሆን የቀሩት በምርምር ስራው የቀጣይነት ባህርይ ምክንያት በሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡ በቴክኖሎጂ አቅርቦት 513 (91 በመቶ) የምርምር ውጤቶች (ቴክኖሎጂዎችና መረጃዎች) ተገኝተዋል፡: በምርምር የፈለቁ ቴክኖሎጂዎችን ተደራሽ ለማድረግ ለ21,709 የልማት ተሳታፊ አካላት የማስተዋወቅ እና ለ13,847 የልማት ተሳታፊ አካላት የማስፋት ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ የተለያዩ የምርምር ጽሁፎችን የማዘጋጀትና ለተጠቃሚው ተደራሽ የማድረግ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡ በሌላ በኩል የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎችን ክህሎት ለማሳደግ ለ23,796 አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮች፣ የልማት ጣቢያ ሠራተኞች፣ የግብርና ባለሙያዎች፣ የዘር አባዦች፣ የግል ባለሀብቶች እና ከተለያዩ የልማት ድርጅቶች ለተውጣጡ አካላት የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፡፡

ቴክኖሎጂዎች ለወደፊቱ ተጠብቀው እንዲቆዩ እንዲሁም ለተጠቃሚዎች እንዲተላለፉ በበጀት ዓመቱ በሰብል ዘርፍ (በብርዕና አገዳ፣ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ስራስር፣ መዓዛማና መድሃኒታማ እና ቡና) በአራቢ፣ በቅድመ-መስራች እና በመስራች ደረጃዎች 12,427 ኩንታል ዘር እና 3,232,664 ችግኞች ማባዛት ተችሏል፡፡

በእንስሳት ምርምር ዘርፍ 141 የወተት ላሞች፣ 179 ጊደሮች፣ 28 ኮርማዎች፣ 586 በግና ፍየሎች፣ 97,846 የ1 ቀን የዶሮ ጫጩቶች፣ 1,095,900 የዓሳ ጫጩቶች፣ 1,795 እንቁላል ጣይ የሐር ቢራቢሮዎች፣ 80 እናት ንቦች ተባዝተዋል። በእንስሳት መኖ ብዜትም 415.12 ኩንታል ዘር እና 8,685,220 ችግኞች ተባዝተዋል።

በተፈጥሮ ሃብት አያያዝ ልማት 6,660 ፓኬት የራይዞቢያ ሕየው-ማዳበሪያ፣ 2.83 ኩንታል የኮምፖስት ትል እና 367 ኩንታል ቨርሚ ኮምፖስት (የተፈጥሮ ማዳበሪያ) ተባዝቷል። በተጨማሪም በዘርፍ ዘለል ፕሮግራም 228 የተሻሻሉ የእርሻ መሣሪያዎች ተባዝተዋል።

ኢንስቲትዩቱ በክልልና ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እንዲሁም ከሌሎች የአገር ወስጥ የምርምር አጋሮች ጋር 243 የምርምር ጥናቶች እንዲከናወኑ በማድረግ በጋራ የመስራት ስራዎች ተከናውነዋል። ለተለያዩ ክልሎች (ሲዳማ፣ ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ ደቡብ ህዝቦች፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ) ፣ ለከ1ኛ እስከ 3ኛ ዲግሪ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እና ለተለያዩ የልማት አጋሮች ከግብርና ምርምርና ልማት ጋር የተያያዘ ሙያዊ ድጋፍ ተደርጓል።

## 11. የግብርና ትራንስፎርሜሽን

### የአርሶ አደር ሰብል ምርት ክለስተር

በአምስቱም ክልሎች (ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደ/ብ/ብ/ሕ/፣ ሲዳማ እና ደቡብ-ምዕራብ ኢትዮጵያ) ለመምረጥ ከታቀዱት 262 ሞዴል የአርሶ-አደር ምርት ክለስተሮች በኦሮሚያ 125፣ አማራ 82 እና የ3ቱ ደቡብ ክልሎች 55 ውስጥ በሙሉ ተለይተውና ተመርጠው የተጠናቀቁ ሲሆን ከጠቅላላዎቹ 253 የሚሆኑት ዕውቅና አግኝተው የምርት ክለስተሩ ሥራ በአግባቡ እየተከናወነ ይገኛል። እነዚ የተመረጡ ሞዴል የአርሶ-አደር ምርት ክለስተሮች በአምስቱ የግብርና ኮመርሻላይዜሽን ክለስተር ዋና ዋና ሰብሎች ስንዴ፣ በቆሎ፣ ቢራ-ገብስ፣ ጤፍና ሰሊጥ እየተከናወነ ይገኛል።

በምርት ዘመኑ አርሶ አደሮች በ85 ሺህ የአርሶ አደር የምርት ክለስተር ተደራጅተው በሰብል ለመሸፈን ከታቀደው 1.5 ሚሊዮን ሄ/ር በ6.6 በመቶ ጭማሪ በመሳየት በ1.6 ሚሊዮን ሄ/ር ማሳ ላይ በዋና ዋና ሰብሎች ተሸፍነዋል። በምርት ዘመኑ ከታቀደው 2.3 ሚሊዮን የአርሶ አደሮች ቁጥር ውስጥ 96 በመቶ (2.2 ሚሊዮን) አርሶ አደሮች ተሳትፈዋል። ከታቀደው የአርሶ አደሮች ቁጥር 83 በመቶ (1.9 ሚሊዮን) የሚሆኑ አርሶ አደሮች የምርጥ ዘር ተጠቃሚ ሲሆኑ 2.1 ሚሊዮን (91 በመቶ) የሚሆኑ ደግሞ የአፈር ማዳበሪያ ተጠቃሚ ሆነዋል። በምርት ዘመኑ ከታቀደው 899 ሺህ ኩንታል ምርጥ ዘር 11 በመቶ ጭማሪ በማድረግ 1 ሚሊዮን ኩንታል ምርጥ ዘር ጥቅም ላይ ውሏል። እንዲሁም ከታቀደው 4.9 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ (70 በመቶ ዩሪያ እና 100 በመቶ NPS) ውስጥ 4 ሚሊዮን ኩንታል (82 በመቶ) የሚሆን ጥቅም ላይ ውሏል። የተለያዩ የሜካነናይዜሽን አገልግሎት ተጠቃሚ

ይሆናሉ ተብለው ከታቀዱት 630 ሺህ አ/አደሮች ዉስጥ 731 ሺህ (100% በላይ) የሚሆኑ ተጠቃሚ ሆነዋል።

**የአርሶ አደር በአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ክለስተር**

በደ/ብ/ብ፣ በሲዳማ እና በኦሮሚያ ክልሎች 62 ተሳታፊዎች (35 አርሶ አደሮች፣ 10 የልማት ሰራተኞች እና 17 ባለሙያዎች) በአትክልትና ፍራፍሬ አምራችና ላኪ ድርጅቶች፣ የተሻሻለ አትክልትና ፍራፍሬ አመራረት፣ እሴት መጨመር ላይ የልምድ ልውውጥ ተካሂዷል። በአትክልትና ፍራፍሬ የአርሶ አደር ምርት ክለስተር በአራቱ ክልሎች 78,100 አርሶ አደሮችን በ1,380 ክለስተር ተደራጅተው 18,600 ሄክታር ማሳ ላይ እንክብካቤ እያደረጉ ይገኛሉ።

የተደራጁትን የአርሶ አደር ምርት ክለስተር የዕሴት ሰንሰለቶች አደረጃጀትና ሌሎች የገበያ ትስስር ዘዴዎችን በመጠቀም በዓመቱ ከታሰበው የአትክልትና ፍራፍሬዎች የገበያ ትስስርን የማሻሻል ሥራዎች ዉስጥ በዓመቱ ዉስጥ በዕቅዱ መሠረት 25 በመቶውን ለማከናወን የታቀደ ሲሆን 25 በመቶውን ለማከናወን ተችሏል።

በደ/ብ/ብ፣ በሲዳማ፣ በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች አትክልትና ፍራፍሬ የግብርና ኮመርሻላይዜሽን ክለስተር 24,900 ሄክታር ማሳ ላይ 20.5 ሚ/ን ኩንታል የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ተሰብስቧል።

ገበያ ትስስር የተደረገለት የእህል ምርት በኩንታል በተመለከተ 41.3 ሚ/ን ኩ/ል ታቅዶ 39.2 ሚ/ን ኩ/ል (95 በመቶኛ) ተከናውኗል። በተመሳሳይ 18.15 ሚ/ን ኩ/ል የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት የገበያ ትስስር ለማድረግ ታቅዶ 15.16 ሚ/ን ኩ/ል (84 በመቶኛ) ተከናውኗል።

## 12. የግብርና ቁጥጥር ስራዎች

### 12.1 ግብርና ቴክኖሎጂ ቁጥጥር

#### 12.1.1 የእንስሳት ቴክኖሎጂ ቁጥጥር

**በእንስሳት ልየታና ምዝገባ ስርዓት ስር የሚያልፉ ለኤክስፖርት የሚቀርቡ የእንስሳት ቁጥር**

በበጀት ዓመቱ በእንስሳት ልየታና ምዝገባ ስርዓት ስር የሚያልፉ የዳልጋ ከብቶች ቁጥር 18,000 ለማድረስ ታቅዶ 16,264 (90%) ለማከናወን ተችሏል። 80 የእንስሳት ምዝገባ ስርዓት በዳልጋ ከብቶች የቁም ኤክስፖርት ላይ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ በማድረግ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚገኙ ባለድርሻ አካላት እንዲሳተፉ በማድረግ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ በ75 (90%) ባለድርሻዎች ላይ ተግባራዊ ለማድረግ ተችሏል። በእንስሳት ልየታና ምዝገባ ስርዓት ስር የሚያልፉ

በጎችና ፍየሎችን ቁጥር 78,000 ለማድረስ ታቅዶ ማከናወን አልተቻለም፡፡ በተመሳሳይ የተሳታፊና ተጠቃሚ የበግና ፍየል ኤክስፖርተሮች ቁጥር ከ0 ወደ 28 ለማሳደግ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም ስራውን ሊያግዝ የሚችል የልማት ክንፍ ባለመኖሩ፣ እንዲሁም የጆሮ መለያዎች የሲስተም ዲዛይን ስራ ባለማለቁ እንዲሁም የአፕሊኬተር ሞዲፊኬሽን ስራ መጠናቀቅ ባለመቻሉ፣ በማድለቢያ ውስጥ የበጎችና ፍየሎች ቆይታ ጊዜ አጭር በመሆኑና በሂደት ላይ ያለውን ስራ (በመዋቅራዊ ለውጥ ምክንያት ስራው የሚወስድ የስራ ክፍል ባለመኖሩ) ለማከናወን አልተቻለም፡፡

### 12.1.2 የሰብል ቴክኖሎጂ ቁጥጥር

100 የሰብል ዝርያዎችን በመስክ እንዲገመገሙ ለማስተባበር እና ለመገምገም ታቅዶ 119 የሰብል ዝርያዎችን በመስክ እንዲገመገሙ ለማስተባበር እና ለመገምገም ተችሏል፡፡

## 12.2 የግብርና አገልግሎት ቁጥጥር

### 12.2.1 በኳራንቲን የቁጥጥር ስርአት ውስጥ አልፈው የእንስሳት ጤና ሰርቲፍኬት የሚሰጣቸው የቁም እንስሳት ብዛት

በበጀት ዓመቱ ለኤክስፖርት የቀረቡ ለ18,000 የዳልጋ ከብቶች የኢንስፔክሽን እና ሰርቲፍኬሽን ለማድረግ ታቅዶ ለ18,115 (>100%) የዳልጋ ከብቶች ምርመራ ተደርጎላቸው ወደ ተቀባይ ሃገሮች እንዲላኩ ተደርጓል፡፡ ለውጪ ገበያ ለሚቀርቡ 78,000 በግና ፍየል ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ ለ70,545 (90.44%) በግና ፍየል ጤና ምርመራ እና የኳራንቲን ጊዜአቸውን ጨረሰው እንዲላኩ ተደርጓል፡፡ ለ13 ሺህ ግመሎች የኢንስፔክሽን እና ሰርቲፍኬሽን እንዲሁም የክትባት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ4,721 (26.2%) ግመሎች የክትባት አገልግሎት አግኝተውና የተቀባይ ሀገራትን መስፈርት አሟልተው እንዲወጡ ተደርጓል፡፡

ከውጪ ሃገር ወደ ሃገር ውሥጥ ለሚገቡ የአንድ ቀን ጫጩቶች 600,000 ምርመራ እና የዶክመንት ማጣራት ተድርጎ በቦሌ ኳራንቲን ጣቢያ ወደ ሀገር ለሚገቡ የመግቢያ ፍቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ1,569,500 የአንድ ቀን ጫጩቶች ዶክመንት ማጣራት ተደርጎ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ ከውጪ ለሚገባ የለማ እንቁላል ለ500,000 ምርመራ እና የዶክመንት ማጣራት ተድርጎ በቦሌ ኳራንቲን ጣቢያ ወደ ሀገር ለሚገቡ የመግቢያ ፍቃድ ለመስጠት ታቅዶ 439,400 የለማ እንቁላል ዶክመንት ማጣራት ተደርጎ እንዲገቡ ተደርጓል:: እቅድ ከክንውን አንጻር 87.88 % ተከናውኗል፡፡

### 12.2.2 የቅድመና ድህረ ዕርድ ምርመራ የተደረገላቸው የቁም እንስሳት

ለ2.18 ሚ/ን የቁም እንስሳት ቅድመ ዕርድ ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ በድምሩ ለ1.77 ሚልየን የቁም እንስሳት (81%) ምርመራው ተከናውኗል፡፡ ምርመራው ከተደረገላቸው የቁም እንስሳት መካከል

ምርመራውን፦ ለ27.07 ሺህ ዳልጋ ከብት ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ ለ11.5 ሺህ (70.7%) ለ 2.281 ሚ/ን በበጎች ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ 140.8 (49%); ለ1.614 ሚ/ን ፍየሎች ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ 1.225 ሚ/ን (71%) ለማድረግ የተቻለ ሲሆን ከተመረመሩት የቁም እንስሳት መካከል በአጠቃላይ 133.87 ሺህ (9.9%) እንስሳት በቅድመ እርድ ምርመራው ውድቅ ተደርገዋል፡፡

ለ1.9 ሚ/ን የታረዱ እንስሳት ድህረ እርድ ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ በ1.3 ሚ/ን የታረዱ እንስሳት (68.42%) ላይ ምርመራው ተከናውኗል፡፡ ምርመራው ከተደረገላቸው የታረዱ እንስሳት መካከል ለ25.93 ሺህ በጎች ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ በ11.43 ሺህ በጎች (44%) ላይ; በ1.71 ሚ/ን ፍየሎች ላይ ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ በ1.18 ሚ/ን (69%) ምርመራው ተደርጓል፡፡ በድህረ እርድ ምርመራ ከተመረመሩት ውስጥ በድምሩ 85.5 ሺህ (5%) ውድቅ ተደርጓል፡፡

## 12.3 የግብርና ምርት ቁጥጥር

### 12.3.1 የእንስሳት ምርት ቁጥጥር

**ደህንነቱና ጥራቱ የተጠበቀ ሥጋና ተረፈ ሥጋ ምርት ተመርቶ ለውጭ ገበያ እንዲላክ የኢንስፔክሽን አገልግሎት መስጠት፣** ለወጭ ገበያ እና ለሰው ምግብነት የሚቀርበው ስጋ ጤንነቱ፣ ደህንነቱና ጥራቱን የጠበቀ የስጋ መሆኑን ለማረጋገጥ የቅድመ ዕርድና ድህረ እርድ ምርመራ በማከናወንና፣ የቄራዎችን ሀይጅንና ሳኒቴሽን እንዲጠበቅ ለመቆጣጠር የኢንስፔክሽን አገልግሎት ከመስጠት በተጨማሪ በላቦራቶሪ ምርመራ እየተደረገ ሲሆን በድምሩ ለ28,000 ቶን የበግ፣ የፍየልና፣ የዳልጋ ከብት ስጋ ምርት ለኤክስፖርትና ለሀገር ውስጥ ምግብነት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ በድምሩ 14,569.55 ስጋ እና ተረፈ ስጋ ወይም የእቅዱ 52% ደህንነቱ ተረጋግጦ እንዲላክ ተደርጓል፡፡ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ለ2,600 ቶን የበግ ስጋ ብቁ መሆኑን በማረጋገጥ ለመላክ ታቅዶ 787.5 ቶን ስጋ 30.2% ተልኳል; ለ17,500 ቶን የፍየል ስጋ ብቁ መሆኑ ተረጋግጦ እንዲላክ ታቅዶ 8,715 (49.8%) ተከናውኗል; 4,000 ቶን የዳልጋ ከብት ስጋ ብቁ መሆኑ ተረጋግጦ እንዲላክ ታቅዶ 711.8 የእቅዱ 17.8% ቶን ስጋ ተልኳል; 3,900 ቶን ተረፈ ስጋ ብቁ መሆኑ ተረጋግጦ እንዲላክ ታቅዶ 4,347.91 ቶን (111.49%) ተረፈ ስጋ ተልኳል፡; የሥጋ ምርት የመድኃኒት ቅሪት ምርመራን በተመለከተ 150 ታቅዶ ከ4 የሥጋ ምርት ኤክስፖርት ቄራ ድርጅቶች በተሰበሰበው 144 የሥጋ ምርት ናሙናዎች ላይ በተያዘው ዕቅድ መሰረት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

**በኳራንቲን የቁጥጥር ስርዓት ውስጥ ያለፉ** ለ200 ቶን ለኤክስፖርት የተዘጋጀ ሰም ጥራቱን አረጋግጦ ሰርቲፍኬት ለመስጠት ታቅዶ ለ357.057 ቶን ሰም (100+%) ኢንስፔክሽንና ሰርቲፍኬሽን አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡ 200 ቶን ማር የኢንስፔክሽንና ሰርቲፍኬሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 179 ቶን ማር

ጥራቱ እና ደህንነቱ ተረጋግጦ የተላከ ሲሆን ክንውኑ በመቶኛ 89.5% ሆኗል፡፡ የሐሞት ጠጠር 200 ኪ.ግ የኢንስፔክሽንና ሰርተፍኬሽን ለመስጠት ታቅዶ 36 ኪ.ግ ሰርተፍኬት ተሰጥቷል፡፡ ይህም 14.2 በመቶ ከታቀደው ተከናውኗል፡፡ ከእንስሳት ውጤቶች መካከል አንዱ ቆዳና ሌጦ ሲሆን ለ2 ሚ/ን የበግና ፍየል ቆዳ የኢንስፔክሽንና ሰርተፍኬሽን አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ ለ2.05 ሚ/ን ሰርቲፍኬሽን የተሰጠ ሲሆን እቅድ ከክንውን አንጻር 100% ተከናውኗል፡፡

ለመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ኤክስፖርት ለሚደረግ በቦሌ ኳራንቲን ጣቢያ በኩል የመልቃቂያ ፍቃድ ለ22,689.08 ቶን ስጋ በቦሌ ኳራንቲን ጣቢያ ምርመራ ለማድረግ ታቅዶ ለ14,569.55 ቶን ስጋ የይለፍ ፍቃድ የተሰጠ ሲሆን ይህም እቅድ ከክንውን አንጻር 52 በመቶ ተከናወኗል፡፡ በእንስሳት ምርት (ሥጋ፣ወተትና ማር) በ400 ናሙናዎች ላይ የላቦራቶሪ ጥራትና ደህንነት ምርመራ ሥራ ለማካሄድ ታቅዶ በ570 (124.5%) ናሙናዎች ላይ ምርመራ ለማድረግ ተችሏል፡፡

### 12.3.2 የዕጽዋት ምርት ቁጥጥር

ወደ ውጭ ለሚላኩ ለ1,550,000 ቶን ዕጽዋትና፣ የዕፅዋት ዉጤቶች ጤንነትና ጥራታቸዉን ጠብቀዉ እንዲወጡ የመስክ እና ላብራቶሪ ምርመራ ለማከናወን ታቅዶ ለ1,010,029 (65%) ቶን ዕጽዋትና፣ የዕፅዋት ዉጤቶች ላይ የመስክ እና ላብራቶሪ ምርመራ ለማከናወን ተችሏል፡፡
ወደ ውጭ የሚላኩ ሰብል ምርቶች ተቀባይነታቸውን ማሳደግ እና የተቀባይ ሃገራትን ቅሬታ (Notification) መቀነስ፣ ተቀባይነትን በማሳደግ 100% ለማድረስ ታቅዶ 98% ማድረስ ተችሏል፡፡ ለውጭ ገበያ በሚቀርቡ በተመረጡ በ350,000 ቶን የግብርና ምርቶች ላይ የማዕጠንት /Fumigation/ ክትትል ለማድረግ ታቅዶ ለ218,849 ቶን (63%) ቶን ምርቶች ላይ ክትትል ለማድረግ ተችሏል፡፡ ክንውኑ ያነሰው ወደ ዉጪ የሚላክ ምርት አቅርቦት አናሳ በመሆኑ ነው፡፡
ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ ዕፅዋት፣ የዕፅዋት ውጤቶችና ሌሎች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ቁሳቁሶች 1,953 የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ ለመስጠት፣ ታቅዶ ለ1,953 የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ 85,700 ቶን ዕጽዋት እና የዕፅዋት ውጤቶች በመግቢያ መስፈርታቸዉ መሰረት ስለመግባታቸዉ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ 59,672 (70%) ቶን ምርቶች ላይ ምርመራ ለማድረግ ተችሏል፡፡ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ ዕፅዋትና የዕፅዋት ዉጤቶች 4 ጊዜ የተባይ ስጋት ትንተና፣ ድህረ መግባት ክትትል እና የመስክ የዳሰሳ ጥናት ለማድረግ ታቅዶ 4 ጊዜ ተከናውኗል፡፡

## 12.4 የግብርና ግብዓት ቁጥጥር

### 12.4.1. የዕጽዋት ግብዓት ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር

የዘር ጥራት ቁጥጥር ጥያቄ ለሚያቀርቡ 25 ዘር አስመጪዎች አምራቾችና አዘጋጅዎች የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠትና ለማደስ ታቅዶ ለ28 (100⁺%) ዘር አስመጪዎች አምራቾችና አዘጋጅዎች የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠትና ለማደስ ተችሏል፡፡ ከውጪ ዘር በሚያመጡና በሚያከፋፍሉ 5 ኩባንያዎች ላይ ድንገተኛ ፍተሻ ለማካሄድ ታቅዶ በ2 ኩባንያዎች ላይ ለማከናወን ተችሏል፡፡ 200 ናሙናዎችን በማምጣት የላብራቶሪ የዘር ጥራት ፍተሻ ለማከናወን እና ውጤት ለማሳወቅ ታቅዶ 169 ናሙናዎችን በመሰብሰብ የላብራቶሪ የዘር ጥራት ፍተሻ በማከናወን እና ውጤት የማሳወቅ ስራ ተከናውኗል፡፡

### 12.4.2. የጸረ-ተባይና ማዳበሪያ ቁጥጥር

የ320 የፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያ ናሙናዎችን በመውሰድ ፍቱንነታቸው እና ውጤታማነታቸውን ለማረጋገጥ ናሙና በመውሰድ በላቦራቶሪ ወይም በሙከራ እንዲረጋገጥ ለማድረግ፣ ታቅዶ በ280 (87.5%) የፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያ ላይ ተከናውኗል፡፡ ለ240 የምዝገባ መስፈርቱን ላሟሉ ፀረ-ተባይ እና ማዳበሪያዎች ምዝገባ ለማካሄድ፣ ታቅዶ ለ175 (72.9%) ምዝገባ ተደርጓል፡፡ የምዝገባ ዘመናቸው የተጠናቀቀ ለ120 ፀረ-ተባዮች የምዝገባ እድሳት ለማድረግ ታቅዶ ለ102 (85%) ጸረ-ተባዮች ዕድሳት ተደርጓል፡፡ ለ2,600 ለፀረ-ተባይና፣ የማይክሮና ማክሮ ንጥረ ነገር ይዘት ላላቸው ማዳበሪያዎች የቅድመ የማስገቢያ ለመስጠት ታቅዶ ለ2,686 (100⁺%) ተከናውኗል፡፡

### 12.4.3 የእንስሳት መድሃኒት ጥራትና ደህንነት የማረጋገጥ

ለ182 የእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መሳሪያዎች ምዝገባ ሰነዶች ግምገማ ለማድረግ ታቅዶ የ81.5% የእንስሳት መድኃኒትና የህክምና መሳሪያ ሰነድ ግምገማ የዕቅዱን 81.5% ማከናወን ተችሏል፡፡

ለ13 አዲስ የእንስሳት ክትባቶች ሰነድ ግምገማ ለማከናወን ታቅዶ 13 አዲስ የእንስሳት ክትባት ሰነድ ግምገማ ተከናውኗል፡፡ አፈጻጸሙም 100% ሆኗል፡፡ ለ325 የእንስሳት መድሃኒት ተቋማት የብቃት ማረጋጋጫ ለመስጠትና ለማደስ ታቅዶ የ325 የእንስሳት መድሃኒት ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ተሰጥቷል፡፡ ለ80 ዳግም የእንስሳት መድኃኒትና የሕክምና መገልገያ መሳሪያዎች ሰነድ ግምገማ ለማከናወን ታቅዶ 65 (81.25%) ተከናውኗል፡፡ ለ546 የእንስሳት መድኃኒት የቅድመ ማስገቢያ ፍቃድ ለመስጠት ታቅዶ 468 (87%) ተከናውኗል፡፡ 5 የግዢ ፍቃድ ጥያቄዎች አስፈላጊውን መስፈርቱን ስላላሟሉ ውድቅ ተደርገዋል፡፡

ከመቆጣጠሪያ ኬላዎች (Consignment) ተሰብስበው በሚቀርቡ 90 የመድኃኒት ናሙናዎች ላይ የፊዚኮ-ኬሚካል ጥራት ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ 90 የተሰራ ሲሆን አፈጻጸሙ 100% ነው። የክትባት መድኃኒት ናሙናዎች የጥራትና ደህንነት ምርመራ ሥራ በተመለከተ በ10 አይነት የክትባት ናሙናዎች ላይ በቀረበው ጥያቄ መሰረት የምርመራ ሥራ ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን፣ አፈጻጸሙ 100% ነው:: በአጠቃላይ በ281 የእንስሳት ህክምና መድኃኒት ናሙናዎች ላይ የጥራትና ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ 259 (92.2%) ናሙናዎች ላይ የፊዚኮ-ኬሚካልና ማይክሮ-ባዮሎጂ ጥራት ምርመራ ተከናውኗል።

### 12.4.4. የእንስሳት መኖ ተቋማት የብቃት ማረጋጋጫ መስጠትና ማደስ

የእንስሳት መኖ ተቋማት የብቃት ማረጋጋጫ መስጠትና ማደስ 98.72% ተከናወኗል። በኢንስፔክሽን ሪፖርት መሰረት በእንስሳት መኖ ንግድ ተሠማርተው ለሚሠሩ 234 የእንስሳት መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃ አምራቾች፣ አስመጪዎችና ጅምላ ንግድ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ዕድሳት ለማከናወን ታቅዶ ለ231 (98.72%) ተከናውኗል። በመኖ ንግድ ተቋማት ለሚሰሩና በመኖ ንግድ የማማከር ስራ ለተሰማሩ 67 የእንስሳት መኖ ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ ዕድሳት ለማድረግ ታቅዶ ለ53 (79.1%) የብቃት ማረጋገጫ ዕድሳት ተከናውኗል። በ60 የተቀነባበረ/ምጥን የእንስሳት መኖ ናሙናዎች ላይ የጥራትና ደህንነት የላቦራቶሪ ፍተሻ ለማከናወን ከተያዘው ዕቅድ በላይ በ71 የመኖ ናሙናዎች ላይ የጥራት ምርመራ ሥራ ማከናወን ተችሏል። በ60 መኖ ናሙናዎች ላይ የአፍላቶክሲን ደህንነት የላቦራቶሪ ምርመራ ለማካሄድ ታቅዶ በ93 ናሙናዎች ላይ የምርመራ ስራውን ማከናወን ተችሏል። የ3,000 የውጭ ሀገር የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር አምራች ድርጅቶችን የመልካም አመራረት ዶክመንት እና ሰነድ በመገምገም፣ የግዥና የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ ለመስጠት ታቅዶ የ3,974.48 (132.48%) ቶን ድርጅቶችን የመልካም አመራረት ዶክመንት እና ሰነድ በመገምገም የግዥና የቅድመ ማስገቢያ ፈቃድ ለመስጠት ተችሏል።

## 13. ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች

### 13.1 በግብርና የሚፈጠር የሥራ ዕድል

በግብርና ንዑስ ዘርፎች 1,381,842 የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ 1,355,003 የሥራ እድል በመፍጠር የእቅዱን 98 በመቶ ለመፈጸም ተችሏል:: በግብርና ዘርፍ ከተፈጠረው የስራ እድል ውስጥ በቋሚነት 1,021,961 የስራ እድል የተፈጠረ ሲሆን አጠቃላይ ከተፈጠረው የስራ ዕድል ውስጥ የቋሚ ድርሻ 75 በመቶ ድርሻ አለው:: እንዲሁም በጊዜያዊነት 333,042 የተፈጠረ ሲሆን ከተፈጠረው የስራ ዕድል ውስጥ በጊዜዊነት የተፈጠረው 25 በመቶ ይሸፍናል::

ለግብርና ኢንተርፕራይዞች 3,388,876,267 ብር ብድር ለማቅረብ ታቅዶ 121,168,213 ብር ለ1,903 ኢንተርፕራይዞች እና ለ12,154 ተጠቃሚዎች በማቅረብ የእቅዱን 3.6 በመቶ ለመፈጸም ተችሏል፤ ለግብርና ኢንተርፕራይዞች 168,674 ሄ/ር መሬት ለማቅረብ ታቅዶ 98,292 ሄ/ር መሬት ለ43,920 ኢንተርፕራይዞች በማቅረብ 902,112 አንቀሳቃሾች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ አፈጻጸሙ 58.3% ይሆናል፡፡ ለ116,117 የግብርና ኢንተርፕራይዞች የአግሪቢዝነስ ልማት አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 47,466 ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ በማድረግ 41 በመቶ የተፈጸመ ሲሆን ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት በክልሎች ያለው አደረጃጀት የተጠናከረ አለመሆኑ ነው፡፡

## 13.2 ምግብና ስርዓተ ምግብ

ለ52 (16 ሴት) በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት እና ለግብርና ሚኒስቴር የስራ ኃላፊዎች መሰረታዊ የሥርዓተ-ምግብ ጽንሰ ሐሳብ እና ምግብን መሰረት ያደረገ የአመጋገብ መመሪያ፣ የግብርናና የሥርዓተ ምግብ ትስስር፣ ድህረ ምርት እና የምግብ ደህንነት እንዲሁም የምግብ ሥርዓት ላይ የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ከፌደራልና ከክልሎች ለተውጣጡ 31 (6 ሴት) ባለሙያዎች ሥርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ላይ መሰረት ያደረገ መሰረታዊ የንግድ ክህሎት ላይ የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

የተሰባጠረ ምግብ አዘገጃጀትና አጠቃቀም ላይ ለ80 ለመንደሩ ሴት ከፊል አርብቶ አዳር እና ከክልል፣ በስርዓተ-ምግብ ተኮር ግብርና አቅም ግንባታ ፕሮጀክት ከሶማሌ ክልል እና ወረዳዎች ለተውጣጡ 21 (1 ሴት) አካላት በስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና እና በክትትልና ግምገማ መሰረታዊ ፅንሰ-ሃሳብ ላይ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በስልጠናው መጨረሻም የፕሮጀክቱ ወረዳዎች የ2015 እቅዳቸውን እንዲያቅዱ ተደርጓል፡፡ የፕሮጀክቱን ሰራተኞች የአፈፃፀም ግምገማ ተካሄዷል፡፡ በሃረዋ ወረዳ አርሞ ቀበሌ የፍራፍሬ ችግኝ ጣቢያ ለማቋቋም የሚያስችል ቦታ ተመርጧል፡፡ በሶማሊ ክልል በሐረዋ እና ሙላ ወረዳ ለሚገኙ በእንስሳትና ግብርና ፅ/ቤት ባለሙያዎች እና የልማት ጣቢያ ሰራተኞች 46 (12 ሴት) እና 92 (34 ሴት) ለታላሚ ቤተሰቦች በስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ፅንሰ ሀሳብና አተገባበር፣ የተሻሻለ እንስሳት እርባታና አትክልትና ፍራፍሬ ልማት ላይ በአ/አደር ማሰልጠኛ ማዕከል ላይ ተግባር ተኮር ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በብሔራዊ ምግብና ሥርዓተ ምግብ ፖሊሲ ላይ የተቀመጡ ተግባራትን ለ53 (6 ሴት) የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስራ አስፈፃሚዎችና የስርዓተ ምግብ ፎካሎች የማስተዋወቂያ አውደ ጥናት ተካሂዷል፡፡

የስርዓተ ምግብ-ተኮር ግብርና የባህሪ ለውጥ አምጪ ተግባራትን ለማከናወን የሚረዳ የተግባቦት መመሪያ ለማዘጋጀት ታቅዶ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የማዘጋጀት፤ የማስተዋወቅ እና ወደ አማርኛ እና ኦሮምኛ ቋንቋዎች የመተርጎም ስራ ተሰርቷል፡፡ የምግብ ደህንነትና ጥራት እና ድህረ ምርት አያያዝ ስትራቴጂዎች ለማዘጋጀት ታቅዶ አስፈላጊው የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ስትራቴጂው ተዘጋጅቶ ቫሊዴት

ተደርጓል: የማህበረሰቡን የምግብ ደህንነት አያያዝ ችግሮችን የመለየት፤ የባህሪ ለውጥ አምጪ መልዕክቶች የማዘጋጀት እና በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ለማስተላለፍ ታቅዶ የአፍላቶክሲን መንስኤ፣ ጉዳቱና መከላከያ ዘዴዎች በተመለከተ ፅሁፍ ተዘጋጅቷል። በPSNP የበጀት ድጋፍ በ2012 በጀት ዓመት በተመረጡ ወረዳዎች የተከናወኑ የስርዓተ-ምግብ ተኮር ግብርና ስራዎች በተጠቃሚ ቤተሰቦች ላይ ያመጡት ውጤት በአማካሪ ድርጅት ለማስጠናት በታቀደው መሰረት የጥናት ስራው በአማካሪ ድርጅት እንዲጠና ተደርጎ ሪፖርት ተዘጋጅቷል። የሥ/ም/ተ/ግብርና ስትራቴጂ ትግበራ ውጤታማነት ለማስጠናት በታቀደው መሰረት ውጤታማነቱ በአማካሪ ድርጅት የማስጠናት፤ የጥናት ውጤቱን የማስተዋወቅ እና ስትራቴጂውን የመከለስ ስራ ለመስራት የሚያስችል የመጀመሪያ ዙር ረቅቅ ስትራቴጂ ተሰርቷል። ሥ/ም/ተ/ግብርና ላይ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማኑዋል ለማዘጋጀት ታቅዶ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የማሰልጠኛ ማኑዋሉ ተዘጋጅቷል።

**የሥ/ም/ተ ግብርና ሞዴል መንደር ለመመስረት፡-**

ኦሮሚያ ክልል ሻሸመኔ ዙሪያ ወረዳ 128 (64 ሴት) ተሳታፊዎች በተገኙበት የተሰባጠረ ምግብ አዘገጃጀትና አጠቃቀም በተመለከተ በተግባር የተደገፈ ስልጠና ተሰጥቷል። ለ25 (2 ሴት) የክልል፣ የዞንና የወረዳ ከፍተኛ አመራሮች በሥ/ም/ተ/ግብርና እና በሞዴል መንደር ፅንሰ ሃሳብ ላይ ስልጠና ተሰጥቷል። ለወረዳ ባለሙያዎች እንዲሁም በቀበሌ ደረጃ ለሚገኙ የም/ስ/ምግብ ኮሚቴ አባላት፤ በድምሩ ለ123 (17 ሴት) ተሳታፊዎች የሥ/ም/ተ/ግ የስልጠና ማንዋል በመጠቀም ስልጠና ተሰጥቷል። ለ152 (67 ሴት) ታላሚ ቤተሰቦች ከም/ስ/ምግብ አንፃር በመሰረታዊ የንግድ ክህሎት እና Gender Model Family (GMF) ላይ የግንዛቤ ማሳደጊያ ስልጠና ተሰጥቷል። ሥ/ም/ተ/ግብርና ሞዴል መንደሩ የ64 ታላሚ ቤተሰቦች ፕሮፋይል/ መሰረታዊ መረጃ የመሰብሰብና የማደራጀት ስራ ተሰርቷል። ለስድሳ ስድስት ታላሚ ቤተሰቦች ለእያንዳንዳቸው 6 እና በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል በቁጥር 15 በድምሩ 411 ዶሮዎች ሥርጭት ተካሂዷል።

በአማራ ክልል ደ/ኤልያስ ወረዳ ለሚገኙ ለ30 (8 ሴት) ባለሙያዎች፣ የልማት ጣቢያ ሰራተኞች በቀበሌ ደረጃ ለሚገኙ የም/ስ/ምግብ ኮሚቴ አባላት፤ ለ60 (26 ሴት) ታላሚ እና ለ35 (4 ሴት) ከክልል፣ ዞንና ወረዳ ለተውጣጡ አመራሮች በድምሩ 125 (38 ሴት) በም/ስ/ም/ተ/ግብርና እና በሞዴል መንደር ፅንሰ ሃሳብ ላይ ስልጠና ተሰጥቷል። የተሰባጠረ ምግብ አዘገጃጀትና አጠቃቀም ላይ ለ62 (56 ሴት) ታላሚ ቤተሰቦች ከክልል ግብርና ቢሮ እና ከባ/ዳር ዩኒቨርሰቲ ጋር በመቀናጀት በተግባር የተደገፈ ስልጠና ተሰጥቷል። ለ139 (62 ሴት) ታላሚ ቤተሰቦች ከም/ስ/ምግብ አንፃር በመሰረታዊ የንግድ ክህሎት እና Gender Model Family (GMF) ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፤

በቆላማ አካባቢ የኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት ድጋፍ በአፋር ክልል በዱብቲ ወረዳ በአሊኢሳ መንደር ላይ የተከናወነ የስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ሞዴል መንደር ምስረታ ስራ፦ ለታላሚ ቤተሰቦች 700 ፍራፍሬ ችግኝ (ፓፓያ 200 ማንጎ 200፣ ብርቱካን 50 ሙዝ 100 አቮካዶ 150) ተሰራጭቷል።

ከSLM ፕሮግራም ጋር በመሆን በአምስት ክልሎች የሥ/ም/ተ/ግብርና ሞዴል መንደር ለመመስረት በተመረጡ ወረዳዎች የቀበሌና መንደር ልየታ፣ ነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ ጥናት፣ የማስተዋወቂያ መድረክ እና የዕቅድ ዝግጅት ስራ ተከናውኗል።

የሥ/ም/ተ/ግብርና ቅንጅታዊ አሰራርን ለማጠናከር ሀገራዊ መድረክ (NNSA Forum) ፎረሙ የሚመራበት ረቂቅ ሰነድ ተዘጋጅቶ 48 የአጋር አካላትና የምግብና ስርዓተ ምግብ ተወካዮች በተገኙበት የፎረሙ ምስረታና ሰነዱን የማፀደቅ ስራ ተሰርቷል። ለሀያ አራት (4 ሴት) የፎረሙ አባላት በበይነ መረብ በምግብ ስርዓት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል።

ከግብርና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጆች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ለማጠናከር ከስራን ክህሎት ሚኒስቴር እና ከአምስት የግብርና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች ለተውጣጡ 24 (4 ሴት) ባለሙያዎች እና መምህራን በስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ማሰልጠኛ ማኑዋል ላይ ስልጠና ተሰጥቷል። ምግብና ስርዓተ ምግብ ጽ/ቤት ከምርምር ማዕከላት እና ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር ለማሻሻልና በተቋማቱ የሚከናወኑ ስ/ም/ተ/ግብርና ተግባራትን በበጀት ለመደገፍ ለተመረጡ ዩኒቨርሲቲዎች ብር 3,500,000 እና ለምርምር ተቋማት ብር 3,500,000 በድምሩ ብር 7,000,000 ከስ/ም/ተ/ግብርና የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት የበጀት ድጋፍ ተደርጓል።

በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች በተመረጡ ወረዳዎች የዲጂታል መረጃ አላላክ ላይ የተገኙ ጅምር ስራዎችን በተመለከተ ከሚመለከታቸው የሚ/መ/ቤቱ አካላት ጋር ውይይት ተደርጓል፤ የመ/ቤቱ የዲጂታል መረጃ አላላክ ስርዓት ላይ የጋጠሙ ችግሮች ላይ በ7 ክልሎች የዳሰሳ ጥናት እና የጤና ተቋም ልምድ ልውውጥ ስራ ተከናውኗል፤ በዳሰሳ ጥናት ሪፖርቱ መሰረት ሲስተሙ ላይ ያሉ ችግሮችን የመፈተሽ እና የኢንተርኔት ችግርን ለመቅረፍ ከኢትዮጵያ ቴሌኮሚዩኒኬሽን ጋር ለልማት ጣቢያ ሰራተኞች በፓይለት ደረጃ የ2G ሲም ካርድ በመግዛት ለሻሸመኔ ዙሪያ ወረዳ ባለሙያዎች ተሰራጭቶ የነበረ ቢሆንም መስራት ባለመቻሉ ወደ 4G የማሳደግ ስራ እየተሰራ ይገኛል።

በሥ/ም/ተ/ግ አቅም ግንባታ ፕሮጀክት ለሶስቱም የፕሮጀክቱ ክልሎች የሚከናወኑ ተግባራትን በመለየት 23,314,483 ብር የበጀት ድጋፍ ተደርጓል። በየደረጃው የምግብና ሥርዓተ ምግብ አፈፃፀም እና ተቋማዊ አደረጃጀት ላይ በ4 ክልሎች የክትትልና ድጋፍ ስራ ተከናውኗል።

## 13.3 ምግብ ዋስትና

በ2015 በጀት ዓመት 7.9 ሚ/ን ተጠቃሚዎችን ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው- አስር ክልሎች ለመደገፍ በእቅድ የተያዘ ሲሆን በመደበኛ ፕሮግራም 7.9 ሚ/ን ተጠቃሚዎችን በፕሮግራም ደንበኝነት የተያዘ ሲሆን በተጨማሪም በፕሮግራሙ የአደጋ ምላሽ ኮምፖነንት መሰረት በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ማለትም አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ፣ ሲዳማ እንዲሁም ደቡብ ምእራብ ኢትዮጵያ የተከሰተውን ድርቅ መሰረት በማድረግ 4.3 ሚ/ን ተጨማሪ ተጠቃሚዎች የአደጋ ምላሽ ድጋፍ ተደርጓል፤ በዚህም መሰረት በአጠቃላይ ሪፖርቱ እስከሚሸፍነው ጊዜ ድረስ 12.2 ሚ/ን ተጠቃሚዎችን (100+%) መደገፍ ተችሏል።

ለልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የገንዘብ ክፍያ ተጠቃሚዎች በ2014 በጀት ዓመት ተከፍሎ መጠናቀቅ ሲገባው በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ሳይጠናቀቅ ቀርቶ ወደ 2015 በጀት አመት የተላለፈው ብር 285,298,929 የተጠቃሚዎች ክፍያ ሙሉ በሙሉ ለተጠቃሚዎች ለመክፈል ታቅዶ ብር 276,684,636 (98%) ክፍያው ተፈፅሟል። በተመሳሳይ መልኩ ከ2014 በጀት ዓመት ወደ 2015 የተዘዋወረው የምግብ መጠን 20,014.60 ሜ/ቶን ሲሆን ከዚህ ዉስጥ 18103.16 ሜ/ቶን (90%) ወደ ወረዳ ተጓጉዞ ለተጠቃሚዎቹ ተከፍሏል። የገንዘብ ክፍያዉ (8,614,293 ብር) ያልተጠናቀቀበት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በነበረው የፀጥታ ችግር ምክንያት በአማራ ክልል ዋግህምራ ዞን ባሉ አንዳንድ ወረዳዎች የፋይናንስ ተቋማት (ባንክ) አገልግልግሎት መስጠት ባለመጀመራቸው ምክንያት ሲሆን በተመሳሳይ የእህል ክፍያዉ ያልተጠናቀቀበት (አፋር እና ኦሮሚያ) ምክንያት የእህል እጥረት በመከሰቱ ሲሆን ሁኔታዎች እንደተስተካከሉ ክፍያው የሚፈፀም ይሆናል።

በ2015 በጀት ዓመት የቋሚ ቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ ለሆኑ (PDS) እና የማህበረሰብ ልማት የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ክፍያ ብር 11,902,259,150 (100%) ብር ለክልሎች ለመላክ ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ለክልሎች የተላለፈ ሲሆን ሪፖርቱ እስከ ተጠናከረበት ጊዜ ድረስ 10,428,440,369 ብር ለፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ክፍያው መከፈሉ በተደረገ በክትትል ለማወቅ ተችሏል።

በ2015 በጀት ዓመት የእህል ክፍያ ለሆኑ የቋሚ የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ እና የማህበረሰብ ልማት የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ክፍያ የሚሆን 61,333.26 ሜ/ቶን እህል ለመላክ ለብሄራዊ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን እንዲጓጓዝ በተጠየቀዉ መሰረት 44,966.623 ሜ/ቶን እህል (73%) ወደ ማሰራጫ ጣቢያ ደርሶ ለተጠቃሚዎች ማስተላለፍ ተችሏል። በተጨማሪም በአማራ ክልል ለ2 ወረዳዎች ቋሚ ቀጥታ ድጋፍ የሚከፈል እህል ክልሉ በጠየቀው የክፍያ ለውጥ (ከጥሬ ገንዘብ ወደ እህል) 3,083.4 ኩ/ል ተጠይቆ (100%) የተጓጓዘ ሲሆን የተጓጓዘው ሙሉ በሙሉ ለተጠቃሚዎች ተከፍሏል።

በ2015 በጀት ዓመት የክፍያ ወቅታዊነትን 65% ለማድረስ ታቅዶ ሪፖርቱ እስከሚሸፍነው ጊዜ ድረስ በአማካይ 80% ለማድረስ ተችሏል፡፡ በ2015 በጀት ዓመት በአጠቃላይ ብር 15,316,594,985 በጀት ለክልሎች የተላከ ሲሆን ወደ ክልሎቹ ከተላለፈው በጀት ውስጥም ለተጠቃሚዎች ክፍያ የሚውል በጀት ትልቁን ድርሻ (86%) ይይዛል፡፡ በ2015 በጀት ዓመት ከ1.4 ሚ/ን በላይ ኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ ስጠቀሙ የነበሩ ነባር የኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴ ተጠቃሚ ወረዳዎች (የትግራይ ክልል ተጠቃሚዎችን ሳይጨምር) 172 ናቸው፡፡

በክልሎች የተከሰተውን የምግብ ዋስትናን ችግር ለመቋቋም እንዲቻል ፌዴራል ምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ፅ/ቤት የድርቅ ምላሽ ዕቅድ በማዘጋጀት ለአለም ባንክ አቅርቧል፡፡ በዚህም መሰረት የህዳርና የታህሳስ ወር ክፍያ 1,312,398 ለሚሆኑ ተጠቃሚዎች ብር 852,113,473 ለክልሎች የተላለፈ ሲሆን ከዚህ ውስጥም ብር 852,113,473 (100%) ለተጠቃሚዎች ተከፍሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በፈረንጆቹ የቀን አቆጣጠር አንደኛ ሩብ ዓመት DRAPን መሰረት በማድረግ ብር 731,418,420 ለአማራ፣ኦሮሚያ እና ደቡብ ለሚገኙ 1,001,729 ተጠቃሚዎች ድጋፍ ወደ ክልሎቹ የተላለፈ ሲሆን ክፍያዉም 100% ለተጠቃሚዎች ተላልፏል፡፡ በአጠቃላይ በ2015 በጀት ዓመት ሪፖርቱ እስከሚሸፍነው ጊዜ ድረስ ለ4,312,173 ተጠቃሚዎች ብር 2,236,652,331 ድጋፍ ተደርጓል፡፡

የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ተግባራትን በተመለከተ የአፈርና ዉሃ ጥበቃ ስራዎች በ357,581 ሄ/ር መሬት ልየታ ለማድረግ ታቅዶ 190,420 ሄ/ር ተከናዉኗል፡፡ በደቡብ ክልል በ4 ሄክታር የአፈር እና ዉሃ ጥበቃ ስራ ለመስራት ታቅዶ በሁሉም ላይ የተከናወነ ሲሆን ለስነ-ህይወታዊ ስራ 587,684 ችግኞች በፕሮጀክት በጀት ተገዝቶ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡

የአየር ንብረት ተስማሚ ስርፀት ፕሮጀክት (CSM-PSNP) ጋር በጋራ የተዘጋጀው የአየር ንብረት ተስማሚ የእቅድ መመሪያ ማንዋል ተጠናቋል፡፡

## 13.4 የአየር ንብረት ለውጥ

የግብርና ዘርፍን የአካባቢ ደህንነትን ለማረጋገጥና ለአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራትን ለመተግበር የሚያስችል የሃብት ግኝትን ለማሳደግና ሃብት ለማፈላለግ ሁለት ፕሮፖዛሎችን ለማዘጋጀትና ሃብት ለማግኘት ታቅዶ ሶስት ፕሮፖዛሎች ከተለያዩ የልማት አጋራት ጋር በመተባበር ተዘጋጅተዋል፡፡ በዚህም መሰረት ከGIZ-RGIL በተገኘ ፋይናንስ ለግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት አንዛር ስራ የድጋፍ፣ የክትትልና የአቅም ግንባታ ስራ ተሰርቷል፡፡ እንዲሁም የተቀሩት ሁለቱ ፕሮፖዛሎች በ"Global Green Growth Institute (GGGI)" አስተባባሪነት በአለም አቀፍ ደረጃ የአየር ንብረት ለውጥን ለመደረፍ ለተቋቋመው የፋይናንስ ተቋም ለ

Green Climate Fund (GCF) በማቅረብ የተቋሙን የምዝና መስፈርት አሟልተው ተቀባይነት አግኝተዋል፡፡ አፈጻፀሙም 100% ተከናውኗል፡፡

የኢትዮጵያን የረጅም ዘመን ዝቅተኛ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ ስትራቴጂ እንደ አገር በ"Global Green Growth Institute (GGGI)" አስተባባሪነት ሲዘጋጅ የግብርና ዘርፍን የማዘጋጀት ስራ ተከናውኗል፡፡

ከAlliance Biodiversity and CIAT ጋር በመተባበር በተለያዩ ባለድርሻ አካላት (መያድ፣ የግል ባለሃብት፣ ዓለም አቀፍ የልማት አጋራት፣ ማህበረሰብ አቀፍ አደረጃጀቶችና ማህበራት) የሚከናወኑ ከአየር ንብረት ጋር የተስተጋበረ የግብርና ልማት ስራዎችን ዙሪያ ተሞክሮዎች፣ልምዶችና መረጃዎችን ለመለዋወጥ እንዲቻል አገር አቀፍ የምክክር መድረክ National CSA Forum ለማቋቋም እየተሰራ ያለው ስራ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ ይገኛል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖዎችን የሚቀንሱ የማጣጣምያና የማስተሰርይ እንዲሁም ዝቅተኛ የካርበን ልቀት ያላቸው ቴክኖሎጂዎች በእርሻ ማሳዎች 3.67 ሚ/ን ሜ/ቶን CO2e ታቅዶ 2.85፡ የተቀናጀ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ስራዎችን በማከናወን 2.7 ሚ/ን ሜ/ቶን CO2e ታቅዶ 2.15 ተከናዉኗል፡ ፡ የእንስሳት ልማት ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተጣጣሙ፣ የእንስሳትን ምርትና ምርታማነትን የሚጨምሩ ስራዎችን በማጎልበት 4.31 ሚ/ን ሜ/ቶን CO2e ታቅዶ 2.5 በአጠቃላይ ከግብርና ሴክተር የሚለቀቀውን የሙቀት አማቂ ጋዝ 10.68 ሚ/ን ሜትሪክ ቶን CO2e ለመቀነስ ታቅዶ 7.5 ሚ/ን ሜትሪክ ቶን CO2e መቀነስ ተችሏል፡፡ አፈፃፀሙም 70.22% ሲሆን ከዕቅዱ በታች የሆነበት ምክንያት በአገራችን ያለው የመረጃ ቅብብሎሽ ስርዓት ያልተጠናከረ መሆኑ፣ ለዚህ ስራ ሊያግዝ በሚችል መልኩ መረጃን ከማደራጀትና ከማጠናከር አንፃር ክፍተት መኖሩ፣ በየደረጃው የተናበበና የተደራጀ አደረጃጀት አለመኖር፣ እንዲሁም የመረጃ ምንጭ የሆኑ መ/ቤቶች በሚፈለገው ሁኔታና ጊዜ መረጃ ማቅረብ ባለመቻለቸው ትንታኔ ውስጥ ባለመካተቱ ነው፡፡ በመሆኑም የግብርና ሴክተር የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ልኬት ስራን በሚ/መ/ቤታችን ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ለማከናዎን የልኬት፣ዘገባና ማረጋገጥ ስርዓት (MRV System) ተቋሙን በሚመጥን ደረጃ ማጠናከርና ስራውን የሚመጥን አደረጃጀት የመፍጠርና የሰው ኃይሉን የማብቃት ስራ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

በግብርና ኢንቨስትመንት ልማት ፕሮጀክቶች አለምአቀፍና ሀገር አቀፍ የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት ስታንዳርድን መሰረት በማድረግ የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት እንዲያረጋግጡ ለማስቻል በጋምቤላ ክልል አኙዋክና መጃንግ ዞን፣ በአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም፣ በሰሜን ሸዋ እና በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ በመስክ ላይ በመገኘት ስድስት የድጋፍና ክትትል ስራ ለመስራት ታቅዶ ስድስቱም ተከናውኗል፡፡ በግብርና ልማት ዘርፍ ላይ ለተሰማሩ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በአካባቢና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ

ያሉበትን ደረጃ በመገምገምና በተለዩት ችግሮች ዙሪያ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት በማድረግና አስፈላጊውን ግብረ-መልስ የመስጠት ስራ ተከናውኗል። በGreen Climate Fund (GCF) ድጋፍ የሚተገበረው ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ፕሮጀክት በሚተገበርባቸው አስራ ስምንት ወረዳዎች እየተተገበረ ያለውን የማጣጣሚያና የማስተሰርያ ስራዎችን በሚፈለገው ደረጃ መተግበራቸውን የማጣጣሚያና የማስተሰርያ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ አራት የክትትልና ድጋፍ ስራ በማከናወን የተሰሩ ስራዎችን ውጤታማነትንና የታዩ ክፍተቶችን በመስክ በመለየት ድጋፍ በማድረግ በቀጣይ ክፍተቶቹ ለማስተካከል በየደረጃው በመገኘት ግብረ-መልስ የተሰጠ ሲሆን የክህሎት ክፍተቶችን የመለየት ስራም ማከናወን ተችሏል። በተለየው ክፍተትንና የባለሙያውን የስልጠና ፍልጎት ዳሰሳ በማድረግ የአቅም ግንባታ ስራዎች ተከናውኗል። በተጨማሪም የማጣጣሚያና የማስተሰርያ ስራዎችን በስታንዳርዱ መሰረት ያከናወኑ ለሁለት ወረዳዎችና ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ግብርና ጽ/ቤት እውቅና የመስጠት ስራ ተከናውኗል።

በክልሎች በመደበኛው በጀት የሚተገበሩ የማጣጣሚያና የማስተሰርያ ስራዎችን በአግባቡ እየተተገበሩ መሆናቸውን የማጣጣሚያና የማስተሰርያ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ የመከታታል፣ የመደገፍና የማረጋገጥ ስራ አራት ጊዜ ማከናወን ተችሏል።

በተቋሙ ስር የሚገኙ ለ13 የስራ ክፍሎችና ፕሮግራሞች የአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታን ለማጎልበት የሚያስችሉ ስራዎችን ዓመታዊ ዕቅዳቸው ውስጥ በማካተት (mainstream) እንዲያደርጉ የማሳወቅና የመከታተል ስራ ተሰርቷል።

በግብርና ሚኒስቴር፣ በተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም እና ከዓለም ምግብና እርሻ ድርጅት በጋራ ከሚተገበረው Scaling up Climate Ambition on Land Use and Agriculture through NDCs and NAPs (SCALA) Ethiopia Programe ጋር በመተባበር በሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ልኬት፣ ዘገባና ማረጋገጥ ፅንስ ሀሳብ እና መሰረታዊ አተገባበር ዙሪያ በIPCC Software National GHG Inventory Preparation and GHG Data Management ላይ ከዓለም ምግብና እርሻ ድርጅት (FAO) ዋና መ/ቤት በመጡ አለም አቀፍ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች በአራት ዙር ተግባር ተኮር ስልጠናዎች ለፌደራል፣ ለክልል ግብርናና ሌሎች የሚመለከታቸው ለ23 (ሴት-2) ባለሙያዎች ተሰጥቷል።

የGCF እና AF ፕሮጀክት እየተተገበረባቸው ባሉ ክልሎች ያሉ ባለሙያዎች የቅድመ ስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ በማድረግ ፍላጎት ላይ መሰረት ያደረገ Climate Smart Agriculture, Nursery Establishment and Mnagement, Result Based Monitoring, Gender and Climate change በሚሉ ፅንስ ሀሳቦች እና አተገባበር ላይ ለ49 (ሴት-5) ስልጠናው ተሰጥቷል።

ከተለያዩ ክልሎች ለተውጣጡ ባለሙያዎች እና ለአምስት የግብርና ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኮሌጆች (አላጌ፣አጋርፋ፣አርዳይታ፣ሚዛንና ገዋኔ) መምህራን ከአየር ንብረት ጋር የተስተጋበረ የግብርና ልማት (Climate Smart Agriculture/CSA) እና የግብርና ዘርፍ የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት (Environment and Social Safeguard Issues of Agricultural Investment Projects) ዙሪያ የግብዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

## 13.5 የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳዩች

ከሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ ከሲዳማና አማራ ክልሎች ለተዉጣጡ ለ33 (19 ሴት) የግብርናና መሬት አስተዳደር ባለሙያዎች እንዲሁም ለ47 (36 ሴት) ከክልል፣ ከዞንና ወረዳዎች ለተወጣጡ የስርዓተ-ፆታ አስተባባሪዎች፣ የሴቶችና ወጣት አደረጃጀትና የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ፈፃሚዎችና ለባለድርሻ አካላት እንዲሁም ከብቃትና የሰው ሀብት አስተዳደር ሥራ አስፈጻሚ ለተውጣጡ ለ70 (45 ሴት) ባለሙያዎች እና ለ20 የግብርና ባለስልጣን ሴት ፈፃሚዎችና ለሆርቲካልቸር ልማት ባለሙያዎች በስርዓተ-ፆታ ፅንሰ ሀሳብ፣ ስርዓተ-ፆታን አካቶ መስራት፣ ሞዴል የስርዓተ-ፆታ መንደር መፍጠርና በሌሎች ተያያዥ አርዕስቶች ዙሪያ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም በGender Transformative Approaches Toolkit ዙሪያ ከሚኒስቴር መ/ቤቱና ከክልሎች ለተዉጣጡ 45 (30 ሴት) ፈፃሚዎች እና በIntroduction to Social Analysis & Action (SAA) ከተለያዩ የስራ ክፍሎች ለተዉጣጡ 40 (32 ሴት) የሚኒስቴር መ/ቤቱ ፈፃሚዎች የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት ተችሏል፡፡

የተቋሙ የፎረሙ አባላትን ለማጠናከር ያስችል ዘንድ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች /GBV/፣ በራስ-መተማመን ፅንሰ ሀሳብ፣ በኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ስርጭት፣ በፎረሙ አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴና በሌሎች ተያያዥ አርዕስቶች ዙሪያ ለ526 (26 ወንድ) የፎረም አባላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

በተቋሙ የሚገኙ የስራ ክፍሎች ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች በሚያደርጉዋቸው የስራ እንቅስቃሴዎች የስርዓተ ፆታን ጉዳይ በአግባቡ በማካተት እየተገበሩ ስለመሆናቸው ግምገማ ነክ የዉይይት መድረክ የተካሄደ ሲሆን መልካም ተሞክሮ ያላቸው ክፍሎች ለሌሎች ልምድ አካፍለዋል፡፡ ከፌዴራል፣ ክልል፣ ከዞንና ከወረዳ ለተወጣጡ የስርዓተ ፆታ አስተባበሪዎች፣ የማህበራዊ ጉዳይ አስተባባሪዎች ጋር የ2014 በጀት አመት እቅድ አፈጻጸም ግምገማ እና የ2015 በጀት አመት አቅድ ውይይት ተካሂዷል፡፡

በተጠሪ ተቋማት የሚቀረፁ ስትራቴጂዎችዎች፣ ሕጎች፣ መመሪያዎች፣ የአሰራር ስርዓቶች ፕሮግራሞች፣ ፓኬጆች እና በሚዘጋጁ እቅዶችና የአፈፃፀም ሪፖርቶች የሴቶችና ተጋላጭ የህብረተሰብ

ክፍሎች ተሳትፎና ተጠቃሚነት አንፃር መቃኘቱን የመከታተልና የመደገፍ ስራ በመስራት ወቅታዊና ችግር ፈቺ ግብረ-መልስ ተሰጥቷል።

የግብርና ሚኒስቴር በግብርናው ዘርፍ የስርዓተ ፆታን እኩልነት ለማረጋገጥ ከCARE ETHIOPIA ጋር በመተባበር የሴቶችን አቅም የሚያጎለብት WE-GO የተሰኘ ፕሮጀክት በጋራ ቀርፆ ወደ ስራ ተገብቷል፤ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ በሚደረግባቸው ሲዳማ እና አማራ ክልሎች የተጠቃሚዎች መረጣ ተደርጓል። በዚህ መስረት በሁለቱ ክልሎች ላይ 5,200 እማወራዎች እና 4,800 አባ ወራዎች በአትክልትና ፍራፍሬ እሴት ሰንሰለት ላይ ተጠቃሚ ሆነዋል።

በክልሎች በሆርቲካልቸር ዘርፍ /የአበባ እርሻ ልማት ዘርፍን ጨምሮ/፣ የሴቶችን የገበያ ትስስር ችግሮችን በመፍታት ረገድ እየተከናወኑ የሚገኙ ተግባራት በተመለከተ የክትትልና ድጋፍ ስራ ተሰርቷል፤ በየደረጃዉ በሚዘጋጁ እቅዶችና የአፈፃፀም ሪፖርቶች ከሴቶችና ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎና ተጠቃሚነት አንፃር መቃኘቱን የመከታተልና የመደገፍ ስራ ተሰርቷል። በገጠር የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሠርቲፊኬሽን እቅድ አፈፃፀም ሂደት የእማ-ወራዎችና ባለትዳር ሴቶች የተጠቃሚነት ደረጃን ለማረጋገጥ የሚያስችል የክትትልና ድጋፍ ስራ ተሰርቷል፤ የእንስሳት ሀብትና የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በሚከናወኑ ተግባራት የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አርሶ/አርብቶ አደር ሴቶች (ለእማ-ወራዎችና ባለትዳር ሴቶች)፣ ወጣቶችና አካል ጉዳተኞች ፍትሀዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነታቸዉን በተመለከተ የክትትልና ድጋፍ ስራ ተሰርቷል፣ በገጠር በሚፈጠሩ የስራ ዕድሎች መሬት አልባ የሆኑ ወጣቶች (ሴት/ወንድ)፤ ሴቶች በልማቱ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የመሬት፣ የብድር አቅርቦትና የገበያ ትስስር በመፍጠር ረገድ የሚስተዋሉ መሰረታዊ ተግዳሮቶችን ለመፍታት እየተከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ የክትትልና ድጋፍ ስራ ተሰርቷል፤ በተከናወኑ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ወቅታዊና ችግር ፈቺ ግብረ-መልስ ተሰጥቷል።

HIV በደማቸዉ ዉስጥ ለሚገኝ የመስሪያ ቤቱ 14 /አስራ አራት/ ሰራተኞች ድጋፍና እንክብካቤ የማድረግ ስራ ተሰርቷል፤ በመሰሪያ ቤቱ ድጋፍ ለሚደረግላቸው ወላጆቻቸውን በሞት ላጡ 7 /ሰባት/ ህጻናት በገንዘብ ብር 21,000 ድጋፍ ማድረግ ተችሏል፤ እንዲሁም ለቤተሰቦች የትምህርት መርጃ ቁሳቁስ ድጋፍ ተደርጓል።

በኦሮሚያ ክልል ደቡብ ምዕራብ ዞን ወሊሶና ጎሮ ወረዳ የኩታ ገጠም እርሻ ተሳታፊና ተጠቃሚ የሆኑ ሴት አርሶአደሮች በጤፍና በበቆሎ ልማት ያለሙትን በመስክ የመጎብኘትና ተሞክሮዎችን የመቀመር ስራ ተሰርቷል።

የግብርና ሴክተር የስርዓተ ፆታ እኩልነት ስትራቴጂ (GESA) የክለሳ ስራ የመግቢያ ሪፖርት የሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላትን አሳታፊ ያደረገ መድረክ በመፍጠር ሰነዱን የማስተቸትና ግብዓት የማሰባሰብ ስራ ተሰርቷል።

ለአምስት ዓመት አገልግሎት ላይ የዋለው በግብርናው ዘርፍ ስርአት ጾታ እኩልነት ስትራቴጂን (GESA) ለመከለስ አማካሪ በመቅጠር ወደ ስራ ተገብቱዋል። በዚህ መሰረት ኣማካሪ ድርጅቱ ባቀረባቸው የመግቢያና የመጀመሪያ ጥናት ሪፖርት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በመገምገም ግብአት ተሰጥቷል።

የማህበረሰብ ተፋሰስ አጠቃቀምና አስተዳደር መመሪያ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ከስርዓተ ፆታ እና ከማህበራዊ ጉዳይ አኳያ እንዲታይ የግብዓት ማሰባሰቢያ የውይይት መድረክ በማካሄድ በመመሪያዉ እንዲካተት ተደርጓል።

የተቋሙ አመራሮች፣ መሪ ስራ አስፈፃሚ፣ ዴስክ እና ከፍተኛ ባለሙያዎች የስርዓተ ፆታን ጉዳይ ዙርያ ለ97 ተሳታፊ ስልጠና ተሰጥቷል። አጠቃላይ በስራ አስፈፃሚ ስልጠና የወሰዱ ወንድ 632 ሴት 1,435 በድምሩ 2067 ተከናውኗል።

የዶሮ ሃብት ልማትና ግብይት ረቂቅ አዋጅ ዙሪያ የሚ/ር መ/ቤቱ የዶሮ ሀብት ልማት የህግ ባለሙያዎችንና ሌሎች ባለሙያዎችን አሳታፊ በማድረግ ከስርዓተ ፆታ እና ከማህበራዊ ጉዳይ አኳያ እንዲቃኝ የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረክ በማካሄድና ክፍተቶችን በመለየት የማካተት ስራ ተሰርቷል።

ጥምረት ለስርዓተ-ፆታ እኩልነት በሚል በግብርና ሚ/ር መሪነት መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚሳተፉበትና በግብርናው ዘርፍ የስርዓተ ፆታን እኩልነት ለማረጋገጥ የተቋቋመው ጥምረት ዓመታዊ የውይይት መድረክ ተካሂድዋል። በመድረኩም በግብርናው ዘርፍ የሰርዓተ ፆታን እኩልነት ለማረጋገጥ የልምድ ልውውጥ ተደርጓል።

በኦሮሚያ ክልል ደቡብ ምዕራብ ዞን ወሊሶና ጎሮ ወረዳ የኩታ ገጠም እርሻ ተሳታፊና ተጠቃሚ የሆኑ ሴት አርሶአደሮች በጤፍና በበቆሎ ልማት ያለሙትን በመስክ የመጎብኘትና ተሞክሮዎችን የመቀመር ስራ ተሰርቷል። በአማራ ክልል ሜጫ ወረዳ እንዲሁም በሲዳማ ክልል ሸበዲኖ ወረዳ በእማወራ አርሶ አደሮችና በሞዴል የስርዓተ-ፆታ ቤተሰቦች የሴቶችን የስራ ጫና እና ፆታዊ ጥቃቶችን በመቀነስ ረገድ እንዲሁም በተቀናጀ የግብርና ስራዎች የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን በመለየትና በመቀመር ተሞክሮዎችን ለማስፋት የሚያስችል የመስክ ምልከታና የምክክር መድረክ ተካሂዷል።

## 14. የበጀት አጠቃቀም

የበጀት አፈፃፀም በሚመለከት ለሴክተሩ በ2015 በጀት ዓመት በመደበኛ ብር 500.36 ሚ/ን በካፒታል ብር 15,511.18 ሚ/ን በድምሩ ብር 16,011.54 **ሚ/ን** የተፈቀደ ሲሆን በበጀት ዓመቱ መጨረሻም መደበኛ በጀት ብር 500.36 ሚ/ን ታቅዶ ብር 1,113.77 ሚ/ን (100+%) ተከናውኗል፡፡ የካፒታል በጀትን በሚመለከት ብር 15,511.18 ሚ/ን ታቅዶ ብር 22,733.33 ሚ/ን (100+%) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በድምሩ የግብርና ሚኒስቴር በ2015 በጀት ዓመት 16,011.54 ሚሊዮን ታቅዶ 23,847.1ሚ/ን (100+%) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ይህም የበጀት አፈፃፀም **በስራ አመራርና አስተዳደር በ4ቱ ዋና ዋና የግብርና** ዘርፎች የበጀት ዓመቱ የመደበኛ እና የካፒታል ወጪ በተመለከተ፣ **በሥራ አመራርና አስተዳደር የመደበኛ ወጪ ብር** 247.92 ሚ/ን **ዕቅድ ተይዞ** 291.03 ሚ/ን (100+%) ተከናውኗል፡፡ በካፒታል 30.00 ሚ/ን እቅድ ተይዞ 5.30 (17.6%) ተፈጽሟል ፡፡ **የእርሻና ሆርቲካልቸር ልማት ዘርፍ** የመደበኛ ወጪብር 136.56 ሚ/ን እቅድ ተይዞ 542.92 ሚ/ን (100+%) ተፈጽሟል፡፡ በካፒታል ወጪ 1,780.03 ሚ/ን ታቅዶ 1,561.61 ሚ/ን (87.73%) ተፈጽሟል፡፡ የተፈጥሮ ሃብት ልማት እና ምግብ ዋስትና ዘርፍ በመደበኛ ወጪ ብር 24.28 ሚ/ን ታቅዶ 142.16 ሚ/ን (100+%) ተፈጽሟል፡፡ በካፒታል ወጪ 12,337.66 ሚ/ን ታቅዶ 20,299.45 ተከናውኗል፡፡ የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ልማት ዘርፍ የመደበና ወጪ ብር 50.14 ዕቅድ ተይዞ 105.65(100+%) ተፈጽሟል፡፡ በካፒታል 1,363.49 ሚ/ን ታቅዶ 866.97 ሚ/ን ተከናውኗል፡፡ የኢንቨስትመንትና ግብዓትና ግብይት ዘርፍ በመደበኛ ወጪ 41.46 ታቅዶ 32.01 (77.2%) ተፈጽሟል፡፡ ከ100 % በላይ ጥቅም ላይ የዋለበት ምክንያት በመደበኛ በጀት በተፈጥሮ ሀብት ስር የታየው ከእቅድ በላይ በጀት ለአረንጓዴ አሻራ የሚሆን ከገ/ሚ 120 ሚ/ን ብር ተጨማሪ የተፈቀደ ሲሆን፣ በእንስሳት ጤና እና ቬተርነሪ ፐብሊክ ሄልዝ ስር የታየው በጀት ለእንስሳት በሽታ ክስተት መከላከያ የሚሆን ከገንዘብ ሚኒስቴር 62 ሚ/ን ብር ተጨማሪ ስለ ተፈቀደ እና በእፀዋት ጥበቃ ሥር የታየው በጀት ለተባይ መርጫ የሚሆን አውሮፕላን አስተዳደርና መድሃኒት ግብዓት ግዢ ምክንያት ከገንዘብ ሚኒስቴር 406 ሚ/ን ብር ተጨማሪ ስለ ተፈቀደ ነው፡፡

የተጠሪ ተቋማትን በጀት አፈፃፀም በሚመለከት ለተጠሪ ተቋማቱ በ2015 በጀት ዓመት በመደበኛ ብር 1,923.03 ሚ/ን በካፒታል ብር 458.60 ሚ/ን በድምሩ ብር 2,381.63 ሚ/ን የተፈቀደ ሲሆን በበጀት ዓመቱ በመደበኛ በጀት ብር 1,679.06 ሚ/ን (87.3%) በካፒታል ብር 312.33 ሚ/ን (68.1%) በድምሩ ብር 1,991.39 (83.61%) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

## ሠንጠረዥ 1፡ የበጀት አጠቃቀም

| የፕሮግራም/የዉጤት ስም | የ2015 በጀት አመት ፋይናንስ /ሚሊዮን ብር/ | | |
|---|---|---|---|
| | እቅድ | አፈጻጸም | አፈጻጸም (%) |
| **ግብርና ሚ/ር** | 16,011.54 | 23,847.10 | 148.9 |
| የመደበኛ ወጪ | 500.36 | 1,113.77 | 222.6 |
| ካፒታል ወጪ | 15,511.18 | 22,733.33 | 146.6 |
| **የፕሮግራም ስም፡ሥራ አመራርና አስተዳደር** | 277.92 | 296.33 | 106.6 |
| የመደበኛ ወጪ | 247.92 | 291.03 | 117.4 |
| ካፒታል ወጪ | 30 | 5.3 | 17.7 |
| **የፕሮግራም ስም፡የእርሻ ልማት ዘርፍ** | 1,916.59 | 22,546.14 | 1176.4 |
| የመደበኛ ወጪ | 136.56 | 542.92 | 397.6 |
| ካፒታል ወጪ | 1,780.03 | 1,561.61 | 87.7 |
| የፕሮግራም 3፡የተፈጥሮ ሃብት ልማትእና ምግብ ዋስትና ዘርፍ | 12,361.94 | 20,441.61 | 165.4 |
| የመደበኛ ወጪ | 24.28 | 142.16 | 585.5 |
| ካፒታል ወጪ | 12,337.66 | 20,299.45 | 164.5 |
| የፕሮግራም 4፡- የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ልማት ዘርፍ | 1,413.63 | 972.62 | 68.8 |
| የመደበኛ ወጪ | 50.14 | 105.65 | 210.7 |
| ካፒታል ወጪ | 1,363.49 | 866.97 | 63.6 |
| የፕሮግራም 5፡- የኢንቨስትመንትና ግብዓትና ግብይት ዘርፍ | | | |
| መደበኛ ወጪ | 41.46 | 32.01 | 77.2 |
| ካፒታል | | | |
| **ተጠሪ ተቋማት** | **2,381.63** | **1,991.39** | **83.61** |
| መደበኛ | 1,923.03 | 1,679.06 | 87.3 |
| ካፒታል | 458.60 | 312.33 | 68.1 |
| ጠቅላላ ድምር | 18,393.17 | 25,838.49 | 140.48 |
| መደበኛ | 2,423.39 | 2,792.83 | 115.2 |
| ካፒታል | 15,969.78 | 23,045.66 | 144.3 |

## 15. በ9 ወር የአፈጻጸም ግምገማ የተሰጡ አቅጣጫዎች አፈጻጸም

### የግብርና ምርት ጥራትን በማሻሻል ከገበያ የማገናኘት ስራ ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት አጠናክሮ መስራት

የግብርና ምርትን ጥራትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተቀናጀ ክትትልና ድጋፍ በመደረግ ላይ ይገኛል። በዚሁ መሠረት የግብርና ምርት የገበያ ዋጋ ለማረጋጋት ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የመግባቢያ ሰነድ ተፈርሞ በጋራ እየተሰራ የሚገኝ ሲሆን የገበያ ትስስር ለመፍጠርም የጋራ የቴክኒክ ቡድን ተቋቁሞ ወደ ሥራ ተገብቷል። ኤክስፖርት ቁራዎችና የስጋና ወተት ኤክስፖርት ጋር ተያይዞ የሚተገበሩ ጉዳዮችን በጋራ መሥራት የተጀመረ ሲሆን ወደ ውጭ የሚላኩ የግበርና ምርቶች የቁም እንስሳትን ጨምሮ የኮንትሮባንድ ቁጥጥር ላይ ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በጋራ እየተሰራ ይገኛል።

### የእርሻ መሬት አሲዳማነት መስፋፋት ለመቀነስ

የእርርሻ መሬት አሲዳማትን ለመቀነስ የንቅናቄ መድረክ በማዘጋጀትና ከአጋሮችና በለሀቶች ጋር የጋራ ግንዛቤ በመያዝ ወደሥራ ተገብቷል። አሲዳማነትን በኖራ ለማከም የኖራ አቅርቦት በልዩ ትኩረት መስራት ተጀምሯል።

### አረንጓዴ አሻራ

በአረንጓዴ አሻራ የ2015/16 በጀት ዓመት ሚመለከታቸውን ሁሉ በማስተባበር 6.3 ቢ/ን ችግን የችግኝ የተተከለ ሲሆን በቀጣይም እንክብካቤና የመጽደቅ ምጣኔ የመረጃ አያያዝ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል።

### የሌማት ትሩፋት የልማት ሥራን ማስፋፋት

በሁሉም ክልሎች የክልል የጋር የጋራ ግንዛቤ በመፍጠርና ከቀድሞ በተለየ ሁኔታ የግብዓት አቅርቦት እንዲሻሻል ተደርጓል። በ12 ክልሎች 9,057 የወተት፣ 11,125 የዶሮ  እና 2,814 የማር፤ 616 የአሳ እርባታ መንደሮች ተደራጅቷል፤  3,561 የቀይ ስጋ ልማት መንደሮች ተለይቷል። የአንድ ቀን የዶሮ ጫጩቶች የማራጨት ሥራ በከፍተኛ ደረጃ ተሰርቷል።

## 16. የግብርና ሚ.ር የ2015 ዓ.ም ተግዳሮቶች. መፍትሄዎች፣ ተሞክሮዎችና ለ2016 በጀ ዓመት ማሻሻያዎች

| ተ.ቁ | የግብርና ልማት | ያጋጣሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶች | የተወሳዱ የመፍትሔ ዕርምጃዎች | የተገኙ ልምዶችና ተሞክሮዎች | ለ2016 ዕቅድ ዓመት የሚወሰዱ ማሻሻያዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | **የእርሻና ሆርቲክልቸር ልማት** | በአፋር፣ ትግራይና አማራ ክልል በአንዳንድ አካባቢዎች የተከሰተው የአንበጣ ወረርሽኝ፣ | የቅድመ መስጠንቃቂያ ትንበያ በማካሄድ ቀድሞ መከላከል እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በበህላዊ እና ዘመናዊ ዘዴ መከላከል | የተገዙ ርጭት አይሮፕላኖች እና የአሰሳ ድሮኖችን የግብርና ሥራዎችን እየሰሩ ገቢ በማስገኘት በበጀት ራሰቸዉን ችላው ወደ ስራ እንዲገቡ የአሰራር ስርዓት ማበጀት፣ | የምስራቅ አፍሪካ የበረሃ አንበጣ መከላከል ድርጅት አህጉራዊ ተቋም ስለሆነ ለተዛማች ተባዮች መከላከል ወሳኝ አስተዋፅኦ ስላለው ከሌሎች አባል ሀገራት ጋር በምክክር የሚጠናከርበትን መንገድ መቀየስ፣ |
| | | የዝናብ እጥረት፣ወይም ዝናብ መብዛት፣ | ቀድሞ በመተንበይ በዝናብ መብዛት የሚከሰተዉን ጎርፍ መከላከል፣ ከዝናብ ጥገኝነት ለመውጠት የመስኖ አዉተሮችን ማስፋፋት እና ያሉትን ጠግኖ ወደ ስራ ማስገባት፣ | የዝናብ መብዛት ሲኖር እንደ ምቹ አጋጣሚ በመጠቀም የግብርና ውሃን ሰብስቦ ዕጥረት ሲኖር ለልማት ማዋል፡ | በዝናብ መጠር እና መብዛት ያሉ አካባቢዎች በዘመነዊ ዘዴ በካርታ በመለየት አስቸኳይ የመፍትሄ ዕርምጃዎችን መውሰድ፣ |
| | | የተቀረጹ ፍላግሺፕ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ለማድረግ በቂ በጀት ማግኘት ያለመቻል፣ | ፕሮጀክቶችንና ዋና ዋና መደበኛ ተግባራትን በየፕሮግራማቸው ውስጥ በማቀናጀት መተግባር፣ የግል ሴክተር ተሳትፎን ማሳደግ፣ | የፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶች እና ዋና ዋና ተግባራትን በፕሮግራም መርህ መሰረት አቀናጅቶ ለመስራት አሰራሮችን በየደረጃው ፈትሾ ማስተካከል፣ | በ10 ፕሮግራሞች ለ10 ዓመት የተቀረፁ ፕሮጀክቶች (አቮካዶ፣ ሙዝ፣ ቲማቲምና ሽንኩርት፣ ስንዴ፣ ሩዝ...ወዘተ) ወደ ትግበራ እንዲገቡ በመንግስት በኩል የበጀት ድጋፍና የግሉ ሴክተር ተሳትፎ ማሳደግ፣ |
| | | ለ2016 የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ተገቢውን የምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ የውሃ መሳቢያ ሞተሮች፣ የመስኖ ተቋማት ጥገና እንዲሁም ለተግባሩ በቂ የማስፈፀሚያ በጀት ያለመመደብ፣ | | | |

| ተ.ቁ | የግብርና ልማት | ያጋጠሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶች | የተወሳዱ የመፍትሔ ዕርምጃዎች | የተገኙ ልምዶችና ተሞክሮዎች | ለ2016 ዕቅድ ዓመት የሚወሰዱ ማሻሻያዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| 2 | የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ልማት | በቂ የሆነ የተመደበ በጀት በፌዴራል እና በክልል ደረጃ አለመኖር | ከግብርና ሚኒስቴር ፕሮጀክቶች በጀት ተመድቦ ለወረዳና ቀበሌ ባለሙያዎች የግንዛቤ ስልጠና ተሰጥቷል፤ ክልሎችም የተወሰነ በጀት መድቧል፣ | የፌዴራልና የክልል መደበኛ በጀት እና የፕሮጀክቶችን አቀናጅቶ በመተግበር የተሻለና ተደማሪ ውጤት እንዳሚገኝ፣ በየደረጃው ከፕሮጀክቶች ጋር አብሮ ማቀድ | ግብርና ልማት የሚዉሉ ሀብቶችን በየደረጃው አቀናጅቶ በማቀድና በመተግብር ስራ ላይ በማዋል የተመጠጠነ የግብርና ልማት መምጣት ስለሚቻል በዚሁ መልክ ታቅዶ ስራ ላይ ማዋል፣ |
| | | የግል ባለሀብት ተሳትፎ በግብዓትና በቴክኖሎጂ አቅርቦት አናሳ መሆን | በሁሉም ክልሎች ለግል ባለሀብቶች ጥሪ በማድረግና በማወያየት በእንስሳት ልማትና ግብዓት አቅርቦት እንድሳተፉ ጥረት በመድረግ ላይ ናቸው፡፡ | | |
| | | ለባለሙያዎች የአቅም ግንባታና ክህሎት ሥልጠና ለመስጠት የበጀት እጥረት ማጋጠም | ከግብርና ሚኒስቴር ፕሮጀክቶች በጀት ተመድቦ ለወረዳና ቀበሌ ባለሙያዎች የግንዛቤ ስልጠና ተሰጥቷል፤ ክልሎችም የተወሰነ በጀት መድቧል፣ | | |
| | | የእንስሳት መኖ አቀነባባርዎችና አልሚዎች በቂ ድጋፍ አለማግኘት | ወጣቶችን እና ሴቶችን በማደራጀት በእንስሳት መኖ ማልማት እና ማቀነባበር ላይ እንድሳተፉ ተደርጓል፡፡ | የግል በለሀብት ተሳትፎን ማሳደግ፣ የመሬት አቅርቦት በሚፈለገው ደረጃ እንድቀርብ ከክልሎች ጋር በቅንጅት መስራት፡፡ | የፌዴራልና የክልል የተቀናጀ የጋራ ዕቅድ በመውጠት ሁሉም ድርሻዉን እንዲወጠ ማድረግ፣ |
| | | የፈሳሽ ናይትሮጂን ማሽኖች በተደጋጋሚ መበላሸትና በፍጥነት ለመጠገን በጀት አለመኖር | በግብርና ሚኒስቴር በኩል 3 ከፍተኛ አቅም ያላቸው አዳዲስ ማሽኖች ግዥ በህደት ላይ ነው፣ በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት 8 አዳዲስ የፈሳሽ ናይትሮጂን ማሽኖች ተገዝቶ እንድቀርቡ እቅድ ተይዟል፡፡ | የግብዓት እና ቴክኖሎጂ አቅርቦትን ተደጋገፎ በሚፈለገው መጠንና ጥራት ማሳደግ፣ | የግሉን ዘርፍ ተሳትፎና የብድር አቅርቦት ማሻሻል |
| | | የሰው ሰራሽ አዳቃይ (Artificial inseminator) ባለሙያ እጥረት መኖር | አዳድስ አዳቃይ ተክኒሻያኖችን ለማሰልጠን እቅድ ተይዟል፤ በሆለታ የአዳቃይ ቴክኒሻን ማስልጠኛ ማዕከል ማስፋፍያ ግንባታ በመጠናቀቅ ላይ ነው፡፡ | የአቅም ግንባታ ስራዎች ከተቋማት ጋር በማቀናጀት ማሻሻል | የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማለትም አደረጃጀት፣ አሰራር ሥርዓትና የሰው ሀብት ልማት ያለበትን ደረጃ በመፈተሽ በዕቅድ አካቶ ምላሽ መስጠት፣ |
| | | የእንስሳት መድኃኒት፣ የሕክምና ላቦራቶሪ መሳሪያዎች አቅርቦት እጥረት ማጋጠም | የግል የእንስሳት ጤና ግብዓት እና አገልግሎት ሰጪዎችን ለማስፋፋት እየተሰራ ነው፣ የእንስሳት መድኃኒት፣የሕክምና ላቦራቶሪ መሳሪያዎች በሀገር ውስጥ እንድመረቱ ባለሀብቶችን ለመሳብ ጥረት እየተደረገ ነው፣ | የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግ | |

| ተ.ቁ | የግብርና ልማት | ያጋጣሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶች | የተወሳዱ የመፍትሔ ዕርምጃዎች | የተገኙ ልምዶችና ተሞክሮዎች | ለ2016 ዕቅድ ዓመት የሚወሰዱ ማሻሻያዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| 3 | የተፈጥሮ ሀብት ልማት | የአሲዳማ አፈርን ለማከም የሚያስፈልገው የውህድ ግብርና ኖራ በመንግስትና በግል ድርጅቶች የማምረት፣ የማጓጓዝ፣ ለአርሶ አደሩ በካሽና በብድር ለማዘጋጀት በጀት አለመኖር፤ | በግብርና ኖራ የአሲዳማ አፈርን ከማከም አንፃር የተለያዩ የልማት አጋር ድርጅቶችን በማስተባበር መጠነኛ የሆነ አሲዳማ አፈር ለማከም ጥረት እየተደረገ የሚገኝ መሆኑን፣ | የተለያዩ የተፈጥሮ ማዳበሪያ በመጠቀም በለሙ አፈር ላይ እየተመረቱ ያሉ የተለያዩ የግብርና ምርቶች (በኦሮሚያ ክልል፣ በሉሜ ወረዳ) | የአሲዳማ አፈርን ለማከም ለሚያስገኘው ለግብርና ኖራ አቅርቦት ከመንግሥት በቂ በጀት ካልተመደበ የአፈር አሲዳማነት እየጨመረ ሄዶ በሀገራችን የግብርና ምርትና ምርታማነት በእጅጉ እየቀነሰ እንዲሄድ ስለሚያደርግ ትኩረት መስጠት፣ |
| | | የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር እንደ ፕሮግራም በበጀት በበቂ ሰው ሀይል ተደግፎ አለመመራት፣ | የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ማስፈፀሚያ በጀት ችግርን ለመቅረፍ ከሌሎች ነባርና መደበኛ ፕሮግራም በጀት እና ባለው ሰው ሀይል አቀናጅቶ ለማስኬድ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ መሆኑ፣ | በፕሮግራም ደረጃ በመደበኛነት ታቅዶ ሀብት ተመድቦላት መቀጠል እንደአለበት፣ | የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ራሱን የቻለ በጀት ተመድቦ በመርሀ-ግብሩ መሰረት ታቅዶ እንዲመራ ማድረግ፣ |
| | | የስነ-አካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች ጥገና፣ ዕድሳት እና ደረጃ ማሳደግ ተግባራት ላይ በክልሎች በኩል ትኩረት ማነስ፣ | በተፋሰሶች ነባር ስትራክቸሮች ጥገና፣ እድሳት እና ደረጃ ማሳደግ ተግባራት ላይ በክልሎች በኩል ትኩረት እንዲደረግበት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ተሠርቷል፣ | በማህበረሰብ ተፋሰሶች ከኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም ጋር በማስተሳሰር የተቋቋሙ ህጋዊ የተፋሰስ ማህበራት (በአማራ፣ በኦሮሚያ እና በደቡብ ብ.ብ.ህ. ክልሎች) በመጠገንና በመንከበከብ ተጠቃሚ መሆናቸው፣ | የማህበረሰቡን ባለቤትነት የሚያረጋግጡ አሰራሮችን በመንደፍና በማቀድ አጠናክሮ በቅንጅት ከባለድርሻ አካላት ጋር መተግባር፣ |
| | | የግንባታ ዕቃዎች በተላይ የሲሚንቶ እና ብረታ ብረት ዋጋ መናር እና እጥረቶች መስኖ አውታሮች ግንባታ እንዲጓተት ያደረገ መሆኑ፣ | የመስኖ አውታር ግንባታዎችን ለማጠናቀቅ እንዲያስችል ከተቋራጮች እና ከየክልሉ ቢሮ ሀላፊዎች ጋር ምክክሮች ማድረግ የግንባታ ዕቃዎች የዋጋ ንረትና እጥረት ለመፍታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ጥረት እየተደረገ መሆኑ፣ | በመንግስት ካፒታል በጀት ባልተለመደ መልኩ ተመድቦ ባለፉት 4 ዓመታት 6,532.1 ሄ/ር መሬት ሊያለሙ የሚችሉ 98 አነስተኛ መስኖ አውታሮችን በማጠናቀቅ 15,292 ቤተሰብ አ/አደሮችን ተጠቃሚ እንዲሆን መደረጉ (በሁሉም ክልሎች) | የግንባታ ዕቃዎች በተላይ የሲሚንቶ እና ብረታ ብረት ዋጋ መናር እና እጥረቶች ላይ በዘላቂነት የገበያ ማስተካከያ እርምጃዎች ከልተወሰደ በመስኖ አውታሮች ግንባታ ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከትላሉ |

| ተ.ቁ | የግብርና ልማት | ያጋጠሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶች | የተወሳዱ የመፍትሔ ዕርምጃዎች | የተገኙ ልምዶችና ተሞክሮዎች | ለ2016 ዕቅድ ዓመት የሚወሰዱ ማሻሻያዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| | | የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ አለመኖር እና የተሻሻለው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ረቂቅ አዋጅ አለመጽደቅ፤ | የተሻሻለው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ረቂቅ አዋጅ እንዲፀድቅ ለማስደረግ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ቀርቦ ክትትል እየተደረገ መሆኑ፣ | ውጤታማ ለመሆን የገጠር መሬትን በፖሊሲ፣ በስትራቴጂ በአሰራር ሥርዓት መምራት እንደሚገባ፣ | የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት በመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ መሠረት በአግባቡ ካልተመራ በገጠር ያለው የእርሻ መሬት በተለያዩ ፕሮግራሞች እየተቀራመተ በቀጣይ ለግብርና ሥራ የሚሆን መሬት በጣም እየቀነሰ እንዳይሄድ የተጀመሩ ሥራዎችን በመጠናቀቅ ወደ ስራ ማስገባት፣ |
| 4 | የግብርና ኢንቨስትመንት፣ ግብይት እና ግብዓት አቅርቦት | የእንስሳት ግብዓት አቅርቦትና ስርጭት፣ የግብርና ሜካናይዜሽን፣ የከተማ ግብርና አደረጃጀቶች እስከ ክልል ድረስ ወጥነት አለመኖር፣ | ከክልሎችና ባለድርሻ አካላት ፈጻሚዎች ጋር የጋራ የግንኙነት መድረክ በመፍጠር የግብዓት አቅርቦትና ስርጭት ፈጻሚዎች ጋር ቀጣይ የሥራ ግንኙነትን ማጠናከርና አደረጃጀቶችን ማስተካከል | በሁሉም ደረጃ የክልሎችን ሁኔታ ያገናዘበ የተናበቡ ግቦችን የሚያሳካ ፈጻሚ አካል መኖር እንደአለበት፣ | ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ጋር ያለውን የአደረጃጀት መለያየትና የመረጃ አለመናበብ ችግርን ለመፍታት ከክልሎች ጋር በመነጋገር በዘርፉ የታቀዱ ስራዎች ባለቤት ማግኘታቸውን በማረጋገጥ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፣ |
| | | ዓለም አቀፍ የአፈር ማዳበሪያ ዋጋ መናር፣ የአፈር ማዳበሪያን ለማጓጓዝ የሚያስፈልጉ የተለያዩ የአገር ውስጥ ወጪዎች መጨመር፣ እና የሌሎች ግብዓቶች አቅርቦቶች አነሳ መሆን | ለአፈር ማዳበሪያ ግዥ የሚውል የውጭ ምንዛሬ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ቅድሚያ እንዲሰጠው ማድረግ፣ ክልሎች ለግብርና ግብዓቶች በቂ በጀት እንዲመድቡ ማድረግ፣ | የ2016/17 በጀት ዓመት ማዳበሪያና ሌሎች የግብርና ግብዓቶች ከባለድርሻ አካላት ጋር ተባብሮ በማቀናጀት ቀድሞ ግዢዉን መፈጸም፣ አማራጭ ኦርጋኒክ ማዳበሪያዎችን መጠቀም፣ | የማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘር፣ አግሮኬሚካል፣ ኖራ እና የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ዘርፍ ግብዓቶች አቅርቦት ላይ ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከርና ቀጣይነት ያለው ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የግብርና ዘርፍ አቅርቦት ስርዓትን ማሻሻል፣ |
| | | ለግብርና ኢንቨስትመንት (ሰብል፣ ሆርቲካልቸር፣ እንስሳት) የሚውል የመሬት (የማስፋፊያና አዳዲስ) አቅርቦት ችግርና የመሬት ሊዝ ጊዜ አጭር መሆን፣ የብድር አቅርቦት አለመመቻቸት እንዲሁም የመሰረተ ልማት (የሃይል አቅርቦት፣ ቴሌኮም | ከባለድርሻ አካላት ጋር የነበረውን ቅንጅታዊ አሰራር የበለጠ ለማጠናከርና ከዕቅድ ዝግጅት ጀምሮና በየጊዜው በሚደረጉ የአፈጻጸም መድረኮች ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥረት መደረጉ፣ | የተቋማት፣ የፕሮግራሞች እና የፕሮጀክቶች በጋራ መስራትን ከዕቅድ ጀምሮ እስከ ክትትልና ግምገማ የባለድርሻ አካላትን በማሳታፍ ቅንጅታዊ አሰራርን አጠናክሮ መተግባር፣ | በግብዓት አቅርቦት (የእፀዋትና እንስሳት)፣ በከተማ ግብርናና ስራ እድል ፈጠራ፣ በሆርቲካልቸርና ሌሎች የግብርና ስራዎች ኢንቨስትመንት ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር እና የሜካናይዜሽን አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከሚሰሩ ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራርን |

| ተ.ቁ | የግብርና ልማት | ያጋጣሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶች | የተወሳዱ የመፍትሔ ዕርምጃዎች | የተገኙ ልምዶችና ተሞክሮዎች | ለ2016 ዕቅድ ዓመት የሚወሰዱ ማሻሻያዎች |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አገልግሎት፣ መንገድ) በሚፈለገው ደረጃ አለመሟላት፣ | | | በማጠናከር የተቀመጡ ግቦችን አናቦ ለማሳካት በታቀደ ሁኔታ መስራት፣ |

## 17. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

የግብርና ትራንስፎርሜሽንን ለማረጋገጥና ግብርና ለሀገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት የሚጠበቅበትን አስተዋፃኦ ለማበርከት በሚደረገው ጥረት  በቀጣዩ በጀት ዓመት በልዩ ትኩረት ለመስራት የሚፈለጉ ጉዳዮች ተለይተዋል፡፡ በዚሁ መሰረት በየዘርፉ ትኩረት የሚፈልጉ ጉዳዮች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**በሰብልና ሆርቲካልቸር ልማት፡** የቅድመ እና ድህረ-ምርት ሜካናይዜሽን መሳሪያዎች አቅርቦት፣ በሽታን የሚቋቋሙ የሰብል ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት፣ ከአፅዋት በሽታ ሀገራዊ ችግር መስፋፋት ጋር የተጣጣመ በአደረጃጀት፣ በሰው ሀይል፣ በሎጂስቲክ የተጠናቀረ መዋቅር ከክልሎች ጋር በትኩረት መሥራት፡፡

**በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት፡** የዝርያ ማሻሻያ ማዕከላት ማጠናከር፣ የፈሳሽ ናይትሮጂን አምራች ማሽኖች ጥገና፣ የዶሮ ማባዣ ማዕከላት ማሻሻል፣ ላብራቶሪዎች፣ የዶሮ ዝርያ አማራጮች የማፈላለግ፣ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎን ማጠናከር፣ የእንስሳት መኖ አቅርቦትና ዋጋ የሚሻሻልበት ዘዴ የማፈላለግ፣ የወተት ላም ዝርያ ማባዣ ማዕከላት የማጠናከር ሥራ፣የተጀመረውን የሌማት ትሩፋት ኢኒሼቲቭን በግብዓት አቅርቦትና በሥልጠና በመደገፍ ከክልሎች ጋር በቅንጀት መስራት  በእንስሳት ዘርፍ በትኩረት የሚሰሩ ናቸው፡፡

**በተፈጥሮ ሀብት ልማት፡** የመሬት አሲዳማነት ለመከላከል በቂ የኖራ አቅርቦት እንዲኖር  በንቅናቄ የመስራት፤ ለመስኖ አውታር ግንባታ የግንባታ ግብዓት አቅርቦት እጥረትና  የዋጋ መናር  ለማሻሻል በቅንጅት መስራት ፤ ነባር የስነ-አካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች ጥገና፣ እድሳት እና ደረጃ ማሳደግ ተግባራት ላይ ከክልሎች ጋር በትኩረት መስራት፣ የተሻሻለው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ረቂቅ አዋጅ በሚኒስትሮች ም/ቤት እንዲጸድቅ ክትትል ማድረግ በተፈጥሮ ሀብት ዘርፍ በልዩ ትኩረትና ቅንጀት የሚሰሩ ይሆናል፡፡

**በግብርና ኢንቨስትመንትና ግብርና ግብይት፡** ለግብርና ኢንቨስትመንት የመሬት አቅርቦት አሰጣጥ በፌደራልና ክልሎች ጋር መተግበር ፤ በግብርና  ግብዓት አቅርቦትና ሥርጭት፣የግብርና ግብዓት ብድር አቅርቦት  የግብርና ሜካናይዜሽን  አገልግሎት መሻሻል፣የቀረጥ ነጻ ድጋፍ ማሻሻል፣ የከተማ ግብርናን የመደገፍና የማስፋፊት  ሥራዎች በግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፍ በልዩ ትኩረት ሊከናወኑ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ግብርና ዲጂታላይዝ ለማድረግ በየዘርፉ የተጀመሩ ሥራዎች በማጠናከር ግብርናን የማዘመን ሥራዎች በልዩ ትኩረት ሊሰሩ ይገባል፡፡

## 18. ማጠቃለያ

የ2015 በጀት ዓመት የግብርና ዘርፍ አፈጻጸም ከተቀመጠው ጊላማ አኳያ አጠቃላይ አፈጻጸሙ አበረታች ነው፡፡ በ2014 በበልግ ወቅት የተከሰተውን የዝናብ መቆራረጥና መጥፋት በአጠቃላይ ሀገራዊ በምርት ላይ ሊያደርስ የሚችለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቀነስ በመኸር ወቅት በአብዛኞቹ ክልሎች የነበረው ምቹ የዝናብ ስርጭት በተገቢው ለእርሻ ተግባር መጠቀም በመቻሉ የ2014/15 የመኸር ሰብል በመልካም ሁኔታ እንዲገኝ ያስቻለ ከመሆኑም በላይ በየደረጃው የሚገኘው አመራርና ባለሙያው ለተግባሩ የሰጠው ትኩረት ለስኬቱ ከፍተኛ ድርሻ እንደነበረው በመስክ ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በመኸር ወቅት ከማዳበሪያና ምርጥ ዘር አቅርቦት ጋር በተገናኘ የነበሩ ችግሮችን የተለያዩ ስልቶችን አስቀድሞ በመንደፍ በጠንካራ ዲሲፒሊን መምራትና መደገፍ በመቻሉ በሰብልና የሆርቲካልቸር ልማት የተጣሉ ግቦችን በአግባቡ ማሳካት ተችሏል፡፡ በእንስሳት እና ዓሳ ሀብት ልማት ዘርፍ የ2015 አጠቃላይ አፈጻጸም እጅግ አበረታች የሚባል ነዉ፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን የተፈጥሮ ሃብት መመናመንና መራቆትን፣ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ላይ የሁለተኛ ደረጃ የመሬት ልኬትና ሰርቲፍኬት አሰጣጥ ተግባራትን በተያዘለት ጊዜ ድርጊት መርሀ-ግብር መሠረት ለማስኬድ የማስፈፀሚያ በጀት ውስንነት ምክንያት የሚታዩ ክፍተቶችን እንዲሁም ሌሎችም ዙሪያ መለስ ተግዳሮቶችን በየደረጃው ያሉ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ችግሮቹን ደረጃ በደረጃ በመቀነስ የህዝብ ተጠቃሚነትን ከማረጋገጥ አንፃር የተጀመረውን ተግባራት አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ረገድ የተገልጋዮችን ተሳትፎና እርካታን የማሳደግ ሥራዎች ላይ ያተኮረ፣ ደረጃውን የጠበቀ ዘመናዊ የአፈር መረጃ ስርዓት በመገንባት ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ አንፃር የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ጤንነቱና ለምነቱ የተጠበቀ የመሬት ሽፋን ከማሳደግ አንፃር በበጀት ዓመቱ ታቅዶ ወደ ተግባር የተገቡ ሥራዎች ተሰርቷል፡፡

ተፈጥሮን የመንከባከብና የመጠበቅ እና መልሶ ከማገገም ረገድ ከባለድርሻና ከተለያዩ ለጋሽ ድርጅቶች ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሠራርን በማጠናከር በመስኖ የሚለማ መሬት ሽፋን በማሳደግ የግብርና ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ አንፃር የላቀ አስተዋጽኦ ከማበርከትም ባሻገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚን በመገንባት አየር ንብረት ለውጥ ዙሪያ እየተደረገ ያሉ ተግባራት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ባለፉት ሶስት ዓመታት ትግበራ በተገኙ ውጤቶች ላይ በመመስረትና ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሻሻያንና እንዲሁም የግብርና ዘርፍ ማሻሻያ (ሪፎርም) እርምጃዎች በማስቀጠል የግብርና ዘርፍ የሶስት ዓመት (2016-2018 ዓ.ም) የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ መሪ ዕቅዱም ቁልፍ የውጤት መስኮች፣ በየውጤት መስኮች በተመረጡ ቁልፍ አመልካቾች ጊላማዎችን በማስቀመጥ፣ ጊላማዎችን ለማሳካት ሊፈፀሙ የሚገባቸው ተግባራት፣ ለዕቅዱ ማስፈፀሚያ የሚያስፈልገውን የኢንቨስትመንት መጠን፣ የሰው ኃይል፣ የማስፈፀሚያ ስልቶችንና ከሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች የግብርና ዘርፍ የሚፈልጋቸው ግብዓቶችን በዝርዝር እንዲያካትት ተደርጎ ተዘጋጅቷል፡፡

## 19. የ2015 በጀት ዓመት ኢላማዎችና አፈፃፀም

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም በመቶኛ (ዓመታዊ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር ማጎልበት (ክብደት = 15) | | | | | | |
| 1.1 | የዕቅድ ዝግጅት፣ የክትትልና ግምገማ እና የስታቲስቲክስ መረጃ አስተዳደር አሰራር ማሻሻል (ክብደት = 1) | | | | | | |
| 1.1.1 | ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ ዕቅድና ሪፖርት ሰነድ ማዘጋጀት | 0.4 | በቁጥር | 5 | 5 | 5 | 100 |
| 1.1.2 | የክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት | 0.3 | በመቶኛ | 10 | 15 | 12 | 80 |
| 1.1.3 | የዘርፉን የአፈጻጸም መረጃ አያያዝ በቴክኖሎጂ በመደገፍ በሙከራ ደረጃ ማደራጀት | 0.3 | በመቶኛ | 3 | 5 | 5 | 100 |
| 1.2 | የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ማሻሻል (ክብደት = 2) | | | | | | |
| 1.2.1 | ግልጽነት የሰፈነበት የሰው ኃይል ስምሪት ማካሄድ | 0.5 | በመቶኛ | 80 | 20 | 20 | 100 |
| 1.2.2 | ለአመራር እና ለሰራተኞች የሚሰጡ ሥልጠናዎችን ማሳደግ | 0.5 | በቁጥር | 460 | 1300 | 1343 | 100+ |
| 1.2.3 | የውስጥ የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት | 0.5 | በቁጥር | 0 | 1 | 0.5 | 50 |
| 1.2.4 | የሰራተኛ እርካታን በማሳደግ ፍልሰትን መቀነስ | 0.5 | በመቶኛ | 0.8 | 0.6 | 0.6 | 100 |
| 1.3 | የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል (ክብደት = 3) | | | | | | |
| 1.3.1 | የተመደበ በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል (ድርሻ) | 0.5 | በመቶኛ | 94 | 96 | 100 | 100+ |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም በመቶኛ (ዓመታዊ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.3.2 | ነቀፌታ ያለበትን የኦዲት ግኝት መቀነስ | 0.5 | በመቶኛ | | 98 | 98 | 100 |
| 1.3.3 | የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ክፍያን ድርሻ ማሳደግ | 0.5 | በመቶኛ | 68 | 80 | 70 | 87.5 |
| 1.3.4 | የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዢን ድርሻ ማሳደግ | 0.5 | በመቶኛ | 0 | 50 | 44 | 88 |
| 1.3.5 | መሰረታዊ አገልግሎትን በቅልጥፍና በመስጠት የደንበኞችን እርካታ ማሻሻል | 0.5 | በመቶኛ | 80 | 90 | 85 | 94.4 |
| 1.3.6 | የንብረት አያያዝ እና የጥገና ወጪዎችን መቀነስ | 0.5 | በብር | | | | |
| 1.4 | የኢንፎርሜሽን፣ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል (ክብደት = 2) | | | | | | |
| 1.4.1 | መረጃ ቋት ማደራጀት | 0.4 | በመቶኛ | 20 | 40 | 50 | 100+ |
| 1.4.2 | በተቋሙ ወረቀት አልባ አሰራርን መተግበር | 0.3 | በመቶኛ | 0 | 20 | 20 | 100 |
| 1.4.3 | በተቋሙ የሚሰጡ አገልግሎቶችን አቶሜት ማድረግ | 0.3 | በመቶኛ | 0 | 20 | 20 | 100 |
| 1.4.4 | የተገልጋዮችን እርካታ ደረጃ ማሳደግ | 1 | በመቶኛ | 40 | 80 | 70 | 87.5 |
| 1.5 | የአጋርነት እና የህዝብ ግንኙነት አሰራርንና ውጤታማነትን ማሻሻል (ክብደት = 1) | | | | | | |
| 1.5.1 | ለተቋም አቅም ግንባታ በሀገር ውስጥ አጋርነት የተገኘ ድጋፍ | 0.25 | በብር | 0 | 10,000,000 | 10,000,000 | 100 |
| 1.5.2 | ለተቋም አቅም ግንባታ በውጭ ሀገር አጋርነት የተገኘ ድጋፍ | 0.25 | ዶላር | 0 | 0 | 1,125.33 | 100+ |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም በመቶኛ (ዓመታዊ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.5.3 | መረጃዎችን በተለያዩ የተግባቦት ዘዴዎች ተደራሽ ማድረግ | 0.5 | በመቶኛ | 65 | 90 | 90 | 100 |
| **1.6** | **ለተጠሪ ተቋማት እና ለክልሎች የሚደረገውን ድጋፍና ክትትል ማሻሻል (ክብደት = 2)** | | | | | | |
| 1.6.1 | የተጠሪ ተቋማት ዕቅድን ከዘርፍ ዕቅድ ጋር ማናበብና ማጣጣም | 0.25 | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 100 |
| 1.6.2 | የየሩብ ዓመት የተጠሪ ተቋማት ሪፖርት መገምገም | 0.25 | በቁጥር | 4 | 4 | 4 | 100 |
| 1.6.3 | የክልሎችን ዕቅድ ከዘርፍ ዕቅድ ጋር ማናበብና ማጣጣም | 0.5 | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 100 |
| 1.6.4 | በየሩብ ዓመት ከክልሎች ጋር የዘርፍ አፈጻጸም በጋራ መገምገም | 0.5 | በቁጥር | 4 | 4 | 4 | 100 |
| 1.6.5 | ለክልሎች ወቅታዊ የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት | 0.5 | በቁጥር | 13 | 13 | 12 | 92 |
| **1.7** | **የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና የክትትል ሥራዎችን ማሻሻል (ክብደት = 1)** | | | | | | |
| 1.7.1 | በብልሹ አሰራር ዙርያ ጥቆማ ከተደረገባቸው ውስጥ ማስተካከያ የተደረገባቸው | 0.25 | በመቶኛ | 50 | 75 | 75 | 100 |
| 1.7.2 | ለብልሹ አሰራር የተጋለጡ አሰራሮች በጥናት በመለየት የማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብ | 0.25 | በቁጥር | 2 | 2 | 1 | 50 |
| 1.7.3 | የሀብት ምዝገባ ያካሄዱ አመራሮች እና ባለሞያዎች ድርሻ ማሳደግ | 0.5 | በመቶኛ | 27 | 80 | 80 | 100 |
| **1.8** | **የሴቶችና ማሕበራዊ ተሳታፊነትንና ተጠቃሚነትን ማሻሻል (ክብደት = 1)** | | | | | | |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም በመቶኛ (ዓመታዊ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.8.1 | የህጻናት ማቆያ አገልግሎት ተጠቃሚ ሴት ሰራተኞች ብዛት ማሳደግ | 0.25 | በቁጥር | 0 | 5 | 0 | 0 |
| 1.8.2 | ወደ አመራር የመጡ ሴት ሰራተኞች ብዛት ማሳደግ | 0.25 | በቁጥር | 15 | 20 | 18 | 90 |
| 1.8.3 | ሥልጠና ያገኙ ሴት ሰራተኞች ድርሻ ማሳደግ | 0.25 | በቁጥር | 918 | 1395 | 1435 | 100+ |
| 1.8.4 | ለአካል ጉዳተኛ ሰራተኞችና ተገልጋዮች ምቹ የስራ ሁኔታና ቦታ መፍጠር | 0.25 | በመቶኛ | 60 | 70 | 65 | 93 |
| 1.9 | የበጎ አድራጎት እና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎችን ማሻሻል (ክብደት = 2) | | | | | | |
| 1.9.1 | የአረንጓዴ አሻራ ተግባራትን ማካሄድ/ችግኞችን መትከል | 0.5 | በቁጥር | 50,000.00 | 75,000.00 | 75,000.00 | 100 |
| 1.9.2 | የአቅመ ደካማ ማህበረሰቦች የመኖሪያ ቤቶች መገንባት | 0.15 | በቁጥር | 5 | 5 | 5 | 100 |
| 1.9.3 | የአቅመ ደካማ ማህበረሰቦች የመኖሪያ ቤቶች መገንባት | 0.15 | በብር | 5,700,000.00 | 14,700,000.00 | 5,880,000.00 | 40 |
| 1.9.4 | የአቅመ ደካማ ቤተሰብ ተማሪዎች ድጋፍ | 0.15 | በቁጥር | 300 | 300 | 300 | 100 |
| 1.9.5 | የአቅመ ደካማ ቤተሰብ ተማሪዎች ድጋፍ | 0.15 | በብር | 275,100.00 | 500,000.00 | 524,000.00 | 100+ |
| 1.9.6 | ለተለያዩ ማህበራዊ ቀውሶች የተደረገ ድጋፍ | 0.3 | በብር | 80,000.00 | 100,000.00 | 147,000.00 | 100+ |
| 1.9.7 | የተደረገ ደም ልገሳ (ድርሻ ከሰራተኛ ብዛት) | 0.3 | በመቶኛ | 8 | 10 | 10 | 100 |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም በመቶኛ (ዓመታዊ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.9.8 | ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናትን መደገፍ | 0.15 | በቁጥር | 366 | 400 | 400 | 100 |
| 1.9.9 | ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናትን መደገፍ | 0.15 | በብር | 183,000.00 | 200,000.00 | 382,609.00 | 100+ |
| 2 | ገበያ ተኮር የሰብልና ሆርቲከልቸር ምርትና ምርታማነትን ማሻሻል (ክብደት = 25) | | | | | | |
| 2.1 | በአነስተኛ አርሶ አደሮች የለማ ሰብልና ሆርቲከልቸር ማሳደግ (ክብደት = 7) | | | | | | |
| 2.1.1 | አጠቃላይ የለማ መሬት ማሳደግ | 1 | በሚ/ን ሄ/ር | 13.4 | 13.4 | 14.06 | 100+ |
| 2.1.2 | የአዝርዕት ምርት ማሳደግ | 1 | በሚ/ን ኩ/ል | 382.6 | 400 | 393.3 | 98.3 |
| 2.1.3 | የአትክልት፣ፍራፍሬና ስራስር ምርት ማሳደግ | 1.5 | በሚ/ን ኩ/ል | 78.2 | 82.5 | 118.6 | 100+ |
| 2.1.4 | የቡና ምርት ማሳደግ | 1.5 | ሺ.ህ ቶን | 652 | 810 | 761.5 | 94 |
| 2.1.5 | የዋና ዋና ሰብሎች ምርታማነት ማሳደግ (እህል ሰብሎች ብቻ) | 1 | ኩ/ል በሄ/ር | | 31 | 30 | 96.8 |
| 2.1.6 | የገበያ መር ኩታ ገጠም እርሻ አሰራር ማስፋፋት | 0.5 | በሺ.ህ ሄ/ር | 4,740.00 | 6,098.00 | 6,098.00 | 100 |
| 2.1.7 | የገበያ መር ኩታ ገጠም እርሻ አሰራር ተሳታፊ ማስፋፋት | 0.5 | ሚ/ን ቁጥር | 4 | 4 | 7.4 | 100+ |
| 2.2 | በሰፋፊ እርሻ ኢንቨስትመንት የለማ ሰብልና ሆርቲከልቸር ማሳደግ (ክብደት = 5) | | | | | | |
| 2.2.1 | አጠቃላይ የለማ መሬት ማሳደግ | 1 | በሚ/ን ሄ/ር | 0.862 | 1.13 | 0.98 | 80.99 |
| 2.2.2 | የአዝርዕት ምርት ማሳደግ | 1 | በሚ/ን ኩ/ል | 14.54 | 25.4 | 30 | 100+ |
| 2.2.3 | የአትክልት፣ ፍራፍሬና ስራስር ምርት ማሳደግ | 1 | በሚ/ን ኩ/ል | 1.6 | 1.8 | 1.76 | 97.78 |
| 2.2.4 | የቡናና ሻይ ምርት ማሳደግ | 1 | ቶን | 900 | 1879.38 | 899.6 | 47.87 |
| 2.2.5 | የዋና ዋና ሰብሎች ምርታማነት ማሳደግ (እህል ሰብሎች ብቻ) | 1 | ኩ/ል በሄ/ር | 17 | 21 | 31 | 100+ |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም በመቶኛ (ዓመታዊ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.3 | በአነስተኛ አርሶ አደሮች እና በሰፋፊ እርሻ በመስኖ የለማ ሰብልና ሆርቲካልቸር ማሳደግ (ክብደት = 5) | | | | | | |
| 2.3.1 | አጠቃላይ የለማ መሬት ማሳደግ | 1 | በሚ/ን ሄ/ር | 1.062 | 1.413 | 2.27 | 100+ |
| 2.3.2 | የአዝርዕት ምርት ማሳደግ (ስንዴ ብቻ) | 1 | በሚ/ን ኩ/ል | 24.5 | 40 | 47 | 100+ |
| 2.3.3 | የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ማሳደግ | 0.5 | በሚ/ን ኩ/ል | 78.18 | 81.94 | 77.88 | 95 |
| 2.3.4 | የአበባ ምርት ማሳደግ | 0.5 | በሚ/ን ኩ/ል | 1.1 | 1.396 | 1.05 | 75.2 |
| 2.3.5 | የቅመማ ቅመም ምርት ማሳደግ | 1 | ሺ.ህ ቶን | 715 | 802 | 790.2 | 98.5 |
| 2.3.6 | የዋና ዋና ሰብሎች ምርታማነት ማሳደግ (ስንዴ ብቻ) | 1 | ኩ/ል በሄ/ር | | 40 | 35.48 | 88.7 |
| 2.4 | የሰብልና ሆርቲከልቸር ልማት ኤክስቴንሽን አገልግሎቶ ማስፋፋትና ማሳደግ (ክብደት = 2) | | | | | | |
| 2.4.1 | የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ አርሶና አርብቶ አደሮች ብዛት ማሳደግ | 0.5 | በሺ.ህ ቁጥር | 11982 | 12769 | 12191 | 95.4 |
| 2.4.2 | የሙሉ ፓኬጅ ኤክስቴንሽን ተጠቃሚ አርሶና አርብቶ አደሮች ብዛት ማሳደግ | 0.5 | በሺ.ህ ቁጥር | 6952 | 8657 | 5848.6 | 67.56 |
| 2.4.3 | የሞዴል አርሶ/ አርብቶ አደሮች ብዛት ማሳደግ | 0.5 | በሺ.ህ ቁጥር | 3918 | 4114 | 3695 | 89.82 |
| 2.4.4 | የሜካናይዜሽን ተጠቃሚ ማሳደግ (በትራክተር የታረሰ መሬት) | 0.5 | በሺ.ህ ሄ/ር | 2040 | 2850 | 2700 | 94.74 |
| 2.5 | የሰብል ምርምርና ቴክኖሎጂ አገልግሎቶችን ማስፋፋትና ማሳደግ (ክብደት = 2) | | | | | | |
| 2.5.1 | ቴክኖሎጂና የአሰራር ማሻሻያ መረጃ አቅርቦት | 0.5 | ቁጥር | 62 | 342 | 225 | 65.79 |
| | የመነሻ ቴክኖሎጂ ብዜት | | ኩንታል | | 14556 | 12,427 | 85.37 |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም በመቶኛ (ዓመታዊ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.5.2 | | 0.5 | ችግኝ ቁጥር | 625,001 | 2,509,661 | 3,232,664 | 100+ |
| 2.5.3 | የቴክኖሎጂ ማስተዋወቅና ቅድመ ማስፋፋት | 0.5 | ተሳታፊ ቁጥር | 4591 | 18977 | 18613 | 98.08 |
| 2.5.4 | የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች ስልጠና | 0.5 | ተሳታፊ ቁጥር | 3008 | 17084 | 13,262 | 77.63 |
| 2.6 | የዕፀዋት ጥበቃ ስራዎችን ማጠናከር (ክብደት = 2) | | | | | | |
| 2.6.1 | የመደበኛ ተባዮች አሰሳና ቁጥጥር ማሳደግ | 0.25 | ሄ/ር | 133,200 | 160,000 | 175,837 | 100+ |
| 2.6.2 | የተዛማች ተባዮች አሰሳና ቁጥጥር ማሳደግ | 1 | ሄ/ር | 420,000 | 300,000 | 288,342 | 96 |
| 2.6.3 | የመጤና ወራሪ አረሞችን አሰሳና ቁጥጥር ማካሄድ | 0.25 | ሄ/ር | 40,000 | 60,000 | 61,070 | 100+ |
| 2.6.4 | በድህረ ምርት ተባዮች ምክንያት ሊደርስ የሚችለውን የምርት ብክነት መቀነስ | 0.5 | በመቶኛ | 15 | 11 | 5 | 45.5 |
| 2.7 | የከተማ የሰብልና ሆርቲከልቸር ልማት ማስፋፋትና ማሳደግ (ክብደት = 2) | | | | | | |
| 2.7.1 | በሰብል ልማት የተመረተ ምርት ማሳደግ | 0.5 | ሺ.ህ ቶን | | 55.46 | 56.2 | 100+ |
| 2.7.2 | በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተገኘ ምርት ማሳደግ | 1.5 | ሺ.ህ ቶን | | 80.29 | 89.2 | 100+ |
| 3 | ገበያ ተኮር የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ምርትና ምርታማነትን ማሻሻል (ክብደት = 20) | | | | | | |
| 3.1 | የእንስሳትና ዓሳ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ (ክብደት = 6) | | | | | | |
| 3.1.1 | አጠቃላይ የወተት ምርት ማሳደግ | 1 | በሚ/ን ሊትር | 7080.35 | 7505.1 | 8692 | 100+ |
| 3.1.2 | አጠቃላይ የስጋ ምርት ማሳደግ | 1 | በሺ.ህ ቶን | 447.77 | 505 | 491.35 | 97.3 |
| 3.1.3 | የዶሮ ስጋ ምርት ማሳደግ | 0.5 | በሺ.ህ ቶን | 90.6 | 96 | 96 | 100 |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም በመቶኛ (ዓመታዊ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.1.4 | የቆዳና ሌጦ ምርት መጠን ማሳደግ | 1 | በሚ/ን ቁጥር | 18.33 | 19.4 | 19 | 98 |
| 3.1.5 | የማር ምርት ማሳደግ | 0.5 | በሺ.ህ ቶን | 146.7 | 155.58 | 194 | 100+ |
| 3.1.6 | የዓሣ ምርት ማሳደግ | 0.5 | በሺ.ህ ቶን | 73.1 | 106.2 | 101.4 | 94.4 |
| 3.1.7 | የዕንቁላል ምርት ማሳደግ | 1 | በሚ/ን ቁጥር | 3246.5 | 3641.5 | 3918 | 100+ |
| 3.2 | የእንስሳት መኖ ልማት ማስፋፋትና ማሳደግ (ክብደት = 3) | | | | | | |
| 3.2.1 | ከሁሉም የመኖ ምንጮች የተመረተ ጠቅላላ ድርቆ መኖ ምርት ማሳደግ | 1 | ሚ/ን ቶን | 142.89 | 164 | 165 | 100+ |
| 3.2.2 | የተፈጥሮ ግጦሽን የማሻሻያ ቴክኖሎጂዎች፣ ግብዓቶችና አሰራሮች በመጠቀም የተመረተ ድርቆ መኖ ምርት ማሳደግ | 0.5 | ሚ/ን ቶን | 37.1 | 41 | 40 | 98.1 |
| 3.2.3 | የሰብል ተረፈ ምርትን አሰባሰብ፣ አከመቻቸትና አጠቃቀም ማሻሻያ አሰራሮችን በመተግበር የተመረተ ድርቆ መኖ ምርት መጠን ማሳደግ | 0.5 | ሚ/ን ቶን | 63.3 | 70 | 64 | 92.3 |
| 3.2.4 | የግል የአርሶ አደር ግጦሽ መሬትና ሬንጅላንድን የማሻሻያ ስትራቴጂዎችን በመጠቀምና በማልማት የተመረተ ድርቆ መኖ ምርት ማሳደግ | 0.5 | ሚ/ን ቶን | 0.00428 | 5 | 7 | 100+ |
| 3.2.5 | በሁሉም ስነ ምህዳር በመስኖ የመኖ ማልማት ትግበራ ላይ የስልጠናና የመስክ ላይ ድጋፍ በማድረግ ምርት ማሳደግ | 0.25 | ሄ/ር | 15370 | 23,055 | 34,658 | 100+ |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም በመቶኛ (ዓመታዊ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.2.6 | የእንስሳትን የውሃ አቅርቦት ማሳደግ | 0.25 | | | | | |
| 3.3 | የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ እና ቴክኖሎጂ አገልግሎቶችን ማስፋፋትና ማሳደግ (ክብደት = 4) | | | | | | |
| 3.3.1 | የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያ ድርሻ በእንስሳት ዓይነት | 1 | በመቶኛ | 0.04 | 0.05 | | 0 |
| 3.3.2 | የተሻሻለ የእንስሳት ዝርያ የተጠቀሙ አርሶ/ አርብቶ አደር | 1 | በመቶኛ | 0.15 | 0.17 | 0.17 | 100 |
| 3.3.3 | አጠቃላይ የተሠራጨ የአባለዘር | 0.5 | በሚ/ንዶዝ | 786,000 | 1.3 | 1.44 | 100+ |
| 3.3.4 | አጠቃላይ የተሠራጨ ፈሳሽ ናይትሮጂን | 0.5 | በሊትር | 337,850 | 341,500 | 220,900 | 65 |
| 3.3.5 | ተመርጠው የገቡ ለአባለዘር ምርት የሚውሉ ታዳጊ ኮርማዎች | 0.5 | በቁጥር | 25 | 40 | 40 | 100 |
| 3.3.6 | ከውጭ አገር ተገዝቶ ለአባለ ዘር ምርት የሚገቡ ኮርማዎች | 0.5 | በቁጥር | 0 | 140 | | 0 |
| 3.4 | የእንስሳት ጤና አገልግሎት አሰራር ሥርዓት ማስፋፋትና ማሳደግ (ክብደት = 3) | | | | | | |
| 3.4.1 | የእንስሳትን የጤና ክልኒክ አገልግሎት ተደራሽነት ማሳደግ | 0.5 | መቶኛ | 90 | 92 | 92 | 100 |
| 3.4.2 | በስጋት ላይ የተመሰረተ የክትባት አገልግሎት ሽፋን ማሳደግ | 0.25 | መቶኛ | 91 | 92 | 92 | 100.0 |
| 3.4.3 | አጠቃላይ የክትባት አገልግሎት ሽፋን (ድንበር ዘለላ እና ድንበር ዘለል ያልሆነ) | 0.5 | በሚ/ን ቁጥር | 199 | 201 | 151 | 75.1 |
| 3.4.4 | የመመርመር አቅምን በማሳደግ ምላሽ የተሰጣቸው የእንስሳት በሽታ ፍንዳታዎች ክስተት | 0.5 | በቁጥር | 136 | 140 | 98 | 70.0 |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም በመቶኛ (ዓመታዊ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.4.5 | የእንስሳትን ሞት መቀነስ | 0.5 | በቁጥር | 30 | 25 | 25 | 100 |
| 3.4.6 | የበሽታ የአሰሳና ቅኝት ስራ ማካሄድ | 0.25 | በቁጥር | 2 | 3 | 4 | 100+ |
| 3.4.7 | ከቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የፀዳ መሬት | 0.25 | ካ.ኪ.ሜ | 50338.95 | 80000 | 44671 | 56 |
| 3.4.8 | የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ዳግም ወረራ ለመከላከል የተሸፈነ መሬት | 0.25 | ካ.ኪ.ሜ | 96780.94 | 108890 | 65519 | 100+ |
| 3.5 | የእንስሳትና አሳ ምርምርና ቴክኖሎጂ አገልግሎቶችን ማስፋፋትና ማሳደግ (ክብደት = 2) | | | | | | |
| 3.5.1 | ቴክኖሎጂና የአሰራር ማሻሻያ መረጃ አቅርቦት | 0.5 | ቁጥር | 102 | 47 | 29 | 61.7 |
| 3.5.2 | የመነሻ ቴክኖሎጂ ብዜት | 0.5 | እንስሳት ቁጥር | | 1,287,502 | 1,196,555 | 92.94 |
| | | | መኖ በኩንታል | | 466 | 415.12 | 89.08 |
| | | | መኖ በችግኝ | 1,172,622 | 6,383,000 | 8,685,220 | 100+ |
| 3.5.3 | የቴክኖሎጂ ማስተዋወቅና ቅድመ ማስፋፋት | 0.5 | ተሳታፊ ቁጥር | 4289 | 5806 | 1,263 | 21.75 |
| 3.5.4 | የቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች ስልጠና | 0.5 | ተሳታፊ ቁጥር | 4251 | 4740 | 1,272 | 26.84 |
| 3.6 | የከተማ የእንስሳትና ዓሳ ልማት ማስፋፋትና ማሳደግ (ክብደት = 2) | | | | | | |
| 3.6.1 | በእንስሳት ልማት የተገኘ ምርት ማሳደግ | 1 | | | | | |
| | የወተት ምርት | | ሚሊዮን ሊትር | 58 | 230 | 332 | 100+ |
| | የስጋ ምርት | | ሺህ ቶን | 59 | 94 | 95.1 | 100+ |
| | እንቁላል ምርት | | ሚሊዮን | 9 | 768 | 801 | 100+ |
| 3.6.2 | በዓሳ ልማት የተገኘ ምርት ማሳደግ | 0.5 | ኪ/ግ | 0 | 10,150 | 11307 | 100+ |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም በመቶኛ (ዓመታዊ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.6.3 | በሀር ልማት የተገኘ ምርት ማሳደግ | 0.5 | በቶን | | 500 | 483 | 96.6 |
| 4 | ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የግብርና ልማትን ለማረጋገጥ ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ማረጋገጥ (ክብደት = 20) | | | | | | |
| 4.1 | የግብርና ተፋሰስ ልማት ሥራዎችን ማጠናከርና ማስፋፋት (ክብደት = 2) | | | | | | |
| 4.1.1 | ከንክኪ ነጻ የተደረገና ተከልለው እንዲያገግሙ የተደረጉ አካባቢዎች ስፋት | 0.25 | በሺ.ሀ ሄ/ር | 529.708 | 200 | 688.1 | 100+ |
| 4.1.2 | ጥገናና ዕድሳት የተደረገላቸው የማበረሰብ ተፋሰሶች ስፋት | 0.25 | በሺ.ሀ ሄ/ር | 2503.32 | 500 | 928.1 | 100+ |
| 4.1.3 | የተፈሰስ ልማት ሥራዎች የተካሄዱበቸው መሬት | 0.5 | በሺ.ሀ ሄ/ር | 290.72 | 500 | 1804 | 100+ |
| 4.1.4 | በሥነ ህይወታዊ ዘዴዎች የተሸፈኑ የማህበረሰብ ተፋሰሶች ስፋት | 0.5 | በሺ.ሀ ሄ/ር | 438 | 471 | 390 | 82.8 |
| 4.1.5 | በጥምር ደን እርሻ የተሸፈነ መሬት ስፋት | 0.5 | በሚ/ን ሄ/ር | 2.04 | 2.31 | 2.31 | 100 |
| 4.2 | ዘላቂና ውጤታማ የገጠር መሬት አጠቃቀም እና አስተዳደር ሥራዎችን ማጠናከርና ማስፋፋት (ክብደት = 3) | | | | | | |
| 4.2.1 | የተለካና የተመዘገበ ማሳ ብዛት | 1 | በሚ/ን ቁጥር | 2.9 | 1.8 | 2.6 | 100+ |
| 4.2.2 | የሁለተኛ ደረጃ የገጠር መሬት የይዞታ ማረጋገጫ የተሰጣቸው ቤተሰቦች | 0.5 | በሚ/ን ቁጥር | 0.66 | 0.6 | 0.7 | 100 |
| 4.2.3 | የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተዘጋጀለቸውና የተሰጠ ማሳ ብዛት | 0.5 | በሚ/ን ቁጥር | 2.3 | 2.1 | 2.44 | 100 |
| 4.2.4 | አሳታፊ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ያዘጋጁ ቀበሌዎች ብዛት | 0.5 | ቁጥር | 247 | 392 | 410 | 100+ |
| 4.2.5 | የተተገበረ የተቀናጀ የቀበሌ አሳታፊ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ብዛት | 0.5 | ቁጥር | 247 | 424 | 412 | 97 |
| 4.3 | ዘላቂ የአፈር ለምነትና ጤንነት ጥበቃ ሥራዎችን ማጠናከርና ማስፋፋት (ክብደት = 3) | | | | | | |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም በመቶኛ (ዓመታዊ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4.3.1 | መሬትን በማንጣፈፍ የለማ የኮትቻ አፈር | 0.5 | በሄ/ር | 637,419 | 655,000 | 655,000 | 100 |
| 4.3.2 | ታክሞ የለማ አሲዳማ አፈር መሬት ስፋት | 1 | በሄ/ር | 12,081 | 300,000 | 8,671 | 3 |
| 4.3.3 | በእቀባ እርሻ የለማ መሬት ስፋት | 0.5 | በሄ/ር | 11,750 | 25,000 | 25,724 | 100+ |
| 4.3.4 | በህየወ ማዳበሪያ የለማ መሬት ስፋት | 0.5 | በሄ/ር | 135,000 | 170,000 | 197,565 | 100+ |
| 4.3.5 | ጥቅም ላይ የዋለ ብሔራዊ የአፈር መረጃ | 0.5 | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 100 |
| 4.4 | ዘላቂና ውጤታማ የአነስተኛ ይዞታ መስኖ ልማት ውሃ አቅርቦትና አጠቃቀም ሥራዎችን ማጠናከርና ማስፋፋት (ክብደት = 3) | | | | | | |
| 4.4.1 | ለመስኖ ልማት ዝግጁ የሆነ የመሬት ስፋት | 1 | በሺ.ህ ሄ/ር | 40 | 29 | 44.08 | 100+ |
| 4.4.2 | የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/ ከፊል አርብቶ አደር ብዛት | 0.5 | በሺ.ህ ቁጥር | 120 | 114 | 114 | 100 |
| 4.4.3 | በማህበረሰብ የሚተዳደሩ አዳዲስ የመስኖ አውታሮች ግንባታ ብዛት | 0.5 | በቁጥር | 218 | 193 | 120 | 62 |
| 4.4.4 | በቤተሰብ የሚተዳደሩ አዳዲስ የመስኖ አውታሮች ግንባታ ብዛት | 0.5 | በሺ.ህ ቁጥር | 52 | 77 | 63 | 82 |
| 4.4.5 | ህጋዊ ሰውነት ያገኙ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት ብዛት | 0.5 | በቁጥር | 167 | 193 | 201 | 100+ |
| 4.5 | ሀገራዊ የደን ሽፋንንና ልማትን የማረጋገጥ ሥራዎችን ማጠናከርና ማስፋፋት (ክብደት = 4) | | | | | | |
| 4.5.1 | የተጠበቀ ነባር፣ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ደን መሬት ስፋት | 1 | በሚ/ን ሄ/ር | 19 | 19 | 19 | 100 |
| 4.5.2 | በደን የተሸፈነ መሬት ድርሻ | 1 | በመቶኛ | 17 | 20 | 17.2 | 86 |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም በመቶኛ (ዓመታዊ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4.5.3 | የደን ማኔጅመንት ፕላን የተዘጋጀላቸው ደኖች ስፋት | 1 | ሚ/ን ሄ/ር | 0.2 | 0.2 | 0.18 | 90 |
| 4.5.4 | ከደን ምርት ኤክስፖርት የተገኘ የውጪ ምንዛሬ መጠን | 0.5 | በሚ/ን USD | 2 | 10 | 19 | 100+ |
| 4.5.5 | ከደን ሮያሊቲ የተገኘ ሀብት | 0.5 | በሚ/ን ብር | 178 | 250 | 329.33 | 100+ |
| **4.6** | **የብዝሀ ህይወት ጥበቃ ሥራዎችን ማጠናከርና ማስፋፋት (ክብደት = 3)** | | | | | | |
| 4.6.1 | የብዝሀ ህይወት ሀብትንና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀት አሰሳና ቅኝት የተደረገባቸው ቦታዎች | 1 | በቁጥር | 357 | 589 | 594 | 100+ |
| 4.6.2 | የብዝሀ ህይወት ሀብትንና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀትን በዘላቂታዊነት አጠቃቀሙን ለማሳደግ የተሰራጩ ዝርያዎች | 0.5 | በቁጥር | 23,493 | 11,255 | 7,687 | 68 |
| 4.6.3 | የብዝሀ ህይወትና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀት ለመለየት የተካሄደ ጥናት | 0.5 | በቁጥር | | 6,193 | 3,254 | 53 |
| 4.6.4 | የብዝሀ ህይወት ሀብትንና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀትን በዘላቂታዊነት አጠቃቀሙን ለማሳደግ የተወሰዱ የዝርያ ናሙናዎች | 0.5 | የናሙና ቁጥር | 891 | 7,650 | 7,650 | 100 |
| 4.6.5 | ከወራሪ መጤ ዝርያዎች ነፃ የተደረጉ ቦታዎች ሽፋን | 0.5 | በሄ/ር | 31,167 | 20,000 | 23,311 | 100+ |
| **4.7** | **የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስና የመቋቋም አቅምን ማጠናከር (ክብደት = 2)** | | | | | | |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም በመቶኛ (ዓመታዊ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4.7.1 | በተሰሩ የሰብል፣ እንስሳትና የተፈጥሮ ሀብት ልማት የማስተሳሪያ እና የማጣጣሚያ ሥራዎች የቀነሳ የሙቀት አማቂ ጋዝ | 1 | በሚ/ን ቶን | 11 | 10.5 | 7.5 | 70.2 |
| 4.7.2 | የተዘጋጁ የተለያዩ ዓይነት ዝርያ ችግኞች | 0.25 | በቢ/ን ቁጥር | 7.625 | 6 | 7.6 | 100+ |
| 4.7.3 | የተተከሉ የተለያዩ ዓይነት ዝርያ ችግኞች | 0.25 | በቢ/ን ቁጥር | 7.625 | 6 | 7.2 | 100+ |
| 4.7.4 | እንክብካቤ የተደረገለቸው ችግኞች | 0.25 | በቢ/ን ቁጥር | | 7.2 | 7.1 | 98.6 |
| 4.7.5 | የችግኞች የጽድቀት ምጣኔ ማሳደግ | 0.25 | በመቶኛ | | 85 | 84.8 | 99.8 |
| 5 | **በግሉ ዘርፍ የሚመራ የግብርና ኢንቨስትመንት እና ዘመናዊ የግብርና ንግድና ግብይት ልማትን ማረጋገጥ (ክብደት = 20)** | | | | | | |
| 5.1 | **ለሰፋፊ እርሻና እንስሳት ልማት የግል ኢንቨስትመንት ማስፋፋትና ማሳደግ (ክብደት = 3)** | | | | | | |
| 5.1.1 | አዲስ የአዝርዕትና ሆርቲካልቸር ሰብሎች ኢንቨስትመንት ማሳደግ | 1.5 | በሄ/ር | 130,540 | 145,000 | 94,600 | 65.2 |
| 5.1.2 | አዲስ የእንስሳትና ዓሳ ኢንቨስትመንት ማሳደግ | 1.5 | በሄ/ር | 130,000 | 140,000 | 131,760 | 94.1 |
| 5.2 | **የግብርና ዘርፍ የወጪ ንግድን በማሻሻል የኤክስፖርት ገቢ ማሳደግ (ክብደት = 5)** | | | | | | |
| 5.2.1 | የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም የወጪ ምርት ማሳደግ | 1 | በቶን | 311,437.19 | 376,919.87 | 247,591.81 | 66 |
| 5.2.2 | የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርት የወጪ ንግድ ገቢ ማሳደግ | 1 | በሚ/ን | 1,441.88 | 1,824.31 | 1,344.30 | 74 |
| 5.2.3 | የአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ የወጪ ምርት ማሳደግ | 1 | በቶን | 335,804.34 | 526,246.95 | 288,313.86 | 54.8 |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም በመቶኛ (ዓመታዊ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5.2.4 | የአበባ አትክልትና ፍራፍሬ የወጪ ንግድ ገቢ ማሳደግ | 1 | በሚ/ን ዶላር | 628.58 | 770.24 | 658.3 | 85.5 |
| 5.2.5 | የስጋና ወተት ምርቶች የወጪ ንግድ ገቢ ማሳደግ | 0.25 | በቶን | 661,286.30 | 1,120,716 | 867,323 | 77.39 |
| 5.2.6 | የስጋና ወተት ምርቶች የወጪ ንግድ ገቢ ማሳደግ | 0.25 | ሊትር | 805,595 | 1,120,716 | 837000 | 74.68 |
| 5.2.7 | የስጋና ወተት ምርቶች የወጪ ንግድ ገቢ ማሳደግ | 0.5 | በሚ/ን | 2,191.09 | 100.3 | 74.31 | 74.09 |
| **5.3** | **ለግብርና ዘርፍ ልማት የግብዓት አቅርቦትን ማሳደግ (ክብደት = 5)** | | | | | | |
| 5.3.1 | የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ማሳደግ | 2 | ሚ/ን ኩ/ል | 15.2 | 12.876 | 10.8 | 84.4 |
| 5.3.2 | የምርጥ ዘር አቅርቦት ማሳደግ | 1 | ሚ/ን ኩ/ል | 0.92 | 1.5 | 0.82 | 54.7 |
| 5.3.3 | የተሻሻሉ የአንድ ቀን ጫጩት አቅርቦትና ስርጭት ማሳደግ | 0.5 | ሚ/ን ቁጥር | 27 | 31.67 | 35.5 | 100+ |
| 5.3.4 | የዓሳ ጫጩት አቅርቦትና ስርጭት ማሳደግ | 0.5 | በሺ.ህ ቁጥር | 1,117.00 | 1,790.00 | 942.76 | 52.6 |
| 5.3.5 | የእንስሳት መኖ ዘር አቅርቦትና ስርጭት ማሳደግ | 0.5 | በሺ.ህ ቶን | 4.7 | 2.75 | 2.834 | 100+ |
| **5.3.6** | **የብድር አቅርቦት ማሳደግ** | 0.5 | ቢ/ን ብር | 48.1 | 118 | 62.945 | 53.3 |
| **5.4** | **ህብረት ስራ ማህበራት ለኦኮኖሚ ያላቸዉን አስተዋጽኦ ማሳዳግ (ክብደት = 2)** | | | | | | |
| 5.4.1 | በገጠር የኅብረት ሥራ ማህበራት አባለት ማሳደግ | 0.25 | በመቶኛ | 47 | 52 | 52 | 100 |
| 5.4.2 | የሚሰበሰበው የቁጠባ ማሳደግ | 0.25 | ቢ/ን ብር | 3.14 | 5 | 9.31 | 100+ |
| 5.4.3 | የሚሰጥ ብድር ማሳደግ | 0.25 | ቢ/ን ብር | 2.68 | 6 | 15.75 | 100+ |
| 5.4.4 | የኅብረት ሥራ ማህበራትን ካፒታል ማሳደግ | 0.25 | ቢ/ን ብር | 2.39 | 2.28 | 4.74 | 100+ |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም በመቶኛ (ዓመታዊ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5.4.5 | በኅ/ሥ/ማህበራት የግብርና ምርቶች ለአገር ውስጥ ግብይት ማቅረብ | 0.25 | በሚ/ን ቶን | 1.3 | 1.72 | 1.8 | 100+ |
| 5.4.6 | ኅ/ሥ/ማህበራት የግብርና ምርቶች የወጪ ግብይት ዶላር ድርሻ ማሳደግ | 0.25 | በመቶኛ | 15.5 | 17 | 36.1 | 100+ |
| 5.4.7 | ኅ/ሥራ ማህበራት ግብርና ምርቶች የወጪ ግብይት መጠን ድርሻ ማሳደግ | 0.25 | በመቶኛ | 10 | 16 | 22.9 | 100+ |
| 5.4.8 | በኅ/ሥራ ማህበራት የተቋቋሙ የምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ማሳደግ | 0.25 | በቁጥር | 20 | 74 | 120 | 100+ |
| 5.5 | የግብይት ሰንሰለትንና ሥርዓትን በማጠናከር የሀገር ውስጥ የግብርና ምርት አቅርቦትን ማሳደግ (ክብደት = 3) | | | | | | |
| 5.5.1 | የግብርና ግብዓት የኩፖን ሽያጭ ተጠቃሚ አርሶአደሮች ማሳደግ | 0.5 | በቁጥር | 7,756,384 | 6,500,000 | 7,726,144 | 100+ |
| 5.5.2 | በግብርና ግብዓት የኩፖን ሽያጭ የብድር ተጠቃሚ አርሶአደሮች ማሳደግ | 0.5 | በቁጥር | 507,538 | 850,000 | 651,629 | 77 |
| 5.5.3 | ገበያ ትስስር የተደረገለት ምርት መጠን ማሳደግ (የገበያ መር ኩታ ገጠም እርሻ) | 1.25 | የእህል ምርት በኩንታል | 38,135,761 | 41,280,695 | 39,200,000 | 95 |
| | | 0.75 | የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት በኩንታል | 18,151,016 | 18,151,016 | 15,159,226 | 84 |
| 5.6 | በግብርና የሚፈጠር የሥራ ዕድል ማስፋፋትና ማሳደግ (ክብደት = 2) | | | | | | |

| ተ. ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈጻጸም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም (ዓመታዊ) | የ2015 አፈፃፀም በመቶኛ (ዓመታዊ) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5.6.1 | በአዝርዕትና ሆርቲካልቸር ሰብሎች ልማት የሚፈጠር የሥራ ዕድል ማስፋፋትና ማሳደግ | 0.75 | በቁጥር | 603,931 | 671,048 | 531,533 | 79 |
| 5.6.2 | በእንስሳትና ዓሳ ልማት የሚፈጠር የሥራ ዕድል ማስፋፋትና ማሳደግ | 1 | በቁጥር | 308,334 | 604,883 | 477,041 | 79 |
| 5.6.3 | በተፈጥሮ ሃብት ልማትና በሌሎች የሚፈጠር የሥራ ዕድል ማስፋፋትና ማሳደግ | 0.25 | በቁጥር | 67,057 | 135,071 | 346,429 | 100+ |